አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ

በ

ሕይወት አበሩ

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ
ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሐምሌ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ

በ

ሕይወት አበሩ

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ
ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ
አብርሃም አለሙ

ሐምሌ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ

ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፊርማ	ቀን
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ	ቀን

ምስጋና

ከሁሉም በላይ የፅሁፌን ረቂቅ በማረምና በማስተካከል ለተባበሩኝ አማካሪዬ እና አስተማሪዬ አብርሃም አለሙ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መረጃ ለማግኘት ይረዳኝ ዘንድ የትብብር ደብዳቤ የጻፉልኝን የዞን አስተዳደር ጽ/ቤትና የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶችን እንዲሁም የወረዳዎቹ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሀላፊዎችን፣ የልቅሶ ሥርዓተ ክዋኔውን በተሳካ ሁኔታ እንድቀርጽ አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ አቶ በድሉ ካሳ፣ አቶ ጳውሎስ ክፍሌ እና አቶ ቢኒያም ከበደን እንዲሁም መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን የየወረዳዎቹ ማህበረሰብ አባላትንም ሁሉ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

ሰለቸኝ ደክመኝ ሳይሉ መረጃዎችን ወደ አማርኛ ለተረጎሙልኝ አቶ ብርሃኑ ወራቁ፣ አቶ አበበ ሰገሰ እንዲሁም አቶ ካሳ ከበደ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የእኔን ጥሩ በመመኘት ከጎኔ ላልተለዩኝ ቤተሰቦቼ እጅግ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ለስራዬ መቃናት በሃሳብ ከጎኔ ለነበራችሁት ሄለን ኤፍሬም እና አበጀ መንበሩ ምስጋና ይድረሳችሁ። በመጨረሻም ጥናቱን በኮምፒውተር የፃፍሽልኝን ፈይዳ ሰልማን አመሰግንሻለሁ።

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና i

መዳዩ ቃላት vi

አጠቃለሎ vii

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study) 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ 4

1.4 የአጠናን ዘደ 5

1.4.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘደ 5

1.4.1.1 ቃለ መጠይቅ 5

1.4.1.2 ምልከታ 6

1.4.1.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት 7

1.4.2 የመረጃ መተንተኛ ዘደ 7

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት 7

1.6 የጥናቱ ወሰን 8

1.7 የመስክ ተሞክሮ 9

1.8 ያጋጠመ ችግሮችና የመፍትሔ እርምጃዎች 11

2. ክለሳ ድርሳናት 13

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ 13

2.1.1 የልቅሶ ስርዓትና የልቅሶ ስርዓት ክዋኔ 13

2.1.1.1 የልቅሶ ስርዓት 13

2.1.1.2 ክዋኔ 15
2.1.1.3 የመከወኛ ምክንያት 17
2.1.1.4 የክዋኔ ተሳታፊ 17
2.1.1.5 ዓውድ 19
2.1.1.5.1 ተጨባጭ አውድ 20
2.1.1.5.2 ማህበራዊ አውድ 20
2.1.1.6 የክዋኔ አመላካች 21
2.1.1.7 ክዋኝ 23
2.1.1.8 የመከወኛ ቁሶች 23
2.2 የቀብር ስነስርዓት 24
2.2.1 ቅድመ ቀብር ክንውኖች 26
2.2.2 ወቅተ ቀብር ክንውኖች 26
2.2.3 ድህረ ቀብር ክንውኖች 27
2.3 ማህበራዊ ደረጃ እና የለቅሶ ስርዓት 27
2.4 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 30
2.4.1 የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ያጠኑ 31
2.4.2 የልቅሶ ስርዓትን እንዲሁም ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን አያይዘው ያጠኑ 33
3. ማህበረ ባህላዊ ዳራ ምልከታ 48
3.1 መልከዓምድራዊ ገጽታ 48
3.2 ቋንቋ 48
3.3 የመኢኒት ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር 49
3.4 የኢኮኖሚ መሠረት 51
3.5 የአለባበስና የአመጋገብ ሥርዓት 52
3.5.1 የአለባበስ ሥርዓት 52
3.5.2 የአመጋገብ ሥርዓት 54
3.6 የዕደጥበብ ሙያና ሙያተኞች 55

3.7 ማህበራዊ ህይወት 55
3.7.1 የጋብቻ ሥርዓት 55
3.7.2 ጥርስ ነቀላ (ኬት) 57
3.7.3 የልቅሶ ሥርዓት(ሮዋ) 58
3.8 እምነት 59
3.9 ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት 59
3.10 ባህላዊ አስተዳደር 61
4. የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት አከዋወን ትንተና 63
4.1 የልቅሶ ሥርዓት አከዋወን 63
4.1.1 በዕድሜ 63
4.1.1.1 ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ ሄዋን ለደረሱ 63
4.1.1.1.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት 64
4.1.1.1.2 ጊዜሞት ዝግጅት 65
4.1.1.1.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች 67
4.1.1.2 ለእድሜ ባለፀጋዎች 68
4.1.1.2.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት 68
4.1.1.2.2 ጊዜ ሞት ዝግጅት 71
4.1.1.2.3 ድኅረ ቀብር ዝግጅቶች 81
4.1.2 ባህላዊ ስልጣን 83
4.1.2.1 ለባለቃልቻዎች "ኬሬይ" 83
4.1.2.1.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት 84
4.1.2.1.2 ጊዜ ሞት ዝግጅቶች 84
4.1.2.1.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች 86
4.1.2.2 ለጎሳ መሪዎች "ኮመሩት" 86

4.1.2.2.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት 87
4.1.2.2.2 ጊዜ ሞት ዝግጅት 87
4.1.2.2.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች 90
4.2 ከአሚሚት ሁኔታ አንፃር 90
4.2.1 በሰው ለተገደለ 90
4.3 የመኢኒት ብሔረሰብ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ማህበራዊ ተግባራት 92
4.3.1 ታሪክን ከማቆየት አንፃር 93
4.3.2 ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅ አንፃር 95
4.3.3 የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት ከመግለፅ አንፃር 98
4.4 ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓቱን ለትውልድ ለማስተላለፍ ያስቻሉ
መንገዶችና የማህበረሰቡ ትጋት 102
5. ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች 105
5.1 ማጠቃለያ 105
5.2 ይሁንታ 106
ዋቢዎች 108
አባሪዎች

ሙዳዬ ቃላት

ኢርኩት - አስከሬን ለማድረቂያ የሚያገለግል ባህላዊ መድሃኒት

ሴላ - የሰላ ወፍ ላባ

ፔሌች - ጡሩንባ

ቢራች - የሬሳ ሳጥን

ሊያች - ዘንግ

ይሻ - በእግር ላይ የሚደረግ ቃጭል

ሎዋን - ጋሻ

ጋሀ - የአስከሬን ማውጫ ቤት

ጆን - ከፍየል ወይም ከጎሽ ቆዳ የሚሰራ ሴቶች በሃዘንና በጭፈራ ወቅት የሚለብሱት

ሮዋ - የለቅሶ ስርዓት

ሬሲት - አስከሬን

ቻካም - ከእንጨት የሚሰራ ለመቀመጫነትና ለትራስነት የሚያገለግል ቁስ

ቃምጡት - ቡዳ

ቡራሊዳይ - ፉካሮ (በወንዶች የሚቀርብ)

ካክሲዳይ - በሴቶች ለሚች የሚቀርብ የሙገሳ ዘፈን

ኮክሲዳይ - በወንዶች እና በሴቶች ለሚች የሚቀርብ የሙገሳ ዘፈን

ሙራሊያዊ - በቀብሩ ላይ የሚቀጠቀጠው ከብት የሚያሰማው ድምጽ

ኮርባ - በግንዘት ስርዓት የወንድ ብልት ማሰሪያ ሃረግ

በኤች - የሚች ልጆች ሃዘናቸውን ለመግለጽ በባዕድ ሰው የሚቀቡት ጭቃ

ቡንጡላ - ጨሞ ወይም ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ

ከኤራ - ከእንጨት የተሰራ ማበጠሪያ

ጆንግ - ቀብር

የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል - የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ፕሮፋይል

የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት - የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በመኢኒት ብሄረሰብ የልቅሶ ስርዓት ክዋኔ እና በስርዓቱ የሚታዩ ተግባራትን በማሳየት ላይ ያተኮረ ገላጭ ጥናት ነው። ጥናቱ በብሄረሰቡ የሚደረግን የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ማሳየት የሚለውን አላማ ያደረገ ነው። በዚህም ጥናቱ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔውን በመግለጽ በሥርዓቱ ላይ የሚቀርቡ ትእይንቶችን ትርጉምና ተግባራት ያሳያል ።
ጥናቱ የመስክ ምርምርን መሰረት አድርጎ የተካሄደ እንደመሆኑ ከመስክ መረጃዎች ስለ ስርዓቱ እና ስለ ባህሉ እውቀት አላቸው ከተባሉ አዛውንቶች፣ የሀይማኖት መሪዎች (ኔይሬ)፣ የጎሳ መሪዎች (ኮሙሩት)፣ የቤት እመቤቶችና የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊዎች በቃል መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት እንዲሁም በአውዱ በመገኘት በምልከታ ተሰብስበዋል። ለዚህም ይረዱ ዘንድ መቅረጸ ድምጽ፣ የፎቶ ካሜራና ቪዲዮ ተገልግያለሁ።

በዚህም ከቀብር ስርዓት አፈጻጸም፣ ከግንዘት እንዲሁም ከቀብር ቦታ መረጣ እና በስርዓቱ ላይ ከሚከወኑ ድርጊቶች አንጻር የብሄረሰቡን የልቅሶ ስርዓት በሁለት ማህበራዊ ደረጃ እና በአሟሟት ሁኔታ ተከፍሎ የሚፈጸም መሆኑ በጥናቱ ታውቋል። የቀብር ቦታ መረጣው፣ የግንዘት ስርዓቱ ፣ከቅድመ ሞት ገዝፉች እስከ ድህረ ቀብር ያሉ ክንውኖች በሞተው ሰው ማህበራዊ ደረጃ የሚወሰኑና ለሞተው ሰው የሚሰጥን የክበሬታ ቦታ የሚገለጹ ሆነውም ተገኝተዋል። ሌሎች በስርአቱ የሚታዩ ክንውኖች የማህበረሰቡን ታሪክ የማቆየት፣ ማህበራዊ ተቋማትን የማስጠበቅና የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት የመግለጽ ተግባር ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

በማህበረሰቡ አንድ ትልቅ ሰው፣ ኔሬይ ወይም ኮሙሩት ሲሞት በልቅሶ ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ከብቶች ይቀጠቀጣሉ። የሚቀጠቀጡ ከብቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ቢመጣም ይህን ልማዳዊ ድርጊት አለመከወን ከማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት የሚያስገልል ነው። በመሆኑም የማህበረሰቡ አባል ለሟች እንዳለው ቀረቤታ እና እንደተጣለበት ትእዛዝ ከብት በመቀጥቀጥ ዝምድናውንና ሀዘኑን ማሳየት ይገባዋል።

ሌላው የሟችን የልቅሶ ሁኔታ የሚወስነው ጉዳይ የሞተበት ሁኔታ ነው። አንድ ሰው በብሄረሰቡ ታሞ ቢሞት እድሜውና ያለው ማህበራዊ ስልጣን ታይቶ የልቅሶ ስርዓቱ ይከናወናል። ሟች በሰው የተገደለ እነደሆነ ግን ታሞ ከሞተው በተለየ የልቅሶ ስርዓቱ ይፈጸማል።

የጥናቱን ግኝት መሰረት በማድረግ ባህሉ እንዲጠበቅና ቀጣይነት እንዲኖረው ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የዞንና የወረዳ አስተዳደሮች ፣የባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይገባቸዋል።

1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀገር ናት። እንደ ብሔረሰቦቿ ብዛትም በየአካባቢው የተለያዩ ሀገረሰባዊ የአኗኗር ደንቦችና ሥርዓቶች ይታያሉ። ከእነዚህ የአኗኗር ደንቦችና ሥርዓቶች መካከል አንዱ የልቅሶ ሥርዓት ነው።

ነገር ግን ይህን የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔ በጥልቀትና በስፋት የመረመረ ጥናት አላጋጠመኝም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን አውታሮች በዘገባ መልክ ቢቀርቡም የብሔረሰቡን ባህል ያጠኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ተመራማሪዎች በሥርዓቱ የሚታዩ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ክዋኔ ያሳዩበት ጥናት አላጋጠመኝም። ስለዚህ ይህ በመኢኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ላይ የቀረበው ጥናት አብይ ትኩረት የመኢኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓትን በመግለፅ የብሔረሰቡን አመለካከትና እምነት ማሳየት ነው።

ይህ ጥናት በሥርዓቱ ላይ ምን ምን የፎክሎር ዘሮች ይኖራሉ? ምን ምን ፋይዳ አላቸው? በብሄረሰቡ ስንት አይነት የልቅሶ ስርዓቶች አሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

የጥናቱ አደረጃጀት ዋቢዎችንና አባሪዎችን ሳይጨምር በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው። የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የጥናቱን ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮ እና ያጋጠመ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች በቅደም ተከተል የቀረበበት ነው።

በሁለተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳን ቀርቧል። በዚህም የልቅሶ ሥርዓትንና ተያያዥ ጉዳዮችን ርዕሰ ነገራቸው አድርገው የተሰሩ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች እና ለተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡ ጥናቶች ተቃኝተዋል። በንድፈ ሀሳባዊ ክፍሉም እንዲሁ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔን አስመልክቶ የተሰነዘሩ ንድፈሀሳባዊ ዕሑፎች ቀርበዋል።

በሦስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ አካባቢና ህዝብ ተቃኝቷል።በዚህም የመኢኒት ብሔረሰብ የሰፈረበት ቦታ መልከዓምድራዊ ገፅታ፣ ስለብሔረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር፣ቋንቋ፣ እና እምነት የመሳሰሉት ጉዳዮች የተቃኙበት ነው።

አራተኛው የጥናቱ ምዕራፍ የመኢኒት ብሔረሰብ በህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ የቀረበበት ነው። በዚህም በልቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ሂደቶችን ከተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች አንፃር ተተንትነው ቀርበዋል።

አምስተኛው ምዕራፍ ጥናቱ ባለፈባቸው ሂደቶች ውስጥ የተገኙ ውጤቶችን በማጉላት ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች የቀረቡበት ነው። በመጨረሻም ዋቢ መፃህፍትና አባሪዎች ቀርበዋል።

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)

የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ የሆነው የለቅሶ ስርአት የተለያዩ ማህበራዊነት ያላቸው ተግባራት የሚስተዋለቡበት ነው። በስርዓቱ የሚታዩ ክንውኖችን ከአራቱ የፎክሎር የጥናት መስኮች ጋር ተያያዥነት አላቸው።

ይኸውም በስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ልማዳዊ ተግባራት (እንደባህሉ ቢለያይም) ከብት ማረድ፣ ከብት መቀጥቀጥ፣ የአስከሬን ሳጥን ለብሶት የነበረውን ልብስ ቤት በር ላይ ማንጠልጠል፣ ዳስ ወይም ጎጆ ሲፈርስ ዶሮ፣ በግ... ማረድ፣ ቡና፣ ቂጣ፣ ቆሎ ወዘተ ማዘጋጀት። የመሳሰሉት ልማዳዊና እምነታዊ ተግባራት ዓላማቸው ሟችን ለማስታወስ፣ ለሟች ያለን ክብር ለመግለጽ፣ አንዳች የሚፈራ መንፈስን ለመለማመን ሊሆን ይችላል። ምድባቸው ግን ሀገረሰባዊ ልማድ(social folk coustm)ውስጥ ነው። ስርዓቱ ሲከወን አብረው የሚታዩ እንደ ሙሾና ረገዳ የመሳሰሉት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት(performing folk arts)ውስጥ ይካተታሉ።በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ሀይማኖታዊና ልማዳዊ ተግባራት ለማካሄድና ለማልቀሻነት የሚወጡ ቁሶች እነደ ጋሻ፣ ጦር፣ ዘንግና አልባሳት (የሟች) ጌጦች ወዘተ. ደግሞ በቁሳዊ ባህል(material culture)የሚፈረጁ ናቸው።የሙገሳ ግጥሞች ደግሞ በስነቃል(oral literature) ስር ይመደባሉ (ፈቃደ፤ 1991፡10፤ Dorson 1972:2-4)።

የፎክሎር ዘሮች ከሚጠበቁበት እና ከትውልድ ትውልድ ከሚተላለፉበት መንገድ አንዱና ዋነኛው ክዎኔ ነው (ፈቃደ፤ 1984:3-5)። ይህ ጥናትም የመኢኒት ብሄረሰብን የለቅሶ ስርአት ክዋኔና በስርአቱ ላይ የሚደረጉ ክንውኖችን፣የመከወኛ ቁሶችን ተግባር በጥምረት የሚያሳይ ነው።

አብዛኛው ህዝብ የሰርካዊ ህይወቱን የሚመራው በሀገረሰባዊ ልማድ እንደመሆኑ እነዚህን የተለያዩ የኑሮ ዘይቤዎችንና ደንቦችን አጥንቶ ዘመናዊ አሰራሮችን በነዚህ ላይ መመስረት ይቻላል ።ነገር ግን በዚህ ረገድ እምብዛም አልተሰራም። ስለሆነም ጥንታዊ የሆነው የራሱን ክዋኔ ላይ ምን ምን ተግባራት ለምን አላማ ይተገበራሉ የሚለውን ነጥብ ጥናቱ ይመረምራል። ጥናቱ ገላጭ እንደመሆኑ ዋና ትኩረቱ ማሳየት ነው።

አንድ ማህበረሰብ የእርስ በእርስ ግንኙነቱን ከሚያጸናባቸው አጋጣሚዎች መካከል የልቅሶ ስርአት አንዱ ነው።በዚህም የማህበረሰቡ አባላት ማህበራዊ ህይወትን የሚያጠነክሩ ባህልና

አመለካከትን የሚገለጹ ተግባራትን ይከውናሉ። ነገር ግን በለቅሶ ስርዓት አማካኝነት የሚገለጹ ተግባራትን አንድምታ መርምሮ የባህሉን ባለቤት አመለካከትና እሳቤ ያመለከተ ጥናት አላጋጠመኝም።ስለሆነም በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት ለመመላት ይህ ጥናት የራሱ ድርሻ ይኖረዋል።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የልቅሶ መነሻ የተለያየ ሊሆን ይችላል ። ከነዚህ ምክንያቶች መካከል በሞት ጊዜ የሚከወነው የተለየና የራሱ ሥርዓት ያለው ነው። ይህ አጋጣሚ እንደማህበረሰቡ ባህልና ልማድ ቢለያይም በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው። ሞት የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ። ይህ ልማዳዊ ስርዓት ፎክሎር ትኩረት ሰጥቶ ከሚያጠናቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው።

በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ ሰው ሲሞት በተለያዩ መንገዶች የልቅሶ ስርዓቱ ይፈጸማል።ይህ እንደማህበረሰቡ ልማድ፣ባህልና ሀይማኖት የሚለያይበት አጋጣሚ ይኖራል።በዚህም መሰረት በመሪር ሀዘን ወይም በጭፈራና በዘፈን ስርአቱ ደምቆ የሚፈጸምበት ሁኔታ አለ።

ይህ ጥናት በተካሄደበት ማህበረሰብ ዘንድ የለቅሶ ስርዓት አፈጻጸምን የሞተው ሰው እድሜና በባህላዊ ስልጣን ይወስኑታል። በእድሜ ትለቅ ሰው ሲሞት ለህጻን ወይም ለወጣት ከሚደረገው ክንውን በተለየ ይካሄዳል ። በለቅሶ ፋንታ ዘፈን በሙሾ ፋንታ ፉከራ ይከወናል። የባህላዊ ስልጣን ባለቤት የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ የተለያዩ እምነታዊ ድርጊቶች ተከናውነው በጭፈራ፣ በዘፈንና በፉከራ የሀዘን ስርዓቱ ይፈጸማል። ይህ ልዩነት ትኩረቴን ከሳቡት ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው ነው። ሌሎች የመነሻ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

1. በስራ አጋጣሚ በአካባቢው በተለያየ ጊዜ በሞቱ ሰዎች የለቅሶ ስርአት ላይ በመገኘት የተለያዩ ስርዓቶች ሲከወኑ መመልከቴ ይህን ርእስ እንድመርጥ አነሳስቶኛል ፣

2. በብሄረሰቡ የለቅሶ ስርአት ላይ የሚታዩ ፎክሎራዊ ተግባራትን ክዋኔ ማእከል ያደረገ ጥናት አለመደረጉ፣

3. በብሄረሰቡ የሚከወነው የለቅሶ ስርአት በተለያዩ ዘመናዊ እውቀቶች ፣ዘመናዊ ሃይማኖቶችና ዘመናዊ አስተዳደሮች ተጽእኖ ነባር ይዘቱ እየተለወጠ በመሆኑ፣

4. የልቅሶ ስርአቱ ነባር ይዘት በተለያዩ ምክንያቶች ዕየተለወጠ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ያለውን ክፍኔ በቴፕ በመቅረጽ ፣በፎቶግረፍ በማንሳትና በጽሁፍ በመዘጋጀት እዲታወቅ የማደረግ ፍላጎት ስላደረብኝ ለማጥናት ተነሳስቻለሁ።።

1.3 የጥናቱ ዓላማ

"የመኢሃት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት አከዋወን" በሚል ርዕስ የተካሄደው ጥናት ዋና አላማ በብሄረሰቡ የልቅሶ ስርዓት ላይ ገለጭ ትንተና በማድረግ የልቅሶ ስርዓቱን ማሳየት ነው።የጥናቱ ዝረዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የልቅሶ ሥርዓቱ በብሔረሰቡ ውስጥ ከሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ አንፃር እንዴት እንደሚከወን ማጥናት፣
2. በልቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚደረጉ ክንውኖችን ትርጉም ማሳየት፣
3. የብሔረሰቡን በህላዊ የለቅሶ ሥርዓት ከትውልድ ትውልድ በማሸጋገር በኩል የማህበረሰቡ ትጋት ምን ይመስላል የሚለውን ማጥናት፣
4. የልቅሶ ስርዓት ክንውኑን ከመግለጽ ባሻገር የክንውኖችን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት፣
5. የልቅሶ ስረአቱ መቼና የት እንደሚከወን በመግለጽ ከዋኝን እና የተሳታፊዎችን ሁኔታ ማሳየት።።

ከዚህ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይገመታል።።

- የመኢሃት ብሔረሰብ ስለ ልቅሶ ያለው እሳቤ ምን ይመስላል?
- በብሔረሰቡ የልቅሶ ሥርዓቱን በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ደንብና ሥርዓት ምን መልክ አለው?
- የብሔረሰቡ አባላት ሥርዓቱን በማስቀጠል ረገድ ምን ሚና ይጫወታሉ?
- በብሔረሰቡ ስንት አይነት የልቅሶ ሥርዓቶች አሉ?
- በልቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚንፀባረቁ ክንውኖች ተግባር ምን ይመስላል?

1.4 የአጠናን ዘዴ

አንድ ጥናት ታላሚ አድርጎ እንደተነሳው ነጥብ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶችን መወሰን የአጥኚው ተግባር ነው። በመሆኑም አጥኝው መስክ ከመውጣቱ በፊት በመስክ ቆይታው መረጃን እንዴትና በምን ሁኔታ መሰብሰብና መተንተን እንዳለበት ይወሰናል።

ይህ ጥናትም ከአብያተ መፃህፍት ከሚገኙ መረጃዎች በተጨማሪ የመስክ ምርምርን የሚጠይቅ በመሆኑ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበዋል።

1.4.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ የሚያገለግሉ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመጠቀም ነው።በአውዱ በመገኘት ትዕይንቶችን በቪዲዮ በመቅረጽ፣ በፎቶግራፍ በማንሳትና በድምጽ በመቅረፅ መረጃ ተሰብስቧል።

ከመስክ በፊትም ስለብሔረሰቡ አጠቃላይ ገፅታ መረጃ ለማግኘት የተለያዩ የፅሑፍ መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥልቅ ንባብ ተካሂዷል። በመቀጠልም ወደ መስክ በመውጣት ቀደም ሲል የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት አስመልክቶ ለመነሻነት የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመያዝ በሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን ለማስተርጎም የተመረጡ ግለሰቦችም የብሔረሰቡን ቋንቋ ወይም መኢኒተኛን እና አማርኛን በደንብ የሚያውቁ እንዲሁም ከዚህ በፊት በቋንቋና በሌሎች ዘርፎች በብሔረሰቡ ላይ በተካሄዱ ጥናቶች በአስተርጓሚነት ያገለገሉ ስለመሆናቸው ነው።

1.4.1.1 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ክፍል በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች እንዴት እንደተመረጡና የቃል መጠይቁ እንዴት እንደተተገበረ የተገለፀበት ነው። በአንድ ባህል ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ስለባህሉ ባላቸው እውቀት የሚለያዩበት ሁኔታ አለ። ስለዚህም መረጃ አቀባዮችን በተለያዩ መስፈርቶች መምረጥ ጠቃሚ ነው። በመሆኑም በቃለ መጠይቁ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። የተመረጡት መረጃ አቀባዮችም፡-

- የቤት እመቤቶች
- በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በባህልና በታሪክ እውቀታቸው የተመሰከረላቸው የሀገር ሽማግሌዎችና የእድሜ ባለፀጋዎች
- የየወረዳዎቹ ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊዎች
- ባለቃልቻዎች (ኔይሬ)
- የጎሳ መሪዎች(ኮመሩት) ናቸው።

በቃለመጠይቆች አማካኝነት የመረጃ አቀባዮች ግለታሪክ ስለብሔረሰቡ ዳራ ያላቸውን እውቀት እንዲነግሩኝ አድርጌያለሁ።ቃለመጠይቁ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች ከተሰበሰቡበት ዘዴዎች አንዱና ቀዳሚው ነው። ይህ ዘዴ በሁለት መልኩ ተግባራዊ ሆኗል። የመጀመሪያው መረጃ አቀባዮችን በማግኘት ጥያቄዎችን በመነሻነት በመጠየቅና ከአቀባዮቹ ምላሽ የሚፈልቁልኝን ሌሎች ጥያቄዎች በማከል መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌያለሁ።

በተጨማሪም በምልከታ ካየኋቸው ተግባራት በመነሳት በቃለ መጠይቁ የተግባራቱን ትርጉሞች ማህበረባህላዊ ተምሳሌቶች እንዲያስረዱኝ አድርጌያለሁ።

ቃለ መጠይቁን በማደርግበት ወቅት በዋናነት መቅረፅ ድምፅ የተገለገልኩ ሲሆን አስር ካሴቶችን ተጠቅሜያለሁ። ቦታውን በተመለከተ እንደ ተጠያቂዎቹ ማንነት በመኖሪያ ቤት ውስጥ፣ በመስሪያ ቤት (ወረዳ፣ ቀበሌ...) በለቅሶ ቤትና በቀበር ቦታዎች አካባቢ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለምሳሌ መንገድ ላይ፣ የቡና ስርዓት ላይ ወዘተ ተከናውኗል።

1.4.1.2 ምልከታ

አንድ የፎክሎር አጥኚ ምልከታን እንደ አንድ ዘዴ ተገልግሎ መረጃዎችን ይሰበስባል። እኔም ይህን ዘዴ በመገልገል መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ። የምልከታ ዘዴን በመጠቀም ከምልከታ በፊት በቃለ መጠይቅ ላገኘኋቸው ቃላዊ መረጃዎች ማረጋገጫነትም ተገልግየበታለሁ። በወቅቱም በፅሑፍ ማስታወሻ በመውሰድ በፎቶግራፍና በቪዲዮ በመቅረጽ በአውዱ የተፈጠሩ መስተጋብሮችን ለማጤን ተሞክሯል። በዚህም መሠረት በአዋኝና በክዋኔ ተሳታፊዎች መካከል ያለውን ተራክቦ ማለትም የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገጽታ መለዋወጥ፣ ወዘተ. ተጢነዋል። የክዋኞች የአለዋወን ስልት የመከወኛ ቁሶችና የክወና ቅደም ተከተሎች ሁሉ በምልከታው ወቅት የፅሁፍ ማስታወሻ ተይዟል።

1.4.1.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ይህ ዘዴ ጉዳዩ የሚመለከታቸውንና ከሁለት በላይ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን በአንድ ላይ አድርጌ ያወያየሁበትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚመለከት ነው። በቡድን የተሳተፉት የባህል አዋቂዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ባለቃልቻዎች ወይም "ኄራይ" የጎሳ መሪዎች ወይም "ኮሙሩቶች"፣ ወጣቶች እና የቤት እመቤቶች ናቸው።

በዚህ ዘዴ ስለብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ አሰፋፈር መረጃዎችን ለማግኘት የሚረዱ ጥያቄዎችን በማካተት እንዲሁም የልቅሶ ሥርዓቱን አከዋወን የተመለከቱ ጥያቄዎችን በመሰንዘር እንዲወያዩ በማድረግ መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

1.4.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በ1.4.1 በዝርዝር ለመግለፅ እንደተሞከረው ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ በገለላ ቀርበዋል። ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በተፈጥሯዊ መቼቶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ትንታኔዎች ለመስጠት ስለሚረዳ ነው።

ስለሆነም ጥናቱ በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ማህበረ ባህላዊ ክንውኖች የትና በማን እንዲሁም ለምን አላማ እንደሚተገበሩ በመግለፅና በመተንተን ቀርቧል።

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ የገንዘብ፣ የጉልበት እንዲሁም የጊዜን መስዋዕትነት የሚጠይቅ በመሆኑ አንዳች ጠቀሜታ እንዲኖረው ይጠበቃል። በመሆኑም "የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት አከዋወን" በሚል ርዕስ የተካሄደው ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- ✓ የመጀመሪያውና ዋነኛው የመኢኒት ብሔረሰብን ባህልና ያለውን ፎክሎራዊ ሀብት ማወቅ ለሚፈልግ አካል መረጃ በመሆን ያገለግላል።
- ✓ ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መገኛ እንደመሆኗ የተለያዩ ባህሎችና ወጎች ባለቤት የሆኑ ህዝቦች እናት ናት። ከእነዚህ ባህሎች መካከል የለቅሶ

ሥርዓት አከዋወን አንዱ ነው። ስለዚህ ይህን ፎክሎራዊ ሀብት ማጥናት በዘርፉ ለወደፊት ሰፊ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ እንደ ግብዓት በመሆን ያገለግላል።

- ✓ የብሔረሰቡ የባህል መገለጫ የሆነውን የለቅሶ ሥርዓት በፅሁፍ ለትውልድ በማስተላለፍ በኩልም ጠቀሜታ ይኖረዋል።
- ✓ የአንድን ማህበረሰብ ባህልና ወግ ማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከትና ፍላጎት ለመረዳት ከሚረዱ መንገዶች መካከል አንዱ ነው። ከዚህ አንፃር የተለያዩ እቅዶችንና ፖሊሲዎችን በምን መልኩ መቃኘትና መተግበር እንዳለባቸው ለፖሊሲ አውጭዎችና ለአስፈፃሚ አካላት ጠቀሜታ ይኖረዋል።
- ✓ ተጠኚው ብሔረሰብ ስለሞት ያለውን እሳቤና ስለለቅሶ ስርዓት አፈፃፀም ልምዱ ለማሳወቅ ይጠቅማል።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በቀዳሚነት ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ቢሆንም ከላይ የተዘረዘሩት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይጠበቃል።

1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የመኢኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ሂደትን በመግለፅና በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው። ለዚህም የለቅሶ ሥርዓቱን ከተለያዩ ማህበራዊ ደረጃች አንፃር በመመልከት ለክንውኖቹ ትርጓሜዎችን በማሳየት ቀርቧል። በአውዱ የሚታየውን የከዋኝና የታዳሚ ማንነትና ግንኙነት ይገልፃል። አውዱን መነሻ በማድረግ መቼና የት እንደሚከወን፣ በክዋኔው የሚታዩ ቁሳቁሶችን ትርጉም ያጠናል። ሆኖም በክዋኔው የሚገለፁ የተለያዩ የስነቃል ዘሮችን (ፉከራ፣ ቀረርቶ፣ መሳ የመሳሰሉትን) አወቃቀርና ይዘት በተመለከተ ዝርዝር ትንተና አያደርግም።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የተካሄደው ባህላዊ እምነት ወይም ኔሬይን በሚከተሉ መኢኒቶች ላይ ነው። ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት ባህላዊ እምነትነን ወይም ኔሬይን የሚከተሉት የብሔረሰቡ አባላት በዋነኛነትና በብዛት ከሰፈሩባቸው ሁለት ወረዳዎች ነው። በዚህም መኢኒት ጎልድና መኢኒት ሻሽ ከተሰኙት ወረዳዎች ከሚገኙ ቀበሌ ማህበራት ነዋሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

1.7 የመስክ ተሞክሮ

መስክ ከመውጣቴ በፊት የጥናቱ ትኩረት የሆነውን ማህበረሰብ እንዲሁም የጥናት ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። ይህንንም ከአብያተ መፃህፍት ለማግኘት ችያለሁ። ከዚህ በኋላ ለመስክ መረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን (ቴፕ፣ ካሜራ፣ ቪዲዮ የመሳሰሉትን) በማዘጋጀት እንዲሁም ለቃል መጠይቅ መነሻነት ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ወደ መስክ ወጣሁ።

ከአዲስ አበባ 555 ኪ.ሎ ሜትር ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሁለት ቀን ጉዞ በማድረግ የቤንች ማጂ ዞን ርዕሰ ከተማ የደረስኩት በ9/08/2007 ዓ.ም ከምሽቱ 12:30 ነበር። በነጋታው ጠዋት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በቀን 04/08/2003 ዓ.ም ለቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ (ቤ/ማ/ዞ/ባ/ማ/ቢ) እንዲሁም ለቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር (ቤ/ማ/ዞ/አ) የተፃፈልኝን ደብዳቤ ለጽህፈት ቤቶቹ አቀረብኩ።

የቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤትም በቀን 10/08/2003 ዓ.ም በግንባር ለመኢኒት ጎልድያና ለመኢኒት ሻሻ ወረዳ አስተዳደሮች በግልባጭ ለቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮና ለአጥኚዋ በፃፈው ደብዳቤ መነሻነት በጥናቱ ወረዳዎች ውስጥ ጥናቴን ልጀምር ችያለሁ።

ለጥናቱ ወደተመረጡት ሁለት ወረዳዎች ከመሄዴ በፊትም ከዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ በመኢኒት ሻሻ ወረዳ በወቅቱ በተከሰተው የሱርማና የመኢኒት ብሄረሰቦች ግጭት ያልተረጋጋ ሁኔታ የሚታይ በመሆኑ በቅድሚያ መኢኒት ጎልድያ ሄጀ ስራዬን መጀመር እንዳለብኝ መረጃ ተሰጥቶኛል።

በቀን11/08/2003 ዓ.ም.መኢኒት ጎልድያ ወደተሰኘው ወረዳ በመሄድ ከዞኑ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በማሳየት አላማዬን አስረድቻለሁ።

በዚሁ ወቅት በወረዳው (በመኢኒት ጎልድያ) አንድ በብሔረሰቡ የታወቁ የሀገር ሽማግሌ በቀን09/08/2003 ዓ.ም. ማረፋቸውን ቀበሌያቸውም ቢያጌሊች የሚሰኝ መሆኑን መረጃ ተሰጠኝ። እኔም ይህን ተፈጥሯዊ መቼት ለመጠቀም ሁኔታዎችን አመቻችቼ ወደተጠቀሰው ቀበሌ አመራሁ። የወረዳው ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ሃለፊ አንድ የካሜራ ባለሙያ እንዲሁም የብሔረሰቡ ተወላጅ የሆኑ እና በተለያዩ ብሔረሰቡን መሰረት ባደረጉ ጥናቶች ላይ

በአስተርጓሚነት ያገለገሉ አቶ ብርሃኑ ወርቁ የተሰኙ ግለሰብን በአስተርጓሚነት እንዲረዱኝ አድርግውልኛል።

በቀን13/08/2003 ዓ.ም ቢያገለኝ ቀበሌ በመሄድ በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ የመጓጓጓር ችግር ቢገጥመኝም በተጠቀሰው ቀን አይሱዙ (የደረቅ ጭነት ማመላለሻ) በመጠቀም ከወረዳው የካሜራ ባለሙያ ከአቶ ቢንያም ከበደ ጋር በመሆን ሄደናል።

በወቅቱ ይዘንብ የነበረው ዝናብ ለመኪና እጅግም የማይመቸውን ሰንሰለታማ መንገድ አስቸጋሪ አድርጎት ነበር። በዚህ ጊዜ ከመኪና እየወረድን በእግር የቻልነውን ያህል በመሄድ ደግሞም ደረቅ ያለና ለመኪና የማያስቸግር ቦታ ስንደርስ በመኪናው በመጠቀም ጨበራ ከተሰኘ ቀበሌ ማህበር ከጠዋቱ 3፡15 ደረስን። ከዚህ ቀበሌ ለቅሶ ቤቱ ወደሚገኝበት ቀበሌ ለመድረስ በእግር 1፡30 ያህል መንገዝ ስለነበረብን ምንም እረፍት ሳናደርግ ወደሚች ቤት አቀናን። በቦታውም ከደረስን በኋላ ከአቶ ብርሃኑ ወርቁ ጋር በመገናኘት ስለአጠቃላይ ሁኔታው ተነጋገርን።

በዚህም ከደረስኩበት ቅፅበት አንስቶ ያየኋቸውን ክንውኖች በፎቶ በቪዲዮና በፅሑፍ ማስታወሻ ለመያዝ ጥረት አድርጌአለሁ። በአውዱ ላይ ያገኘኋቸውን የሚችን ልጅ አቶ ኤርሚያስ አኛኝ፣ የሚች አጎትን አቶ ሴላ ቦላካሮን፣ እንዲሁም የሚች ሴት ልጅ የሆነችውን ሞይና አኛኝን ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸዋለሁ።[1] አሻም እያሉ መጨበጥና ሰላምታ መስጠት የተካኑት መኢኒቶች በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ ለቃለ መጠይቅና ለቪዲዮ ቀረፃው በሙሉ ፈቃደኝነት ተባብረውኛል። ለዚህ ደግሞ የወረዳው የባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ቢሮ ቀድሞ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ የላካቻው ግለሰብ ትልቅ ሚና ነበራቸው።

በዚሁ ቀን ከላይ ከጠቀስኳቸው ግለሰቦች በተጨማሪ የሚች አጎት የሆኑት አቶ ኢፋይ ቦሙ ቃለመጠይቅ አድርጌላቸዋለሁ። እንዲሁም በወቅቱ የተለያዩ የሀዘን መግለጫ ቁሶችን የያዙ እና አልባሳትን የለበሱ የለቅሶ ተሳታፊዎችን በፎቶና በቪዲዮ ለመቅረጽም ችያለሁ።

በቀን 19/08/2003 ዓ.ም ለጥናቱ ወደተመረጠው ሌላኛው ወረዳ ወይም መኢኒት ሻሻ በመሄድ ከዞኑ የተባረልኝን ደብዳቤ በማሳየት አላማዬን አስረድቻለሁ። ከወረዳው አስተዳዳሪና ከወረዳው ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ የተገኙ የየጽሁፍ መረጃዎችን (ያለታተሙ የስራ

[1] አሻም በመኢኒቶች ሰላም ማለት ነው።

ሪፖረቶች) ተመልክቼ ማስታወሻ ወስጃለሁ። እዚህ ወረዳ በደረስኩበት እለት (በ19/08/2003 ዓ.ም) ለወረዳው አስተዳዳሪ መረጃ አቀባዮችን እንዴት ማግኘት እንደምችል ጠይቄ ስለነበር አዋቂ ሰዎችን (የባህልና የታሪክ) ከየቀበሌ ማህበራቱ በመጥራት መረጃ እንዳገኝ ረድተውኛል።

በብሔረሰቡ የኪነት ቡድን አባል የሆኑት አቶ አበበ ለገሰ የጎሳ መሪ የሆኑ ግለሰብ ከቀበሌያቸው ወደ ወረዳው እንደሚጠሩልኝ ሆኖም የውሎ አበል ለሁለቱም መክፈል እንዳለብኝ በነገሩኝ መሠረት በዚህም ተስማምተን ጥሩ መረጃ እንዳገኝ ረድተውኛል።

ከዞኑ (ከቤንች ማጂ ዞን) በተሰጠኝ መረጃ መሰረትም የተለያዩ ሽማግሌዎችንና የጎሳ መሪዎችን ስምና አድራሻ በመጠቀም፤ከወረዳው ባህልና ታሪክ አዋቂ ናቸው የተባሉ ግለሰቦችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች የሚገኛቸውን መረጃዎች ትክክለኝነት ለማረጋገጥም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች ለተለያዩ ሰዎች በማቅረብ፤አውራ መረጃ አቀባዮችን በተለያዩ ሁኔታዎች በይዘት ተመሳሳይነት ያላቸውን በአጠያየቅ ቀድሜ ከጠየቅኩበት ስልት በተለየ መልኩ በማቅረብ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ጥረት አድርጌአለሁ።

ሌላው በመስክ ቆይታዬ ያከናወንኩት ስራ አማርኛ እንዲሁም መኢኒትኛ ቋንቋን በሚያውቁ ሰዎች መረጃዎችን ወደ አማርኛ ማስተርጎም ነው። የመረጃዎቹን ትክክለኛ ትርጉምነት በተቻለ መጠን ለማረጋገጥ በተለያዩ ሰዎች የትርጉም ስራው እንዲከናወን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። በቃለመጠይቁ ወቅት የተጠቀምኩባቸው ካሴቶችም ወደጽሁፍ የተቀየሩት በዚሁ ወቅት ነው።

1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ እርምጃዎች

በዚህ ጥናት በመስክ ስራ የሚጠበቁ እንደ የመጓጓጎና የማረፊያ እጦት ያሉ ችግሮች አጋጥመውኛል። ለነዚህ ችግሮች እንደ መፍትሔ በተለይም በመኢኒት ጎልድያ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሞተር ሳይክል መስጠት እንዲሁም በየቀበሌ ማህበራቱ የሚገኙ ግለሰቦችን ማረፊያ እንዲያመቻቹ በማድረጉ ችግሩ ተቀርፏል።

የመረጃ አቀባዮች በቀጠሮ አለመገኘት ፣ከተለያዩ ቀበሌ ማህበራት ነው የመጣነው በማለት የውሎ አበል እንዲሰጣቸው መፈለግ፣መረጃ አቀባዮችን በምጠይቅበት ወቅት "አሁንይሄ ምን

አይነት ጥያቄ ነው" በሚል አንዳንድ አቀባዮች ፈቃደኛ ያለመሆን ችግሮች አጋጥመውኛል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ባይቻልም በሚከተለው መልኩ ለማቃለል ተችሏል። መረጃ አቀባዮቹ የጠየቁትንም ያህል ባይሆን የምሳና የሻይ ወጭዎችን በመስጠት፣ ተደጋጋሚ ቀጠሮዎችን በማስያዝና በአስተርጓሚዎች በኩል አላማዬን እንዲረዱ በማድረግ እንዲሁም ይህን ባህል የማንነታቸው መሰረት በመሆኑ ስለባህላቸው መናገር፤ ባህላቸውን ማሳወቅ መቻል እንደሚገባ በማስረዳት ችግሮቹን ለማቃለል ተሞክሯል።

ሌላው በጥናቱ ያጋጠመኝ ችግር በተለይም ንድፈ ሀሳባዊ መነሻ ለመያዝ የጠቀመ መፃህፍትን ንባብ ሳደርግ የውጭ ሀገር ባህሪያንን ያታ ለመለየት መቸገር ነበር። ለዚህ እንደ መፍትሔ የወሰድኩት ግምታዊ አሰራርን ከመከተል ይልቅ የፀሐፊዎቹን ስም በመገኛ ቋንቋው በማስቀመጥ ብለዋል፣ ገልፀዋል፣ ወዘተ. የተሰኙ አገላለጾችን ተጠቅሜአለሁ። እኒህ አገላለጾች ሁለቱንም ያታ ይወክላሉ ብዬ በማሰብ።

በመጀመሪያ ያገኘሁትን ተፈጥሯዊ መቼት የቀረጽኩበት ቪዲዮ ወደ ሲዲ ለመገልበጥ አለመቻል ዋናው ያጋጠመኝ ችግር ነበር። ይህም የተከሰተው በካሜራ ችግር ምክንያት መሆኑን በዞኑ (ቤንች ማጂ ሚዛን ከተማ) ያሉ የሙያው ባለቤቶች ገልጸውልኛል። እንደመፍትሄም የተወሰደው እርምጃ በሚኢኒት ሻሻ ወረዳ በተከሰተ የአንድ አዛውንት ልቅሶ ሥርዓት ላይ የወረዳው ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ቀረጻ ያካሄድ ስለነበር እኔም አብሬ እንድቀርጽ ማስፈቀድ ነበር። በዚህም ተፈጥሯዊ መቼቱን በቪዲዮ ለመያዝ ችያለሁ።

2. ክለሳ ድርሳናት

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

2.1.1 የልቅሶ ስርዓትና የልቅሶ ስረዓት ክዋኔ

በዚህ ምዕራፍ ትወራዊ ዳራና የተካማጅ ጽሑፍ ክለሳ ተደርጓል። በዚህም የአንድን ህዝብ ታሪክ ለመመርመር እንዲሁ እምነትና ፍልስፍናውን ለማወቅ ልማዳዊ ተግባሩ ማስረጃዎች መሆናቸውን ለመጠቆም ተሞክሯል።

2.1.1.1 የልቅሶ ስርዓት

ለቅሶ በተለያየ ምክነያት የሚከሰት ቢሆንም የጥናቱ ትኩረት በሰው ሞት የሚከወነውን ለቅሶ በመሆኑ ሞት ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ማየት ያስፈልጋል። ሞት የስጋና የነፍስ መለያየትን የሚገለጽ ነው። በሌላ በኩል ከሰናይ (እነደ ባህሉና ሀይማኖቱ የሚለያበት ሁኔታ አለ) ምግብራት መለየት ሞት መሆኑ ይገለጻል ። ይህ አስተሳሰብ ሞት የስጋና የነፍስ መለየየትን ብቻ የሚመለከት አለመሆኑን ያሳያል። በዚህ ወቅት ሚከወን የህዘን መግለጫ ስረአት የለም ይልቁንም ማህበረሰቡ ሰናይ ብሎ ወዳመነው ምግባር (አፈንጋጩ) እንዲመለስ (ጸሎት፣ ምክር ፣ቅጣት ወዘተ.) እንደ ርምጃ የሚወሰዱ ይሆናሉ። እነዚህ እርምጃዎች የሚወሰዱት በህይወት ላለ ሰው ነው። ነፍሱ ከስጋው ለተለየች ግን የመጨረሻ ስንብት መሆኑን የሚገለጹ እንደ ባህሉና ወገ የተለያዩ ስርአቶች ይከወናሉ።

በዚህም ሰዎች በሚች መለየትን የተሰማቸውን ህዘን፣ ካላቸው ቅርበት አንፃር ሚች በህይወት ዘመኑ ያደረገላቸውን ውለታ በማስታወስ አልያም እሱ በመሞቱ ወደፊት ሊቀርባቸው የሚችለውን እርዳታና ድጋፍ በማሰብ ያለቅሳሉ።

አንድ ሰው ሲሞት እንደበቀለበት ማህበረሰብ ወግና ልማድ የተለያዩ ክንውኖችና ስርዓቶች ይደረጋሉ። በመሆኑም የልቅሶ ስርዓት አከዋወን ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ከባህል ባህል ይለያያል።

> *"በአንዱ የለቅሶ ስርዓት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል፣ ይዘለላል። በሌላው ደግሞ የቅርብ ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ፣ ፀጉራቸውን ይነጫሉ። በቀሪው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጠፈር የልቅሶ ክዋኔ ይደረጋል። በሆታና በድልቂያ የሚሰናበቱ አሉ።" (ዘሪሁን፤ 1992፡ 23)*

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የሚኢኔት ብሔረሰብም ከወጣትነት እድሜ የዘለለ ሰው ሲሞት በቃጭል በመታጀብና በመዝፈን ግብአተ መሬቱ እንደሚፈፀም አስፈላጊውን ክንውን ያካሄዳሉ።

በዚህም የተለያዩ የሀዘንና የልቅሶ ስርዓቶችን እንመለከታለን። የሟች አስከሬን እንደየ ማህበረሰቡ እምነትና ልማድ ወደ ቀብር ጉዞ ሲደረግ የሚታይ የልቅሶ ስርዓትና ክዋኔ፣ አውዱን የሚያመለክቱ ቁሳቁሶችንና ድርጊቶች በመመርመር ማህበረሰቡ በዚህ ክስተት ለእያንዳንዱ ክንውንና ድርጊት ያላቸውን ግምትና እምነት ወይም ክብር መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የልቅሶ ስርዓት የማህበረሰቡን ማንነት፣ እምነት እንዲሁም አመለካከት ለማወቅ ግብአት የሚሆኑ ጉዳዮችን ያካተተ ክዋኔ ነው። ስለሆነም የለቅሶ ስርዓት አከዋወንን ፎክሎራዊነት ማጥናት ማህበረሰቡን ለማወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚ ላይ የሚደረግ ርግዶ ወይምንም በሙሾ ስልት የሚካሄድ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ ምድብ እንደ Dorson፤ 1972:2 እና ፈቃደ፤ 1991፡10-16 ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk art) ውስጥ ነው። እኒህ እንቅስቃሴዎች ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም በተግባር ጊዜ አንዱ ያለአንዱ ሊካሄድ አይችልም።

ከልቅሶ ስርዓቱ ጋር አብረው ከሚታዩ ጉዳዮች መካከል ከሟች ነፍስ መውጣት ጋር ተያይዞ ከቀብር በኋላ የሚደረጉ ልማዳዊ ክንውኖች፡- በሬ፣ በግ ወይም ዶሮ ማረድ፣ የለቅሶ ቤት ድንኳን ወይም ጎጆ ሲፈረስ ቡና፣ ቆሎና የመሳሰሉትን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት፣ ሟችን እንደገደለው በሽታ ልቅሶ ማልቀስና አለማልቀስ የሚወሰንባቸው ጊዜያት ሁሉ አሉ። እኒህ ልማዳዊ ተግባራትና ክንውኖች ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነትና ልማድ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። እኒህ ክንውኖች የማህበረሰቡን እምነትና ፍልስፍና በአውዱ ያላቸውን ፋይዳና ትርጉም በማስተንተን ማጥናቱ ተገቢነት ያለው ይሆናል።

በልቅሶ ክንዋኔ ላይ ሰፊና ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ደግሞ ከርግዶ እንዲሁም ከሌሎች ትእይንቶች ጋር ተስተጋብሮ የሚቀርበው ሙሾ ወይንም የሀዘን መገለጫ ልቅሶና ነው። በአንዳንድ ቦታዎች እና ባህሎች በሀዘን ስርዓቱ ላይ እንደ ሟች ማህበራዊ ደረጃ የሚፎከርበት፣ የሚዘፈንበት እንዲሁም የሚለቀስበት ሁኔታ አለ። እነዚህን ጉዳዮች በአውዳቸው ማጥናቱ ተገቢነት አለው።

ስለዚህም የልቅሶ ስርዓት ክዋኔ ሲጠና አጠቃላይ ክዋኔው ድባቡን ህይወት እንዲኖረው በማስቻል ረገድ ትልቅ ሚና ስላለው ተያይዞ የሚጠና ነው። የለቅሶ ስርዓት ሲከወን ከአልቃሽ የሙሾ ግጥም በተጨማሪ ድባቡን ለማድመቅ የሚያገለግሉ አልባሳት እና ቁሶች እንዲሁም የአውዱ ተሳታፊዎች እንደ ማህበረሰቡ ባህላዊ ዳራ የሚወጡት ሚና ሁሉ ተያይዞ የሚታይና የሚጠና ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ያለሙሾ ርግዶ አይኖርም፣ ያለሀዘን የሀዘን ልብስ አይለበስም ቢለበስም ትርጉም ሊኖረው አይችልም። ቀንቆጥሮ አርባ ማውጣት እንዲሁም ከሀዘን የመንፃት ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ የቀብር ቦታና አቅጣጫ የመምረጥ ልማድ በልቅሶ ስርዓት ከሚታዩ ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዱ ነገር ከክንውኑ ጋር ያለውን ተያያዥነት ማጥናት የባህሉን ባለቤት ለማወቅ ጠቃሚና አስረጂ ነው።

በመሆኑም የፎክሎር ምርምር ምልዓት ይኖረው ዘንድ የአንዱ ድርጊት ለአንዱ ማጉያነት ያለው አስተዕኦ እና ፋይዳ እንዲሁ መጠናትና በተገቢው ሁኔታ መታየት አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ማህበረሰቡን አጠናን አወቅን ያለውን ባህልና አመለካከት ተረዳን ማለት ዘበት ከመሆን አያመልጥም።

2.1.1.2 ክዋኔ

ክዋኔ ለለቅሶ ሥርዓት ህልውና መሠረታዊ ከሆኑ ነጥቦች ውስጥ የመጀመሪያው ነው።

> *አንዲት አልቃሽ በአንድ ለቅሶ የምታደርገውን ግጥም ሰብስብ በዕሁፍ ማስፈርና ለአንባቢ ማስተላለፍ ይቻላል ዛሬ። ነገር ግን ይህ ሰብስብ የሙሾውን አከዋወን አይጨምርም። አልቃሽ ከግጥሙ ውጭ የሆነውን የክዋኔዋ ማጎልበቻ አድርጋ የምትገለገልባቸውን ጠቅላላ ድባብንም አይጨምርም። የሚያነበውን ሰው ስሜት ምንም ያህል አይነካም፤ ... አካሉ ከሆነው ማህበራዊ እውነታና ክዋኔው ተለይታለና። (ፈቃደ፣ 1984:1-3።*

በመሆኑም አንድን የፎክሎር ዘር በዕሁፍ መሰነድ ቢቻልም ህልውና እንዲኖረውና ይህንንም ለማስጠበቅ ዋናውና አስፈላጊው ጉዳይ የክዋኔ መኖር ነው። ስለሆነም ክዋኔ መሠረታዊና የማይቀር ጉዳይ ነው። በለቅሶ ክንውኑ ወቅት የሀዘን መገለጫ የሆኑ ልብሶች በመለበስ፤ የሀዘን ዘፈን ወይም ሙሾ ይካሄዳል። ክንውኑን ሊያጎሉ የሚችሉ የሚች አልባሳት፣ በህይወት ዘመኑ የተጠቀመባቸው ቁሶች (በተለይም የሚችን ማህበራዊ ደረጃ የሚያመለክቱ) እንዲሁ የሚችን ስራ የሚያስታውሱ (የሚዘክሩ) ፉከራዎች ሁሉ ይካተታሉ። እነኝህ ግብዓቶች ከሌሉ ክዋኔ የሚታይበት ወይም የሚገለዕበት መንገድ የለም። እነዚህ

ማኅልበቻዎች ለለቅሶ ስርዓት ክዋኔው ያላቸው ጠቀሜታ ለጉዳዩ ህይወት መስጠት በመሆኑ ክዋኔ ከሌለ የሚፈለገው መልዕክት ከነሙሉ ስሜቱ ተደራሲ ለማድግ የማይቻል ነው። ምክንያቱም አንድ የፎክሎር ዘርፍ በተለይም ደግሞ የለቅሶ ስርዓት ለስሜት ቅርብ ሆኖ የሚታይና የሚያሳትፍ የሚሆነው ሲከወን ብቻ በመሆኑ ነው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ክዋኔ በተለይ እንደ ልቅሶ ላሉት ማህበራዊ አጋጣሚዎች የጀርባ አጥንት ነው። ክዋኔ እንደዚህ አስፈላጊ ከሆነ እንዴት ሲከወን ወይም በምንመልከው ሊካሄድ ይችላል የሚለውን "Frequently, performances have clear setting and recognizable structures that indicate to participants that indicate to participants that performance is taking place" (Martha and Martine 2005:128) በማለት ያስረዳሉ።

ጥቅሱ ክዋኔ የራሱ የሆነ መዋቅርና መቼት ሊኖሩት እንደሚገባ ያስረዳል። እነዚህ መሰረቶች መኖራቸው ደግሞ ለታዳሚው ፍንጭ በመስጠት በኩል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸውንም እንረዳለን። ይህ የሆነበት ምክንያት ክዋኔ የአንድ ድርጊት ወይም ክንውን (የልቅሶ፣ የሰርግ... የመሳሰሉት) መገለጫ በመሆኑ ነው። ክዋኔ በልቅሶ ስርዓት ላይ የሚፈጥረውን ስሜት ፈቃደ ሲገልፅ፡-

> *ጠቅላላ ድባቡ፣ የመሶ አውራጅ የድምፅ ማማር፣ የዜማ አሰባበር፣ አወራረዷ፣ በእጇ፣ በድምፅና በፊቷ የምታደርጋቸውን ድርጊቶች፣ ከተቀባዮች ጋር የምታደርገው የዜማና የግጥም መለዋወጡ፣ የደረት መምታት፣ የዋይ ዋይ፣ በሀዘንተኛው አእምሮ ውስጥ ስለሟች የተቀረጹ ሀሳቦችና ሀዘንተኛ በሀዘንተኛ ላይ ያለው ተፅዕኖ (የአንዱ ማልቀስ ለሌላው ሰበብ ሊሆን ይችላልና) ወዘተ. እነዚህ ሁሉ በአንድ ሀብር ሲገኙ ነው ሰውን የሚያባቡት፣ የሚያሳዝኑትና የሚያስለቅሱት። (ፈቃደ፣ 1970:2)*

(Marthal and Martine፣ 2005:128-129) በክዋኔ ወቅት ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ የክዋኔ ማሄጃ ወይም ክዋኔው እንዲከናወን መሰረት የሆኑ ነጥቦችን በመዘርዘር እጅግ የተቆራኘ ገለጻና እንዳላቸው አስረድተዋል። እነዚህ የክዋኔ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች ደግሞ የመጀመሪያው ክዋኔው የሚከወንበት አጋጣሚ (occasion)፣ በክዋኔው የሚሳተፉት ወይም ታዳሚዎች (audience)፣ ከዋኝ (performer)፣ ክዋኔውን አመላካች ወይም ጠቋሚ (markers) የመከወኛ መሳሪያዎች (ቁሶች) እና አውድ (context) ወዘተ. መሆናቸውን ያመለክታሉ። በተመሳሳይ ቦውማን (Bauman) ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ቁርኝት *The term performance 'has been used to convey a dual sense of artistic action*

the doing of folklore an artistic event the performance situation, involving performer, art form, audience, and setting (Bauman, 1977:4) በማለት ይገልፁታል።

በመሆኑም የልቅሶ ክዋኔ በተሳታፊዎች እንቅስቃሴ፣ በመከወኛ ቁሶች ግብዓትነት እንዲሁም በከዋኝ ተግባር የሚካሄድ ነው። አንዱ ለአንዱ መሰረትና እርስ በእርስ በመስተጋብር የሚካሄድ ነው።

2.1.1.3 የመከወኛ ምክንያት

አንድ የፎክሎር ዘርፍ ለመከወን የተወሰነ ቦታና ጊዜ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የመከወኛ ምክንያት ሊኖረው ይገባል። የለቅሶ ስርዓት እንዲከወን የሰው መሞት በምክንያትነት መኖር አለበት። "Performances are not produced at random times the occasions for performances are limited and can be observed in the field" (Jan Vansina, 1985:39) በጥቅሱ እንደተመለከተው አንድ ክዋኔ በዘፈቀደ አይከወንም ይልቁንም አንድ የተወሰነ የመከወኛ ምክንያት እና ወቅት ያስፈልገዋል እንጂ። በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅትም እንደ ማህበር ባህላዊ ዳራው ቢለያይም መሶ እንዲወርድ፣ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ በክብት በደም መታጠብ፣ በቃጭል ታጅቦ የሀዘን ዘፈን መገዘፉን እንዲቻል የሰው መሞት በምክንያትነት መቅረብ አለበት።

የለቅሶ ስርዓት አከዋወን እንደ ሌሎች (ዘፈን፣ ጭፈራ) ሁሉ እንዲከወን የራሱ የሆነ ምክንያት ያስፈልገዋል። ይህ ደግሞ አንድ የፎክሎር ቅርፅ የሚከወንበት የሚዜምበት የሚነገርበትና የሚተረክበት የተወሰነ የመከወኛ ምክንያት (occasion) ያስፈልገዋል።

2.1.1.4 የክዋኔ ተሳታፊ

ለፎክሎር በተለይም ለለቅሶ ስርዓት የተሳታፊዎች መኖር አስፈላጊ ነው። አስፈላጊ ብቻም ሳይሆን ግዴታ ነው። ከዋኝ ያለታዳሚ ወይም ያለ ተሳታፊ የለቅሶ ስርዓትም ያለክዋኔ ህልውና የላቸውም። ተሳታፊንና ከዋኔን አስመልክተው Ben-Amos ያስፈሩትን እንመልከት"Both the performers and the audience have to be in the same situation and be part of the same performance 'group'." (Ben-Amos, 1982:13)

የለቅሶ ስርዓት እንዲከወን ከከዋኝ በተጨማሪ ተሳታፊዎች መገኘት አለባቸው። በዚህ ጊዜ ተሳታፊዎች ፍጠ ተመልካች ሳይሆኑ ተሳታፊና ለድባቡ ተስማሚ የሚሆነውን አልባሳትና የሀዘን መግለጫ ሚና የሚወጡ ናቸው። በመሆኑም ከዋኝና ተሳታፊ በአውዱ እጅግ የተቆራኘ ሚና አላቸው። ለዚህም ነው "... the audience is really part of the performance it self," (Finnegan, 1977:216) በማለት የገለፁት።

ከክዋኔ ተሳታፊ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነጥብ የተሳታፊዎች የእድሜ ክልል እንዲሁም የፆታ ሁኔታ በተጨማሪም የባህል ሁኔታ ናቸው። የለቅሶ ስርዓት በሚከወንበት ወቅት ህፃናት ታዳሚ የሚሆኑበትና የማይሆኑበት ባህል መኖሩንም ልብ ይሏል። ለጀግና ሟች የሚገኙ ተሳታፊዎችና ክንውናቸው ለ"ተራ ሰው" ከሚያደረጉት ክንውን ይለያል።

ታዳሚ እንደ ፊኔጋን(Finnegan, 1977:216) አገላለፅ ክዋኔን ለመመልከት ብቻ ሳይሆን በተለያየ ዘዴ የከዋኙን ሞራል እያነቃቃ በክዋኔውም እየተሳተፉ ስርዓቱን የሚያደምቅ መሆኑን እንረዳለን። ከዋኝ በሚከውነው ተግባር በመታገዝ የሚወጡት አልያም እንዲፈፀሙ የሚሰጣቸው ተግባር አለ። በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የመሾ አውራጅን ሚና ተክትሎ የተሳታፊ ሚና ይቀጥላል። ይህ ደግሞ በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በዜማ (በድምጽ) እና በመሳሰሉት ይገለፃል። ይህ መስተጋብር ካልታየ ማርታና ማርቲን (Martha and Martine) እንዳሉት "... it my not be a successful expression of the performer's ideas." (Martha and Martine, 2005:129) ከዋኝ ሊያስተላልፍ የፈለገው አንዳች ጉዳይ ያለተሳታፊው ግብረ መልስ የትም አይደርስም። በመሆኑም ተሳታፊ ፍጠ ሳይሆን ከከዋኝ ጋር ሚና በመለዋወጥ ክዋኔውን ህልው የማድረግ ተግባር መወጣት ይጠበቅበታል።

አብዛኞቹ የፎክሎር ዘሮች ታዳሚ የሚሹ ናቸው። እንደየ ባህሪያቸውና አይነታቸው የታዳሚዎቹ ሚና እና አይነት የተለያየ ነው። የለቅሶ ስርዓት ደግሞ በውስጡ የተለያየ ፎክሎራዊ ገፅታዎችን የያዘ ነው። ይህ ማህበራዊ አጋጣሚ ቡድናዊ እንደመሆኑ የከዋኝን እና የታዳሚን መስተጋብር በእጅጉ የሚሻ ነው። የከዋኝን ድርጊትና እንቅስቃሴ በማድመቅና በመከተል መሳተፍ ከታዳሚው የሚጠበቅ ነው። ስለዚህም ታዳሚው በተለያየ መንገድ በክዋኔው ተካፋይ ይሆናል።

በተጠኘው ማህበረሰብ የልቅሶ ስርዓት አከዋወን እንደሟች ማህበራዊ ደረጃ (ህፃን፣ ወጣት እንዲሁም ጎልማሳና አዛውንት ብሎም ጀግናና ሀብታም) የከዋኝ ተግባር እና የተሳታፊ ሚና

በጥምረት ይካሄዳል። ለህፃናት ሞት የአልቃሽን ክዋኔ ተከትሎ ማልቀስ ለቀሩት የእድሜ ክልል ሚኞች ደግሞ በተለያዩ ቁሳቁሶች ድምፅ ታጅቦ የለቅሶ ዜማ (የሀዘን ዘፈን) የምታወርደውን አልያም የሚያወርደውን ተከትሎ መዝፈን፣ ለሀዘነተኞች ምግብ ማዘጋጀት፣ የቀብር ቦታማዘጋጀት ወዘተ. የክዋኝና የታዳሚ ተግባር ነው። በዚህ ጊዜ የክዋኝን ሀሳብ ታዳሚ በመረዳቱ ብሎም በመሳተፍ ክዋኔው መሉዕ ይሆናል።

2.1.1.5 ዓውድ

አውድ አንድ ሁነት የሚከወንበት ቦታን፣ ጊዜንና አጠቃላይ ድባብን የሚመለከት ነው። "... context in which folklore exists or is performed" (Goldstein, 1964:80) በማለት ይገልፀታል። ማርታና ማርቲን ደግሞ "The physical settings and social situations in which members of folk groups share for wore, as well as the relationships among audience members and performers: make up the context of the performance. .... Context refers to anything and everything tat surrounds a text and performance" (Martha and Martin, 2005:137) በመሆኑም አውድ የክዋኔውን ቦታ፣ ጊዜን፣ የተለያዩ ባህላዊና እምነታዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው። የለቅሶ ስርዓት እንደየ ባህሉና እንደ ማህበረሰቡ እምነት በተለያዩ ማህበራዊ ክንውኖች ይታጀባል። ደረት መድቃትና ፊት መንጨት በአንዱ ማህበረሰብ የከፍተኛ ሀዘን መገለጫ ናቸው። ጥቁር አልያም ነጭ ልብስ መልበስ፣ ፀጉር መላጨት፣ አንገት ላይ ነጭ ክር ማሰር እና የመሳሰሉት ሁሉ የሀዘነ መግለጫዎች በአውዱ የሚከናወኑና አውዱን የሚያጎሉ ድርጊቶች ናቸው።

አውድ ክዋኔው የሚከወንበት ቦታ እና ጊዜ የተለያዩ ክስተቶች ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ በፎክሎር ጥናት አውዱ በአጠቃላይ መጠናት እንዳለበት "In studying a certain folk text we can not simply lift it from the context and begin to understand its importance to a particular group accurately. It must be seen within a larger context as part of a cultural system. (Martha and Martin, 2005:137) በማለት ያሳስባሉ። በተጨማሪም Finnegan (1970:12), Ben Amos (1982:27) እና Bauman (1983:362-368) የትኛውም የፎክሎር ምሳሌ ጭብጥ ለመተንተን የክዋኔውን አውድ በጥንቃቄ መመርመር ተገቢነት ያለው ተግባር መሆኑን ያስገነዝባሉ። በዚሁ መሠረት ጭብጥን ከማጉላት አንፃር፣ ክንዋኔው የተዘጋጀበት ቦታና ጊዜ፣ በጉዳዩ ወይም በልቅሶ

ስርዓቱ የሚሳተፉ ሰዎችና የሚኖራቸው ሚና፣ የክዋኞች ጥበባዊ አቀራረብ፣ የታዳሚዎች አቀባበልና ሌሎች የክዋኔ መሠረቶች ግምት ውስጥ ገብተው መጠናት አለባቸው። ይህን ሀሳብ አስመልክቶ Bauman (1977:11፤1983:3) እና (Finne 1984:65) መረጃዎችን ከመስክ በመሰብሰብም ሆነ በመተንተን ረገድ የልቅሶ ክዋኔውን አውድ ማጤን እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ።

2.1.1.5.1 ተጨባጭ አውድ

ይህ የአውድ አይነት ክዋኔው የሚካሄድበት ቦታን፣ ጊዜን እንዲሁም ድባቡን የሚመለከት ነው።

> *The physical elements of the performance itself are also part of the context. These include gestures, changes in tone of voice, shifts in pitch, and rhythm. Frequently, we can record performances on tape and film, but sometimes we are unable to capture performances on tape, particularly those that are not preset in time or place as a performance, or are not recreated for the purposes of "collection". In these cases, it is important to observe carefully and take accurate notes on the physical elements in order to describe in writing the details of a performance as accurately as possible. (Marth and Martin, 2005*:138).

ተጨባጭ የሆኑ ነገሮች በራሳቸው የአውድ አካል ናቸው። በመሆኑም ተጨባጭ አውድ በቴፕ አልያም በፎቶ ለማነሳት የማይችሉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እና አንዳንድ ሁነቶችን ለመግለፅ ያገለግላል።

2.1.1.5.2 ማህበራዊ አውድ

ማህበራዊ አውድ በክዋኔው ወቅት ያለውን ነገር ወይም መዋቅር የሚያመለክት ነው። "... social context in which folklore actually functions in a society." (Goldstein, 1964:80) በማት በማህበራዊ አውድ አንድ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ በተጨባጭ የሚተገበርበትን ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን ይገልፃሉ። ማርታና ማርቲን ደግሞ *"Brood elements of the performance context include those things that relate to the group, community, and culture with in which the communicative expression takes place. (Martha and Martin, 2005:139)*. በማለት ገልፀውታል።

ይህ የአውድ አይነት በክዋኔው ወቅትና ቦታ የሚገኙ ነገሮችን እና ከሱሩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን፣ ከባህሉና ከማህበረሰቡ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ጉዳዮች የሚመለከት መሆኑን ያስረዳሉ። በተጨማሪም በክዋኔው ወቅት የታዳሚዎች ሁኔታ (የፆታ፣ የመደብ፣ የሀይማኖት፣ የጎሳ እና የባህል የመሳሰሉት) ማህበራዊ አውድ እንደሚባሉ፤ እኒህ ጉዳዮች ክዋኔውን የሚወስኑ መሆናቸውንም አያይዘው ያመለክታሉ። *"... ethnic background, religious affiliations, occupation, regional connections, culture... all these are social aspects of performers, audiences and setting that influence the events taking place during performance. (Martha and Martin, 2005:139)*

ስለዚህ በለቅሶ ስርዓት አከዋወን ወቅት የተሳታፊው ሁኔታ በእድሜ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሙያ፣ በሀይማኖት በመሳሰሉት ጉዳዮች የተለያየ መሆኑን በማጤንና በመገንዘብ እኒህን ጉዳዮች መመርመር ተገቢነት አለው።

2.1.1.6 የክዋኔ አመላካች

ይህ ነጥብ አንድ የፎክሎር ዘውግ ለመከወኑ ወይም እየተከናወነ ለመሆኑ ግልፅ የሆነ ጥቆማ የሚሰጥ ነው። ክዋኔ አመላቾች በአንድ ሁነት ወይም ክንውን ላይ የመግለጥ ተግባር አላቸው። በዚህም አንድ ክንውን እየተካሄደ መሆኑን የሚያመለክቱ ከመሆናቸው በላይ የክዋኔውን ምንነትና አላማም የመጠቆም ፋይዳ አላቸው።

> *... people communicate within specific situations and settings, and these communications are "performed" for certain reasons and in certain ways that have meaning to the members of folk groups and communities. Performances are usually set off from everyday experience by certain markers" words or gestures, which signal when a performance is about to take place and when it ends. (Martha and Martin, 2005:133)*

ከጥቅሱ መመልከት እንደሚቻለው ማህበረሰቡ በክዋኔ አመላካቾች አስረጂነት ስለክዋኔው አይነት፣ ቦታ እንዲሁም መቼ ተጀምሮ እንዴት ተካሄዶ መቼ የሚያበቃ መሆኑን ይረዳል። በዚህም ክዋኔው ለምንና እንዴት እንደሚከወን ፍንጭ በመስጠት በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው።

በተጠኚው ማህበረሰብ በለቅሶ ስርዓት ላይ ለቅሶ ብቻ ሳይሆን እንደ ሚች የእድሜ ደረጃ የሀዘን መግለጫ ዘፈን ይዘፈናል። እንዲሁም ሀዘንተኞች በድንጋይ ተቀጥቅጦ የተገደለን በሬ ስጋ ከተመገቡ በኋላ ነው የሀዘን መግለጫ ዘፈኑን የሚከውኑት። ለባዕላት ለሰርግና ለመሳሰሉት አጋጣሚዎች ደግሞ በሬው ወይም ኮርማው በስለት ይታረዳል እንጂ ተቀጥቅጦ አይገደልም። ይህን ልዩነት ስንመለከት ከድርጊቶቹ ትርጓሜ መለያየት በተጨማሪ ሰርጉ እና ለቅሶው ወይም ሌላ ክንውን የሚከወኑበት የየራሳቸው የሆነ ማህበራዊና ባህላዊ አካሄድ ያላቸው መሆኑን እንረዳለን። እነዚህ አመላካቾች አማካኝነትም ማህበረሰቡ የሚከወነውን ነገር በማወቅ አውዱ የሚፈቅደውን ሁነት ለማድረግ ያስችሉታል። ይህንን አስመልክተው ማርታና ማርቲን (Martha and Martine) የሚከተለውን አስፍረዋል። *Performances have clear setting are recognizable structures that indicate to participants that the performance is taking place. Many rituals... begin at a predetermined time and place, and an announcement or other signal opens and closes the performance. (Martha and Martine, 2005:128)*

የክዋኔ አመላካቾች አንድ የፎክሎር ዘር እየተከወነ መሆኑን ከማሳወቅ በተጨማሪ የታዳሚውና የተሳትፊ ተግባር ምን ሊሆን እንደሚችል የመጠቆም ተግባር አላቸው። በመሆኑም ክዋኝና ታዳሚ ሚና የመለዋወጥ ተግባር እንዲወጡም የሚያስችሉ ናቸው።

የክዋኔ አመላካቾች አንድም በታዳሚና በክዋኝ እንቅስቃሴ ሊገለፅ ይችላል። በተጨማሪም ለአውዱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችም የክዋኔ አመላካች ሆነው ይገኛሉ። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የሀዘን ዘፈን ሲከወን የሚች እድሜ ከወጣትነት የዘለለ መሆኑን (በቃጭል ታጅቦ ነው የሀዘን ዘፈኑ የሚከወነው) ይታወቃል። በመሆኑም በለቅሶ ስርዓት አከዋወን ወቅት እንደማህበረ ባህላዊ ዳራው ይሆነኝ ብሎ የሚገለገልባቸውን አመላካቾች ትኩረት ሰጥቶ ማጥናቱ ተገቢ ነው። *ማረታ እና ማርቲን(Martha and Martine)* ክዋኔውን ለመመርመር የክዋኔ አመላካቾች ሚና ትልቅ መሆኑን ያስረዳሉ። ምክንያቱም የክዋኔ አመላካቾች ለተሳታፊ በክንውኑ በንቃት እንዲሳተፍ፣ እረፍት እንዲያደርጉና ከአንዱ ድርጊት ወደ ሌላ እንዲሸጋገሩ በማስቻል በኩልም ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ ነው።

> *"... Markers generally signal for performers and listeners that it is time to pay attention, guide them through the performance and let them known when it is time to relax, or perhaps comment on the performance they have just seen (Martha and Martine, 2005:142).*

2.1.1.7 ከዋኝ

ከዋኝ በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚኙ በህይወት ዘመኑ ስለፈፃማቸው ተግባራት፣ ስለዘመድ ወዳጆች ሀዘንና ስለመሳሰሉት በማንሳት ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን እንዲገልፁ የማድረግ ተግባር ይወጣል።

በልቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት ከዋኝ ስለሚኙ ስብዕና በማንሳት ስነቃሉችን በመሸ ስልት፣ በቀረርቶ እና በፉከራ በመሳሰሉት ይከውናሉ። ይህ ደግሞ እንደ ፊኔጋ /Finnegan) አገላለፅ የለቅሶ ስነቃል ያለከዋኝ ሊተላለፍ የሚችልበት መንገድ የለም።ምክነያቱም "oral literature by definition is dependent on a performer who formulates it in words on specific occasion. There is no other way in which it can be realized as a literary product". (Finnegan; 1970:2) ስለዚህ ክዋኔ እውን እንዲሆን የከዋኝ መኖርና መከወን ግድ ነው።

ጥናቱ በሚያተኩርበት ማህበረሰብ አዛውንት ሲሞት የሀዘን ስነ-ስርዓቱን በሀዘን ዘፈኖቹ የሚያደምቁ ከዋኞች አሉ። እነዚህ ከዋኞች ለሟች ያለን ክብርና ውዳሴ በማነሳሳት የሀዘን ዘፈን ያቀርባሉ። እንዲሁም ህፃናት ሲሞቱ ለቅሶ በመምራት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

2.1.1.8 የመከወኛ ቁሶች

ፎክሎር የሚለው ቃል ፎክ እና ሎር በማለት በሁለት ተከፍሎ የተበየነ ነው። ፎክ አንድ የጋራ የሆነ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል። ሎር ደግሞ የጋራ ሆኖ የሚያሰባስባቸው ጉዳይ ነው። ጉዳዩ ግን ምንም ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የሚያገናኛቸው ወይም የሚያሰባስባቸው ጉዳይ አልተወሰነም። ወይም ይህ ብቻ ነው አልተባለም። በዚህ ስራም የጋራ ጉዳይ ወይም የመሰባሰቢያ ምክንያት የሰው ሞት ሀዘን ነው። የቡድን አባላት በለቅሶ ክንውናቸው ወቅት የሚገለገሉባቸው የተለያዩ ቁሶች አሏቸው። ከዋኙ ተግባሩን ለመወጣት የሚያገለግሉት የተለያዩ ቁሶች ሊጠቀም ታዳሚዎችም እንደዚሁ ለተግባራቸው ማጉያ ይሆኑ ዘንድ የተለያዩ ቁሶችን ይጠቀማሉ። ስለዚህ በክዋኔ ወቅት ከሚጠኑ ጉዳዮች መካከል በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደቡት የመከወኛ ቁሶች ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህ ቁሶች እንደማንኛውም እቃ የምናጠናቸው ብቻ ሳይሆኑ በዋነኛነት ከቁስነታቸው ባሻገር በአውዱ ያላቸውን አንድምታ በጥልቀት ማየት ይገባል።

በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ሀብቶች ሲጠኑ የመከወኛ ቁሶች፣ መጠናት አለባቸው ካልሆነ ግን እንደ Glassie አገላለፅ "we miss more than most people in recent times and every one in the most ancient days. When we restrict research to verbal documents we miss the word less experience of all people, rich or poor, near or far." (Glassie፤ 1999:44)። ጥቅሱ ጥናትን በቃላዊ ሀብት ላይ ብቻ መወሰን ቃል አልባ ልማድን እንድንዘነጋ የሚያደርግ መሆኑን ይጠቁመናል። በመሆኑም በአንድ ክንውን ላይ የሚያገለግልን መከወኛ ቁስ ከነተምሳሌትነቱ በማጥናት ለሁነቶች የተሟላ ፍቺና ትርጉም ለማግኘት መጣር ተገቢ ነው።

በለቅሶ ስርዓት አከዋወን ላይ ስርዓቱን ከማድመቂያነት በተጨማሪ አንዳች ባህላዊ ወይም እምነታዊ ፋይዳ እንዲያመጡ ቁሳዊ ባህሎች (የሀዘን መግለጫ ልብስ፣ ፈትል አንገት ላይ ማሰር፣ የአስከሬን ሳጥን ለብሶት የነበረውን ጋቢ (ነጠላ) እሚች በር ላይ ማንጠልጠል (በተለይ በሰሜን ሸዋ) ማስተዋላችን በዚህ ዘርፍ የድርጊቶቹና የቁሶቹ አንድምታና ትርጓሜ መጠናት እንዳለበት ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

2.2 የቀብር ስነስርዓት

ቀብር ሰው ከሞተ በኋላ አስፈላጊው ክንውን ተካሂዶ እንደ እምነትና ባህሉ ግብአተ መሬቱ የሚፈፀምበት ስነስርዓትን ይመለከታል።

ኪዳነወልድ ክፍሌ ቀብር ለሚለው ቃል የሰጡት መዝገበ ቃላዊ ፍች፡- "ቀበር፤ ቀበራ፤ አቀባበር፤ ግንዘት፤ አገናነዝ፤ የሬሳ ህግ፤ ሽቱ መቀባት፣ ማጠን፤ ማጤስ፤ መፍታት፣ ማልቀስ፣ ርግዶ መ·ሸ፤ የመሳሰለው ኹላ" (ኪዳነወልድ፤ 1948፡781) የሚል ነው።

ከላይ ለማየት እንደሚቻለው በቀብር ስርዓት አፈፃፀም ላይ እንደማህበረሰቡ ባህላዊ ዳራ ቢለያይም የተለያዩ (ልማዳዊ፣ ሃይማኖታዊ ወዘተ.) ስርዓቶች ይስተዋላሉ። ይህም እንደ ሚች ማህበራዊ ደረጃ፣ የዕድሜ ሁኔታ እና ባህላዊ ስልጣን የሚወሰንበት አጋጣሚ አለ Linton, 1964:113)።

ቀብር መዕሀፍ ቅዱሳዊ መሠረትም አለው። “ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና” (ኦሪት ዘፍጥረት 3፡19) ሰው ሲኖር የላቡን የወዙን ይበላል፤ በመጨረሻም ከአለም ይለያል በዚህ ጊዜ ወደ አፈር ይገባል ። ይቀበራል። “እግዚአብሔር ተናግሯልና። እንግዲህ ተነስተሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ እግርሽም ወደ ከተማ በገባ ጊዜ ልጁ ይሞታል። እስራኤልም ሁሉ ያለቅሱለታል፤ ይቀብሩታልም።” (መዕሐፈ ነገስት 13፡9) የሚለው ጥቅስ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው ።

ሞት ሰው ከበጎ ምግባር በመራቁ የመጣ ቅጣት ቢሆንም በስርአተ ቀብር መፈጸም ደግሞ ለመልካም ምግባር ባለቤቶች የተሰጠ፤ የተፈቀደ መሆኑን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል። እግዚአብሔር አምላክ ለኢዮርብዓም ስልጣን ሲሰጠው ፈፅሞ ልቡን ማስገዛት ባለመቻሉ ተቀጣ በዚህም የተነሳ ልጁን በሞት ተነጠቀ። ነገር ግን “... በስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ በኢዮርብዓም ቤት በዚህ ልጅ መልካም ነገር ተገኝቶበታልና ከኢዮርብዓም እርሱ ብቻ ይቀበራል። (መዕሐፍ ነገስት 14፡9) የሚለውን የመዕሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ስንመለከት ሞት የተከለከለን ከመስራት፤ ትዕዛዝን ካለመፈፀም የመጣ ቅጣት ቢሆንም ቀብር ግን ለመልካም ምግባር ባለቤቶች የሚሰጥ (የተፈቀደ) መሆኑን እንረዳለን። (ኤርምያስ 22፡19፣ መፃህፍ ነገስት ካላአይ 9፡10፣ 25-26፤ 33-37 እና ኤርምያስ 22፡19 ተመልከት)።

በሌላ በኩል ስርዓተ ቀብር የሚፈፀመው ለሟች ያለን ክብር እና እንክብካቤ መግለጫ እንዲሁም ከሞት በኋላ አለ ተብሎ በአንዳንድ ባህሎች ለሚታመነው እንደቅድመ ዝግጅት የሚተገበር ነው።

በስርዓተ ቀብር ክንውን ወቅት እና ከቀብር ቀድሞ እንዲሁም በድህረ ቀብር የተለያዩ ድርጊቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ ክንውኖች በስርዓተ ቀብር፣ ድህረ ቀብርና ወቅተ ቀብር የሚካሄዱ ክንውኖች በማለት እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል።

2.2.1 ቅድመ ቀብር ክንውኖች

ሟች ነፍሱ ከመውጣቱ በፊት ሀብት ንብረቱን በእምነት አባቶች ፊት እንዲናዘዝ ይደረጋል። ይህ ለሟች የበሽታ ጥንካሬና እድሜ ደረጃ ሊተገበርም ላይተገበርም ይችላል። ሌላው በቅድመ ቀብር ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል የተለያዩ ስርዓቶች ይገኛሉ። እነሱም ግንዛት አንዱ ነው። ግንዛት በደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላት መሠረት አስከሬን ማጠብ እንዲሁም ሽቶ መቀባት ማጠን የመሳሰሉትን ይመለከታል። እነዚህና መሰል ክንውኖች ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የተለያዩ የሚሆኑበት አጋጣሚ በመኖሩ ልዩነቱን ከነአንድምታው ማጥናቱ ተገቢነት አለው። በአንዱ ማህበረሰብ የግንዛት ስርዓት ሲፈፀም በሸማ (ነጠላ፣ ጋቢ) አስከሬን መጠቅለል እንዳለ እናስተውላለን። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ በትኩስ የበሬ ቆዳ አስከሬኑ ተጠቅልሎ የግንዛት ስርዓቱ ይከናወናል።

የሟችን የቀብር ሁኔታ መወሰን (ሰዓቱን፣ ቀኑንና የቀብር ቦታውን)፣ ለዘመድ ወዳጅ የማርዳት ክንውን እንዲሁም ለሀዘንተኛ በአጠቃላይም ለለቅሶው ተሳታፊ የሚሆን ምግብ ዝግጅት የመሳሰሉት ሁሉ ተጠቃሽ ቅድመ ቀብር ተግባራት ናቸው።

2.2.2 ወቅተ ቀብር ክንውኖች

በዚህ ወቅት እንደ ማህበረሰቡ እምነትና የኑሮ ፍልስፍና ቦታ መርጦ የሟችን ግብዓተ መሬት የሚፈፅምበት ወቅት ነው። ለሟች የሚደረግ የለቅሶ፣ ሙሾና ርግዶ እና መልስ የሀዘን መገለጫ ድርጊቶች የሚከናወኑበት ወቅትም ነው። አስከሬን ሲቀበር የሚይዘው አቅጣጫ የወቅት ቀብር ክንውን አካል ነው።

በዚህ ወቅት ሟችን ገደለው ተብሎ እንደሚታመነው በሽታ ሌሎች ልማዳዊ ክንውኖችን እንመለከታለን። ከነዚህም ውስጥ ሟች የሞተው "በባለጅ" ወይም "በቡዳ ተበልቶ" ነው ተብሎ ከታሰበ ወይም ከታመነ ከአስከሬኑ ጋር የተለያዩ ብረቶች አብረው የቀበራሉ። ይህ ተግባር የሚከናወነው "የበሉት ሰዎች" አውጥተው አሽከር ወይም ሰራተኛ እንዳያደርጉት

ለመከላከል የሚዘየድ (ይህ ተግባር በተለይ በሰሜን ሸዋ በስፋት ይታያል) ነው። በመኢኒት በሄረሰብ ደግሞ አስከሬን መጠበቂያ ጎጆ የመስራት በህል አለ።

2.2.3 ድህረ ቀብር ክንውኖች

የሚች ግብአተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ የሚደረግ ክንውን እንደየ ባህሉና ማህበረሰቡ እምነት የሚለያይ ቢሆንም የተለያዩ ክንውኖችን በድህረ ቀብር እናገኛለን። ከነዚህም ውስጥ ሀዘንተኞችን መሰናበት፣ በሚች ቤት የተዘጋጀን ምግብ መመገብ የመሳሰሉትን እናገኛለን። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ምግብ ከመመገብ በፊት አስከሬን የወጣበት ቤት ውስጥ ደም ማፍሰስ (ማረድ) የሀዘንተኞችን መቀመጫ አስተካክሎ እንዲቀመጡ ማድረግ የመሳሰሉት ክንውኖች ይገኛሉ። በሚች ቀብር ላይ ምልክት ማኖር እንዲሁም እፅዋት መትከል ሁሉ በድህረ ቀብር ክንውን የሚካሄዱ ናቸው። በተጨማሪም ሚችን መዘከር ወይም ለሚች መታሰቢያ ማዘጋጀት፣ በተጠኚው ማህበረሰብ ደግሞ ከሀዘን የመንፃት ፕሮግራም ማዘጋጀትና የመሳሰሉት ይጠቅሳሉ።

በአጠቃላይ በቀብር ስርዓት ላይ የሚደረጉ ክንውኖች ከቦታ ቦታ፣ ከማህበረሰቡ ማህበረሰብ ልዩነት ቢኖራቸውም ክንውኖቹ በጋራ (በቡድን) የሚከናወኑ መሆናቸው፣ ልማዳዊ ተግባራት በእጅጉ የሚስተዋልባቸው በመሆናቸው ይመሳሰላሉ። ክንውኖቹ ለስርዓቱ ተካፋዮች ስሜትን ማነሳሻና የተሰማቸውን መግለጫ (መተንፈሻ) በመሆንም ያገለግላሉ። ስለዚህም ይህን ነጥብ ማጥናቱ ተገቢነት አለው።

2.3 ማህበራዊ ደረጃ እና የልቅሶ ስርዓት

በእያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደየ ባህሉ እና ወጉ ለተለያዩ የማህበረሰቡ አባላት የሚሰጣቸው ደረጃ እና የሚያከናውኗቸው ተግባራት አሉ ወይም ይኖራሉ። ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ማንኛውም አባል የራሱ ሚና ወይም ኃላፊነት እንዲኖረው ያደርጋል። ማህበራዊ ደረጃ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጥ የክበሬታ እንዲሁም የግብር ክፍፍልን ከማሳየቱ በተጨማሪ አንድ የማህበረሰቡ አባል በማህበረሰቡ ውስጥ ካለው ቦታ የተነሳ በሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖም ያሳያል። “Status in the abstract is a position in a particular pattern” (Linton, 1964:113) በማለት በማህበረሰቡ የሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለን ቦታ የሚያሳይ መሆኑን ያስረዳሉ።

ማህበረሰቡ ለአንድ ግለሰብ አንድ ማህበራዊ ደረጃን ሲሰጥ ከግለሰቡ የሚጠብቀው ተግባር አለ። ምክንያቱም ሹመት አልያም አንዳች ማህበራዊ ደረጃ የሚሰጠው ለሚጠበቀው ተግባር ግለሰቡ በእድሜ፣ በፆታ፣ በሀብት ንብረት መጠን እንዲሁም በጀብደኝነትና በመሳሰሉት ማህበራዊ መዋቅሮች ብቁ ነው ብሎ በመታመኑ ነው። ይህን ሀሳብ ይበልጥ እንዲያብራራልን የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፡

> *The relation between any individual and any status he holds is some what like that between driver's seat with its steering wheel, accelerator and other control is constant with ever present potentialities for action and control while the driver may be any member of the family and may exercise these potentialities very well or very badly (Linton, 1964:113).*

ማህበራዊ ደረጃ ከሚሰጥባቸው መንገዶች መካከል እድሜና ፆታ ዋነኞቹ ናቸው Linton 1964:119) በእድሜና በፆታ የሚመጡ ማህበራዊ ደረጃዎች ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ከእነዚህ ውጭም በማህበረሰቡ የሚሰጡ ደረጃዎች አሉ። አንድ ሰው ባለው እውቀት፣ ጀግንነትና ኃይለኝነት፣ ደግነትና ለጋስነት፣ ወዘተ. የተወሰነ ማህበራዊ ደረጃን ሊያገኝ ይችላል (Haebel, 1966:311)።

ዕድሜና አወላለድን በመሳሰሉ ተፈጥሯዊ ምክንያቶች የሚሰጡ ማህበራዊ ደረጃዎች በሁሉም የሰው ልጅ ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ያሉ ሲሆን የደረጃው ባለቤቶች የሚኖራቸው ሚና የተለያየ ነው። ምንም እንኳን ሚናና ተግባራቸው በየማህበረሰቡ የሚለያይበት ሁኔታ ቢኖርም ሁልጊዜም ደረጃቸው ከሚናው ይቀድማል። በአንባሩ ደግሞ በስራ የሚገኘው ማህበራዊ ደረጃ ከደረጃው ተግባሩ ነው የሚቀድመው። አንድ ሰው በአንድ ስራ ለምሳሌ በአደን የበቃ አዳኝ ሲሆን ለብቁ አዳኞች የሚሰጠውን ማህበራዊ ደረጃ ያገኛል። ይህን ሀሳብ አስመልክተው፡-"... societies mark the individual's progression from role to role by changing his name or by giving him designations that indicate each particular role." (Brown, 1963:49) ጥቅሱ እንደምንመለከተው አንድ ግለሰብ በሚያሳያቸው የተግባር ሽግግሮች ማህበረሰቡ የስያሜ ለውጥ ያደርግለታል። በተጨማሪም ስያሜውም ለተግባሩ የሚገባውን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያመለክት እንረዳለን።

ተፈጥሮን መሠረት አድርገው ከሚሰጡ ማህበራዊ ደረጃዎች አንዱ እድሜ ነው። እድሜን መሠረት አድርጎ የሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ በሁሉም ማህበረሰቦች ዘንድ ያለ ነው። ሆቤል

(Hoebel, 1966:34) ይህንን በተመለከተ ሲያብራሩ በአጠቃላይ ሦስት የዕድሜ ምድቦች መኖራቸውን ያስረዳሉ።

ሌላውና ተፈጥሮን መሠረት አድርጎ ማህበራዊ ደረጃ የሚያሰጥ ጉዳይ ፆታ ነው። የፆታ ልዩነት ተፈጥሯዊ ክስተት ነው። ልዩነቱን መሠረት አድርገው በባህል የሚወሰኑ ደረጃዎች ይገነቡበታል። (Hoebel) እንደ መውለድ ካሉ ተፈጥሯዊ ተግባራት በስተቀር በፆታ ልዩነት ዙሪያ ሳይንሳዊና ባህላዊ የሆኑት ባህሪያት ተለይተው አለመቀመጣቸውን ጠቁመው እያንዳንዱ ማህበረሰብ ግን ወንዶችና ሴቶች የተለያየ ሚና እንዲኖራቸው መፈለጉና ተግባራቸውም መለያየቱን ይገልፃሉ። (Hoebel, 1963:313) ይህንን ሀሳብ አስመልክተው በፆታ የሚሰጥ ደረጃ በሁሉም ማህበረሰብ መሠረታዊ ጉዳይ ተደርጎ እንደሚወሰድ ያስረዳሉ። ምንም እንኳን በየማህበረሰቡ ለሴትም ሆነ ለወንድ የሚሰጠው የስራ ድርሻ ቢለያይም።(Linton,1964፡117) የፆታ ሚና እያንዳንዱ ባህል ወይም ማህረሰብ ለፆታዎቹ የሚያወጣው የስራ ድርሻ መሆኑን ገልፀው በፆታዎቹ መካከል ያሉት አብዛኞቹ ልዩነቶች ከተፈጥሮ ይልቅ በባህል አማካይነት የሚከሰቱ መሆናቸውን የሚናገሩት ደግሞ ኮታክ (Kottak) ናቸው። *Gender refers to the cultural construction of sexual differences. Male and female are biological sexes that differ in their x and y chromosomes culture takes that biological difference and associates it with certain activities: behavior, and ideas (Kotatak 2002:460).*

በአጠቃላይ ሰዎች በበቀሉበት ማህበረሰብ የተሰጣቸውን ማህበራዊ ደረጃ የሚያገኙት በተለያዩ መንገዶች ነው። ይሁንና ሰዎች ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸው ደረጃ በተለያየ መልክ ይገለፃል። ከነዚህ መገለጫዎች ደግሞ የለቅሶ ስነስርዓት አከዋወን አንዱ ነው። ሟች በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳለው ማህበራዊ ደረጃ የለቅሶ ስነስርዓቱም ይወሰናል። ጀግና ሲሞት የሟችን ጀግንነት በሚዘክር አኳኋን የለቅሶ ስነስርዓት ይከናወናል። ሟች ህፃን ከሆነ ደግሞ እንደ ማህበረሰቡ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ቢለያይም ለእድሜ ባለፀጎች (አዛውንቶች) የሚደረገው የልቅሶ ስርዓት አይካሄድለትም። ስለዚህም የለቅሶ ስርዓት በሟች ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል። ይህንን ሀሳብ "When death takes... some important member of the group the whole community becomes involved every where people the fact of grief and almost every where there are patterns of mourning" (Brown, 1963:60) በማለት ያስረዳሉ።

በማህበረሰቡ ከፍ ያለ ማህበራዊ ደረጃ የተሰጠው ሰው መሞቱ ሲሰማ የሀዘኑ ሁኔታም በሁሉም ማህበረሰብ ተሳታፊነት ይከናወናል። በለቅሶ ሥርዓቱ የሚካሄዱ ክንውኖች ለየቅል ናቸው። ይህም ማለት የእድሜ ባለፀጋ ከህፃን ልጅ ለቅሶ ክንውን በተለየ መልኩ ይካሄዳል። ወጣት ሚች ከጀግና ወይም ከሌላ ማህበራዊ ደረጃ ባለቤት በተለየ መልኩ የለቅሶ ሥርዓቱን ይከወንለታል።

በዚህ ክፍል በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ የንድፈ ሃሳባዊ መረጃዎች ቀርበዋል። በዚህም የለቅሶ ሥነሥርዓት ምንነትና ለቅሶ ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር እንዴት ይከናወናል የሚሉትን ነጥቦች በጥቂቱ ለማየት ተሞክሯል።

በዚህም የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ እና የክዋኔ ግብዓት የሆኑት እንደከዋኝ፣ ተሳታፊ፣ የመከወኛ ቁስ፣ የክወና አመላካቾች ተዳሰዋል። በለቅሶ ስነስርዓት ውስጥ አንድ ክንውን የሆነው የቀብር ስነስርዓትንም ለማየት ተሞክሯል።

2.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

እስካሁን በተደረገ ቅኝት የመኢኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔን ያሳየ ጥናት አልተገኘም። ይሁን እንጂ ለመነሻነት የተገለገልኩባቸው አስራ ዘጠኝ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ዕሑፎች (ሁሉም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ተማሪዎች የተሰሩ ናቸው) አንድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት (ከኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የተገኘ ነው) እና አራት ለተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡ በድምሩ ሃያሦስት ተዛማጅ ጥናቶችን ቃኝቻለሁ። በዚህም መሰረት ከልቅሶ ስርዓት ክዋኔ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ምክንያቶችን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል።

ቅኝት የተደረገባቸውን ጥናቶች ከመዘርዘር ይልቅ ልዩነታቸውን እንዲሁም አንድነታቸውን በሚያሳይ መልኩ በተጨማሪም ድግግሞሽን ለማስወገድና ለአሰራር ያመች ዘንድ ባነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳስሎ ለመመደብ ተሞክሯል። በዚሁ መሠረት የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ያጠኑ እና የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ከሙሾ፣ ቀረርቶና ፍካሮ ጋር አያይዘው ያጠኑ በማለት በሁለት ምድብ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል። አቀራረባቸው እንደተጠኑበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል ሲሆን በተመሳሳይ ዘመን የተጠኑና በአንድ ምድብ የሚካተቱ ጥናቶች ሲያጋጥሙ በጥናት አቅራቢዎች ስም ፊደል ተራ ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል።

2.4.1 የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ያጠኑ

ታደሰ መንግስቱ (1963)፤ "የጎጃም ለቅሶ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፉን አቅርቧል። በጥናቱ የሚችን ስም እንደ ርዕስ በመገልገል ጥቂት ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ በቀጥታ ወደ ሙሾ ግጥሞቹ ይገባል። ስራው በአጠቃላይ ትንታኔ የለውም። የልቅሶ ግጥሞቹ በይዘትም ሆነ በቅርፅ ያልተተነተኑ ስብስቦች ናቸው።

በታደሰ ጥናት ላይ የታየው ክፍተት በማጠቃለያው ላይ ጥናቱ በተካሄደበት ማህበረሰብ በአብዛኛው ገዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት ግጥሞች የወል ቤት፣ የወል ታጣፊ፣ ደጋጋሚና ከብረሽ ቆይኝ አይነት እንደሚታይባቸው ገልፃDል። ለዚህ ማጠቃለያው ማስረጃ የሚሆን አንድም ምሳሌ ለማሳየት አለመቻሉ ግን ጥናቱን የተሟላ እንዳይሆን አድርጎታል።

ብርሃኑ መኮንን (1973)፤ "የአማርኛ ሙሾ ግጥሞች ጠባይ፣ ይዘትና የዘይቤ አጠቃቀም" በሚል ርዕስ የዲግሪ ማሟያ ጥናቱን አቅርቧል።

በጥናቱ ይዞት የተነሳው አላማ አማርኛ በሚነገርባቸው አካባቢዎች ያሉ የሙሾ ግጥሞች ተመሳሳይ መሆናቸውን ማረጋገጥና የየራሳቸው ይዘትና ውበት መያዛቸውን ማሳየት ነው። በዚህ ስራው የአማርኛ የሙሾ ግጥሞችን ስነፅሁፋዊ ጠባይ አይቶ የሙሾ ግጥሞቹ በመልከአምድራዊ አቀማመጥ እንደማይለያዩ ለማሳየት ሞክሯል። ከዚህም ሌላ የግጥሞቹን ቅርፅና ዘይቤ በመውሰድ ውበትን (የምን ውበት እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም) ለማሳደግ እንዳገለገሉ አብራርቷል። ይዞት ከተነሳው አላማ አንፃር በስብስቦቹ መሠረት የአማርኛ ሙሾ ግጥሞች ተመሳሳይነትና አንድነት አላቸው ብሎ ለመቀበል የሚያዳግት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ምክንያቱም የጥናቱን ወሰን በግልፅ አለማስቀመጡ ለተቀባይነት ማጣቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። በተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ የባህል ልዩነት ሊኖር እንደሚችልም አለማጤኑ በጥናቱ የሚታይ ክፍተት ነው።

ባልከው ቸርነት፤ (1974) "የመንዝ የለቅሶ ግጥሞች ጥናት" በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል።

ባልከው ለጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የህዝቡን /የመንዝን/ ስነቃላዊ ቅርስ ለመጭው ትውልድ፣ ለባህል አጥኝዎችና ተመራማሪዎች መነሻ ይሆን ዘንድ ግጥሞቹን ሰብስቦ ማቆየት መሆኑን ገልፏል። አያይዞም ይህን አላማ የነደፈው ግጥሞቹ በመጠኑም ቢሆን ባህሉን እንደሚንፀባርቁ ለማመን መሆኑን አያይዞ ገልፃDል።

ጥናቱም በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን የመጀመሪያው የመንገዝ ህዝብ የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን በመንገዝ የሚኖሩ ህዝቦች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የመሳሰሉት የተዳሰሱበት ክፍል ነው። ሁለተኛው የግጥሞቹ ጠባይና ቅርፅ የቀረበበት ነው። ሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ግጥሞቹ በአባሪነት የቀረበቡት ነው።

በአጠቃላይ የለቅሶ ግጥሞች ያሁኑን፣ ያለፈን እና መጪ ጊዜን የሚጠቁሙ መሆናቸውን ፍሬ ሀሳባቸው ለማዘኛ፣ ለመተከጎ፣ ለፀፀት ወዘተ ብቻ የቀረቡ ሳይሆኑ የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ያሳረፈውን ችግር፣ የገጠመውን የህይወት ውጣ ውረድ፣ ለቅሶ በቋሚ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመግለፅ ጭምር የሚያገለግሉ ናቸው። በማለት ጥናቱን አጠናቋል።

ባልከው ለጥናቱ የመረጠው ግሼ የተባለውን አካባቢ ቢሆንም ቦታውን ለምንና እንዴት እንደመረጠው ምንም ያለው ነገር የለም። በተጨማሪም መረጃ የሰበሰበው ከመንገዝ ግሼ አውራጃ መሆኑን ገልፏል። ነገር ግን ቃለመጠይቅ ያደረገላቸው ሰዎች ከተጠቀሰው በተጨማሪ የአዲስ አበባም ነዋሪዎች ይገኙበታል። ይህን ለምን እንዳደረገ (ትውልዳቸው፣ እድገታቸው ወይም አካባቢው ጥናት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን) የገለፀው ነገር የለም።

ሌላው በጥናቱ ላይ ያየሁት ክፍተት መረጃ በምልከታና በቃለ መጠይቅ እንደሰበሰበ ራሱን አስችሎና ርዕስ ሰጥቶ ባይሆንም በመግቢያው ይገልፃል። ስለ መረጃ አተናተን መንገዱ ግን ይህ ነው የሚል ፍንጭ አልሰጠም።

ወርቅነሽ ደምለው (1992)፤ "ጀግና ወንዶችና ሴቶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች (በአቸፈር ወረዳ ዙሪያ)"። በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፏን አቅርባለች።
ወርቅነሽ በአቸፈር ዙሪያ የለቅሶ ስርዓቱን አፈፃፀምን በዕለት የሚፈፀም የለቅሶ ስርዓት እና በቀጠሮ (በምስል) የሚፀም የለቅሶ ስርዓት ተብለው የሚከፈሉ መሆናቸውን አስረድታለች።
በጀግና ለቅሶ የሚደረደሩ የሙሾ፣ የቀረርቶና የፍክሬ ግጥሞች ክዋኔዎችን በመግለፅ የጀግና ለቅሶ የሙሾ ግጥሞችን ከሚች ጠንካራነት፣ የስራ ወዳድነት ከሚች ውለታና በሞቱ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት፣ የአልቃሹን ብሶት የሚጠቅሱ እንዲሁም አልቃሽ ስለሞተና ህይወት ያለውን አመለካከት የሚገልፁ የሙሾ ግጥሞች በሚል በመከፋፈል አስቀምጣለች። ክፍፍሎቹም የጀግና ለቅሶ የቀረርቶ ግጥሞች እና የጀግና ለቅሶ ግጥሞች በሚሉ ርዕሶች የቀረቡ ናቸው።

በወርቅነሽ ጥናት የተመለከትኩት ጠንካራ ጎን የጥናቷ ትኩረት የክርስትና እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ስትገልፅ በምክንያትነት ያቀረበችው ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ የክርስትና እምነትን የሚከተሉ ብቻ የሚኖሩበት መሆኑን በግልፅ ማስቀመጧን ነው። የየትኛው ማለትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የጀባ፣ የአድቬንቲስት ወዘተ. እንደሆኑ በግልፅ ባይቀመጥም።

2.4.2 የልቅሶ ስርዓትን እንዲሁም ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን አያይዘው ያጠኑ

ፋሲካ በለጠ (1953)፤ "The Death Customs Among the Amharas of Sewo" በሚል ርዕስ "Ethnogical society Bulletin" በተባለ መፅሔት የቀረበው ጥናት የለቅሶ ስርዓት ከጎባዜ አፈላፀም ጀምሮ የመርዶው ሁኔታ፣ ለሟች የሚደረግ የፍትሀት ስርዓትና አይነት ወዘተ. ተግባራት የተገለፀበት ነው። ከጥናቱ ርዕሰ እንደምንመለከተው በየትኛው የሸዋ ክፍል ብለን ለምናነሳው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ የወሰን ገለፃ አልተካሄደም። በዚህ የተነሳም የሸዋ አማራ የለቅሶ ልማድ ይህን ይመስላል ብሎ ማጠቃለያ መስጠት የሚያስደፍር አይደለም። ጥናቱ የወሰን መስፋት ችግር ስለሚታይበት በውል የሸዋ አማራን የለቅሶ ልማድ ለማስረዳት የተደረገው ጥረት ግቡን ያልመታ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ነጋ ተሰማ (1953)፤ "The death Customs in the Province of Tigre" በሚል ርዕስ "Ethnological society bulletin" ለተሰኘ መፅሔት ጥናቱን አቅርቧል። በዚህ ጥናትም አጥኝው የትግራይ ክልል የሚደረግ የለቅሶ ስርዓትን ምን መልክ እንዳለው ለማሳየት ሞክሯል። ነገር ግን የጥናቱ ትኩረት የትኛው ወረዳ ወይንም ዞን በተጨማሪም በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የየትኛው እምነት ተከታዮች እንደሆኑ የተገለፀ ነገር የለም።

ነጋ በጥናቱ አንድ ሰው ከሞተበት እስከ ግብአተ መሬቱ ፍፃሜ ያለውን የድርጊት ክንውን የሚያሳይ ነው። ርዕሱ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በትግራይ የሚካሄድን የለቅሶ ልማድ በጥልቀት ለማየት የሚያስችግር ከመሆኑም በላይ በጥናቱ የተገለፀው የለቅሶ ስርዓት የሁሉንም የትግራይ ማህበረሰብ የለቅሶ ልማድ ያሳያል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው። ሐረገወይን ድፋባቸው (1974)፤ "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች"[5] በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፏን

[5] የሐረገወይንን ስራ በዚህ ምድብ ያመጣሁበት ምክንያት በርዕሱ እንደሚታየው የለቅሶ ግጥሞችን ብቻ ሳይሆን የለቅሶ ስርዓቱንም ለማሳየት በመሞከሯ ነው።

አቅርባለች። ሐረገወይን በመግቢያዋ እንደገለፀችው የክስታኔ ህብረተሰብን የለቅሶ ሁኔታ ለማሳወቅ ብሎም መዝግቦ ለማስቀመጥ የሚል አላማ ይዛ ነው ጥናቷን ያካሄደችው።

በጥናቷ የክስታኔ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓትና የግጥሞቹ ባህላዊ ይዘት በሚል ርዕስ በጉራጌ ህብረተሰብ የሚገኙት ጎሳዎች በቋንቋ፣ በሀይማኖት በባህል፣ በለቅሶ ስርዓት ከክስታኔ ብሔረሰብ የተለየ መሆኑን ለማሳየት ሞክራለች።

በትንታኔዋም አንድ ሰው ከሞተበት ጊዜ አንስቶ እስከሚቀበርበት ጊዜ ያለውን ስርዓት እንደ ሚች ማህበራዊ ደረጃ፣ እድሜና ፆታ ክፋፍላ አቅርባለች። ነገር ግን የለቅሶ ስርዓቱን እንደ ሚች ማህበራዊ ደረጃ፣ እድሜና ፆታ ከፋፍላ ያስቀመጠችበትን ምክንያት አልገለጸችም።

የሐረገወይን በሌለው የጥናቷ ክፍል የሚደረደሩ ግጥሞችን ከቅርፅ አንባር የተነተነችበት ነው። በዚህ ክፍል የግጥሞቹን የሀረግና የቀለም አቆጣጠሩን አሳይታለች። ነገር ግን የግጥሞቹ የሀረግና የቀለም አቆጣጠር ስርዓት የአማርኛን ህግን ስርዓት የተከተለ ይሁን የክስታንኛ ወይም የራሱ የሆነ ህግና ስርዓት ይኑረው በግልፅ የተቀመጠ ማብራሪያ ወይም ማስረጃ ምላሌ ያልቀረበ በመሆኑ እንደ አንድ ድክመት የታየ ነው።

ሌላው በጥናቱ ላይ የታየ ክፍተት የክስታኔ የለቅሶ ግጥሞች "ህገወጥ" ቤት አመታት በአብዛኛው የሚታይባቸው መሆኑን እንዲሁም ስንኞቹም በተለያየና በተመሳሳይ ሆሄያት የሚጨርሱ መሆናቸው በተጨማሪም ከዚህ በተለየ ሁኔታ አጨራረስ እንደሚታይባቸው ብትገልፅም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የትና በምን ሁኔታ እንደሚገኝ የቀረበ ማስረጃ የለም።

ንጉሴ አክሊሉ (1974)፤ "ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረጉ ግጥሞች (በምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ)" በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል። ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው የመጀመሪያው ምዕራፍ የኪነተቃልን አመጣጥ ምንነትና ጥቅም ያካተተ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በስነቃሎች ስብስብ ወቅት ከመረጃ አቀባዮች የተገኘውን መረጃ መሠረት አድርጎ ለጀግኖች የሚደረገውን የለቅሶ ግጥምና የፉከራ ሁኔታ ይጠቁማል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጀግንነት መገለጫ ስለሀገር መሞት /patriotizem/፣ አዳኝ መሆን ወይም ግዳይ መጣል መሆናቸውን ያስረዳበት ክፍልም ይገኛል። በሌላ በኩል አስታራቂ ሽማግሌና ለጋስ ሰው ሲሞትም የለቅሶ ስርዓቱም በጀግና ደንብ የሚካሄድ መሆኑን አስረድቷል። ሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የለቅሶ ግጥም አወራድና ክዋኔው እንዴት እንደሆነ ያሳየበት ክፍል ነው።

በዚህም መሠረት የተሳታፊዎች እንቅስቃሴ የመከወኛ ቁሶች እንዲሁም በአልቃሽና በአስለቃሽ መካከል ያለውን ግንኙነት በአጠቃላይ ክዋኔው የተብራራበት ክፍል ነው።

አራተኛው ምዕራፍ ለጀግኖች የሚገጠሙ ግጥሞች ለ"ተራኪው" ከሚገጠሙት የሚለዩበትን መንገድና ሁኔታ ያስረዳል። አምስተኛው ምዕራፍ ጠቅለል ባለ መልኩ ለጀግኖች የተገጠሙ የለቅሶ ግጥሞችን ከይዘታቸው አንባር የተነተነበት ነው። በትንተናው መሠረትም ግጥሞቹን ጀግንነትን የሚገልፁ፣ መሪን የሚገልፁ፣ ምኞትንና ተስፋን የሚገልፁ፣ ለመሳሪያዎቹ የተገጠሙ፣ የሞትን ምንነት የሚገልፁ፣ ወዘተ በማለት ምሳሌና ማብራሪያ በማከል አሳይቷል።

አምስተኛው ምዕራፍ የግጥሞቹን ቅርፅ መሠረት አድርጎ በተለይም ለዘይቤያዊ አነጋገሮች ትኩረት ሰጥቶ የተነተነበት ነው።

የንጉሴ ጥናት የወሰን ግልፅ አለመሆን ችግር ተስተውሎበታል። "ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞች (በምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ)" በርዕሱ እንደምናየው በምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ የሚገኙት ቦታዎች የሚያጠቃልል ይመስላል። በምንጃር እና ሸንኮራ አካባቢ ደግሞ ከአማራ ብሔር ውጭ የኦሮሞ ብሔረሰብ ይገኛል። በዚህ በኩል መረጃ ከናዝሬት መሰብሰቡን (በየትኛው ቋንቋ እንደሆነ አልተገለፀም) መግለፁ ከጥያቄ የሚያስመልጠው ነው። ነገር ግን በኦሮሞና በአማራ መካከል የቋንቋ፣ የባህልና የመሳሰሉት ልዩነቶችን እንዴት እንደተመለከተው የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ በጥናቱ የታየ ክፍተት ነው።

ሌላው በንጉሴ ጥናት የታየው ክፍተት ያለ እድሜ ለተቀጠፉ ህፃን የቀረበ የሙሾ ግጥም አለ በማለት አሳይቷል። ሆኖም ግን የሙሾ ግጥሞቹ በምን ያህል እድሜ ክልል ላሉ ህፃናት የሚቀርቡ እንደሆነ ግልፅ አለማድረጉ ነው።

በመጨረሻም በጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ የቀረበበት ቦታ ስለሌለ የጥናቱ ግኝት ምንነት አልታየም። አጥኚውም ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ያድርስ አያድርስ የሚያሳውቅና የሚጠቀም ነገር የለም።

ድጋፌ ፈይሳ (1975)፤ "የሲዳማ ብሔረሰብ ለየለቅሶ ስርዓት።" በሚል ያቀረበው ጥናት በዋናነት ትኩረት የሰጠው የለቅሶው ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ያለውን የቀብር ስነስርዓት አፈፃፀም ሁኔታ ማሳየት ነው። በዚህም ከስርዓተ ግንዘት እስከ ቀብር ስርዓት

ያሉትን ክንውኖች በቅደም ተከተል አስቀምጧል። ከዚህም በተጨማሪ የሲዳማን የለቅሶ ስርዓትና የግጥሙን ዝምድና ከተለያዩ ይዘቶች አኳያ ተመልክቷል።

የሲዳማን የለቅሶ ስርዓት ለህፃን ለአዋቂ ብሎ በሁለት መከፈል እንደሚቻልና የአዋቂዎችን የለቅሶ ስርዓት እንደገና ለተራ ሰዎችና ለትልቅ ሰው "የጨመሳ" ተብሎ በሁለት ይከፈላል በማለት የሲዳማን የለቅሶ ስርዓት በእድሜና ሚች በህብረተሰቡ ዘንድ ባለው ደረጃ ለይቶ ማጥናት የሚቻል መሆኑን ገልፏል።

አስመላሽ ወ/ማርያም (የአባትስም ወ/ማርያም ተብሎ ነው የተፃፈው) እና ጽጌረዳ ተክሌ (1980)፤ "በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልዕክቶች" በሚል ርዕስ ጥናታቸውን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ሴሚናር ጥናት አቅርበዋል።

የጥናቱ አቅራቢዎች የመሸ ግጥሞች የመከወኛ ምክንያት የለቅሶ ስርዓት አይነት የሆነውን የቀብር ስርዓት እና የመታሰቢያ ስርዓቶችን (አርባ፣ ሰማኒያና መት ዓመት) መሆናቸውን አሳይተዋል።

በተጨማሪም በለቅሶ ላይ አልቃሾች የሚያነሷቸው ግጥሞች ሚችን በተመለከተ ብቻ የሚገጠሙ አለመሆናቸውን ይልቁንም የለቅሶ መኖርን በምክንያትነት በመጠቀም የህብረተሰቡን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሁሉ የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን አሳይተዋል።

መዓዛ ተስፋይ (1982)፤ "በዐጋመ አውራጃ የቀብር ስነስርዓት አፈፃፀምና የለቅሶ ግጥሞች የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናቷን አቅርባለች።

መዓዛ በጥናቷ በዋናነት ትኩረት ያደረገችው በአጋመ አውራጃ የለቅሶ ሥነሥርዓት አፈፃፀምን ማሳየት ላይ ነው። በዚሁ መሠረት ሁለተኛ የቀብር ስነስርዓትንም አፈፃፀም አሳይታለች። ሚች በተላላፊ በሽታ ከሆነ የሞተው አስከሬኑን ከቤት የሚያወጡት ካህናትና በእድሜ የገፉ አዛውንቶች መሆናቸውን ገልፃለች። ይህ በህብረተሰቡ እምነት ካህናቱን ተላላፊው በሽታ አይጠጋቸውም ምክንያቱም በመስቀል ኃይል የሚሸነፍ በመሆኑ፤ አዛውንቶች ደግሞ በሽታው ቢለከፍም ከወጣቶች ይልቅ እነሱ ብዙ አለም ያዩ በመሆናቸው መሆኑን አስረድታለች።

ጥናቷ ለአብዛኛው የመሸ ግጥሞች የሚደረደሩት (በአርባ በመት ዓመት) ከሚደረደሩት በላቀ ሁኔታ በቀብርና በሁለተኛ ቀብር ሥርዓቶች ላይ እንደሆነ ገልፃለች። በመጨረሻም የግጥሞቹን ይዘት ትንተና አሳይታለች።

በአጋመ አውራጃ የሚደረገው የቀብር ስርዓት አፈፃፀም በእድሜ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ. እንዴት እንደሚፈፀም በግልፅ ስላልተቀመጠ የተጠቀሰውን አውራጃ የለቅሶ ሥርዓት በግልፅ ለመረዳት የሚያስችል አይመስልም።

አየለ መሰሬ (1986)፤ "የሀድያ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የጥናቱን ትኩረት የሆነው የሀድያ ብሄረሰብና የለቅሶ ስርዓቱን ዳራ እንዲሁም የጥናቱን አላማ፣ ወሰን እና የአጠናን ስልቱን የገለፀበት ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ የሀድያ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ከቅድመ ቀብር እስከ ድህረ ቀብር ክንውኖች በስፋት የተዳሰሰበት ነው።

በዚሁ መሠረት ሟች አረጋዊ ከሆነ አስከሬኑ ሳይቀበር ከ3-6 ቀናት ሊቆይ እንደሚችል ሟች ጀግና ከሆነ ደግሞ አስከሬኑ ሳይቀበር 3-6 ቀን ይቆያል። ነገር ግን አረጋዊያን ሲሞቱ ለቅሶውን ይፋ ለማውጣት ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል በተለየ መልኩ በገበያ ልፈፋ የሚካሄድ መሆኑን ገልፃል።

የቀብር ስርዓት አፈፃፀምን አስመልክቶ ደግሞ ህፃናት (እስከ አንድ ዓመት ያሉትን) ስብዕና አላገኙም ተብሎ ስለሚታን ሳይለቀስ በድብቅ እቤት ውስጥ የሚቀበሩ መሆኑን ገልፃDል። በማህበረሰቡ ህፃን ጠፍጣል እንጂ ሞታል እንደማይባል ገልፃDል። አራሽ (ገበሬ) የሆነ ሰው ሲሞት ቀብሩ በእርሻው ውስጥ ይፈፀማል። ወጣቶች ሲሞቱ ደግሞ በመራር ለቅሶ የሚችን ፆታ በሚጠቁመው የለቅሶ ግጥሞች ታጅበው የሚቀበሩ መሆኑን አስረድቷል። ሙሽሮች ሲሞቱ ደግሞ ሀዘኑ መሪር እንደሚሆን ገልፃል። አዛውንት የሚል ርዕስ ሰጥቶ ስለሞት ድንገት ደራሽነት ከመግለፅ ውጭ ሌላ ያለው ነገር የለም።

አየለ ሟችን እንደገደለው የበሽታ አይነት የለቅሶ ሥርዓቱም የሚወሰን መሆኑን በማመላከት በስጋደቄ ህመም ለሞቱ ሰዎች የማይለቀስ መሆኑን ጠቁሟል። ከሟች ቤትም ከተሰራ ምግብ የሟች ቤተሰብ እራሳው እስኪቀበር ምንም እንዳይቀምሱ የሚከለከል መሆኑን፣ የመገነዝና የመቅበር ስርዓቱን የሚፈፅሙት ፋጋዎች /ቆዳን በመፋቅና በሽክላ ስራ/ የሚተዳደሩ መሆናቸውን አስረድቷል።

ድህረ ቀብረ ክንውኖች በሚል ርዕስ ከቀብር በኋላ ያሉ ዝግጅቶችን የመታሰቢያ ድግስ፣ የመቃብር ላይ ተግባሮች በሚል በዝርዝር አሳይቷል። በዚህም የሚች ቀብር እርሻ ውስጥ ቢሆንም እንደማይታረስ ይልቁንም የሚከበርና እንደ "አድባር" የሚቆጠር መሆኑን እንዲሁም በሚች የበኩር ልጅ ሚች ዓመት እስኪሞላው ድረስ ወተትና ማር ያፈስለታል። ይህም ሚች "ያምረዋል" በሚል የሚከወን መሆኑንገልፏል። ሌላው በድህረ ቀብር ክንውኖች ያነሳው ነጥብ የስልጣን መወራረስን ነው።

የሙሾ ግጥሞቹን በሀድያ ቋንቋና በአማርኛ አቻ በማስቀመጥ በይዘት ለሀብታሞች፣ "ለዘረብርቱዎች"፣ በውጊያ ጀግንነትን ላሳዩ፣ አድነው ለገደሉ፣ ወዘተ. በማለት መድቦላቸዋል።

ጌጡ ታደሰ (1986)፤ "ክዋኔ በሳንደር ከተማ ለቅሶ ሥነሥርዓት" በሚል ርዕስ የመመረቂያ ፅሁፉን አቅርቧል። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍም በሳንደር ከተማ ውስጥ በርካታ ማህበራዊ ልማዶች መኖራቸውን ገልፏል። በተጠቀሰው ቦታ በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ ልማዶች በለቅሶ ክዋኔው ባሉ ተሳታፊዎች የሚከናወኑ መሆኑን ገልፏል።

ጌጡ በክዋኔ ወቅት ስነቃላዊ ግጥሞች በዜማ ከመውጣታቸው ጀምሮ ስሜትን ለመግለፅ የሚያስችሉ (የስሜት መገለጫ የሆኑ) የአካል እንቅስቃሴዎች የገፅታ መቀያየርና የመሳሰሉትን ተመልክቷል። በዚህም የለቅሶ ክዋኔው፣ የቀብር ስርዓት አፈፃፀም እና የለቅሶ ግጥሞች እንደ ሚች ወገን ማንነት እና ማህበራዊ ደረጃ የሚለያይ መሆኑን አስረድቷል። በዚህም ለመንፈሳዊ ሚች ቀረርቶ፣ ፋከራና እርግዶ አይታይም ይልቁንም መንፈሳዊ ዜማ፣ ወረብና ሽብሸባ የሚደረግ መሆኑን አስረድቷል። ከዚሁ ጋር አያይዞ የሚች ቤተሰቦች ካባ ደርበው ለቅሶ ሊደርስ የመጣውን ቆመው በማልቀስ እንደሚያስተናግዱ ገልፏል። ይሁን እና ለምን ይህን የልብስ አይነት ለብሰው እንደሚያለቅሱ ያስቀመጠው ነገር የለም። በተጨማሪም ለመንፈሳዊ ሚች ለምን አለማዊ ሰው የሚከወነው ስርዓት እንደማይካሄድ ግልፅ በሆነ መልኩ አላስቀመጠም። በተጨማሪም ርዕሱ ሰፋ ከመሆኑ የተነሳ ለእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል የሚደረገው የለቅሶ ስነስርዓት በአግባቡና በጥልቀት አልታየም። በዚህም የተነሳ በጥናቱ አንድ የሳንደር ከተማን የለቅሶ ክዋኔ ሲገልፅ ትኩረት ያደረገው በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሆኑ ሁለት በየአካባቢው (በሳንደር ዙሪያ) ከሚካሄደው የለቅሶ ስርዓት ጋር ያለውን አንድነት ወይም ልዩነት የሚያሳይ አለመሆኑ በጥናቱ የታዩ ችግሮች ናቸው።

የለቅሶ ስርዓቱን የሚች ነብስ ከወጣበት ቅጽበት እስከ ስርዓተ ቀብር ያለውን ክንውን በስፋት በማሳየቱ ደግሞ በጠንካራ ጎንነት የሚታይ ነው።

ወርቁ ማንደፍሮ (1987)፤ "በሊቦ ከምከም ወረዳ የልቅሶ ሥነሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች" በሚል ርዕስ በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ በሊቦ ከመከም ወረዳ የሚከናወነውን ስርዓት አሳይቷል። በዚህም አንድ ሰው ነብሱ ከስጋው ከተለየችበት ሰዓት እስከ ቀብር ድረስ የሚከናወኑ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ክዋኔዎችን ተመልክቷል። በስርዓቱ የሚከወኑ የሙሾ ግጥሞችንም ተንትኗል። በትንታኔውም ለእናት፣ አባት፣ ለወንድም፣ ለእህት፣ ለጀግናና ለመሳሰሉት የመሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች እና ፍካሬዎች ከፋፍሎ አሳይቷል። ይሁን እንጂ ለምን በእነዚህ ማህበራዊ ደረጃዎች ለመከፋፈል እንደፈለገ ምክንያት አላስቀመጠም።

የጥናቱን ወሰን በሊበከምከም የሚኖሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሆናቸውን መግለፁ እንዲሁም የሙሾ ግጥሞቹን በይዘት ተንትኖ ማስቀመጡ በጠንካራ ጎንነት የሚታዩ ናቸው።

Jon Abbink 1990 "The Final Rite: Burial Amang the me'en of sourth west Ethiopia" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ባቀረቡት ጥናት በብሔረሰቡ ከሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ አንዱ በሆነው በአረጋውያን ሞት ላይ ትኩረት አድርገዋል። ይሁን እና ጥናቱ የብሔረሰቡን የቀብር ሥርዓት እንደሚወክል ተደርጎ ነው የቀረበው። ከዚህ ባሻገር በቀብር ሥርዓቱ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ጥናት ነው። ይህ ደግሞ ከለቅሶ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ መሆኑ ልብ ይሏል።

ወርቃየሁ አረጋ (1995)፤ "የአዊ ህብረተሰብ ሲንቲ (የለቅሶ ሥርዓት እና የአዋኒ ዝንዚመኒ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍን አቅርባለች። በጥናቷም ትኩረት ያደረገችው የአዊ ብሔረሰብን የለቅሶ ስርዓትና የአዊኛ የሙሾ ግጥሞች በሚል ርዕስ በየታ ከፋፍላ ማቅረብ ላይ ነው። ነገር ግን በዚህ መልክ ለማቅረቧ በምክንያትነት ያስቀመጠችው ነገር የለም።

ወርቃየሁ በርዕሷ ላይ የ"አዊ" የሚለውና የ"አዊኛ" የሚለው ህብረተሰቡ የሚገኝበትን ቦታ (አካባቢ) የሚገልፅ ይሁን ወይንም በአካባቢው የሚነገረው ቋንቋ በግልፅ አልተቀመጠም።

የጥናቱ አቅራቢ በአዊ ህብረተሰብ የሚደረግ የለቅሶ ስርዓትን ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜና በድህረ ቀብር ያሉ ክንውኖች በማለት በስፋት ተመልክታለች። በዚህ መሠረትም በስርዓተ

ቀብር ወቅት የሙሾ አወራረድ፣ ሥርዓተ ቀብሩን በማስፈፀም ረገድ የእድሮችን ተግባር በተጨማሪም ከቀብር መልስ የሚካሄዱ ተግባራትን በስፋት አሳይታለች።

ዘላለም ኢዮብ (1995)፤ "በጎፍ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዮሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነግጥማዊ ገፅታ" በሚል ባቀረበው ጥናት አላማ አድርጎ የተነሳው በጎፍ ህብረተሰብ የሚከወነውን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ለማያውቁት ከማላወቅ ውጭ በስነቃሉ (በለቅሶ ግጥሞቹ) የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ እምነትና ማህበረ ባህላዊ ጉዳዮች ተመልክቶ የሚጠቅምና የሚጎዱት ለመለየት መሆንን በመግቢያው ገልፏል።

የዘላለም ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው መግቢያውን እና የጥናቱን አቀራረብ የያዘ ነው። በምዕራፍ ሁለት ተዛማጅ የሆኑ ጥናቶች የተቃኙበት ነው። ሦስተኛው ምዕራፍ የጥናቱን አካባቢና ማህበረሰቡን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተመለከተበት ነው። በአራተኛው ምዕራፍ የባህላዊ ለቅሶው ገፅታና ክዋኔን የተመለከተበት ነው። በዚህም መሠረት የጎፍ ብሔረሰብ የለቅሶና የሀዘን ሁኔታ፣ የለቅሶ ባህላዊ አቀማመጥ ከማሳየቱም በተጨማሪ በብሔረሰቡ የሚከናወን የለቅሶ ስርዓትን ከህፃን እስከ አዛውንት በመከፋፈል አሳይታል። በተጨማሪም የለቅሶ ቅድመ ዝግጅት፣ የመቃብር አዘገጃጀትና የቀብር ስርዓቱ ምን እንደሚመስል አሳይታል። በጎሳዎች መካከል በሚኖር የደረጃ ልዩነት ምክንያት በመቃብር ስፍራዎች ላይም ልዩነት እንዳለ አሳይታል።

ዘላለም በጥናቱ በማህበረሰቡ የተለያየ ማህበራዊ ደረጃ የተሰጣቸው ሰዎች ሲሞቱ በስርዓተ ቀብር አፈፃፀሙ ላይ የተለያዩ ድርጊቶች የሚከወኑ መሆናቸውን አስረድታል። የክንውኖቹን ትርጉሙም የማህበረሰቡን እምነትና ፍልስፍና የሚያነፀባርቁ መሆናቸውን በምሳሌ በማስደገፍ ገልፏ ል። በተጨማሪም ለለቅሶ ስርዓቱ የሚካሄዱ /የሚደረደሩ/ የሙሾ ግጥሞችን በመተንተን አቅርቧል። የግንዘት ሁኔታም በሟች ማህበራዊ ደረጃ የሚወሰን መሆኑን አስረድታል።

ዘላለም ከላይ የተጠቀሱትን ጠንካራ ጎኖች ቢያሳይም የጥናቱ ትኩረት የለቅሶ ግጥሞ ወይም ስነቃል ሲሆን የተጠቀመባቸው የንድፈ ሀሳብ ድርሳናት የስነ ጽሑፍ መሆናቸው ነው። ምንም እንኳን የስነፅሁፍ መሠረቱ ቃላዊ ስነፅሁፍ ቢሆንም በጥናቱ ይህ ዳራ ከዋናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወይም በተናጠል ካለመነሳቱ ጋር በተያያዘ እንደ ክፍተት ተመልክቸዋለሁ። በተጨማሪም የሙሾ ግጥሞቹን ስነግጥም እያለ ነው የተነተናቸው።

በባህላዊ ለቅሶው የሚከወኑ የሙሾ ግጥሞችን ከባህሪያቸው አንፃር በሚል ርዕስ የቃላት ምርጫን፤ የዘይቤ አጠቃቀምንና ግልጋሎቱን ከእድሜ አንፃር ተመልክቷል።

በመጨረሻም የለቅሶ ግጥሞቹ ለስሜት ቅርብ መሆናቸውን አከዋወናቸው ላይ የታዳሚን ቀልብ ለመግዛት እንዲችሉ ተደርጎ በወንድም በሴትም የሚከወኑ መሆናቸውን አስረድቷል። በዚህ ወቅት የሚች የቅርብ ዘመዶች ከማልቀስና ከማዘን በተጨማሪ በለቅሶው ላይ ማን መጥቶ ማን እንደቀረ የመቆጣጠር ኃላፊነት ያላቸው መሆኑን ገልጿል። እንደ ፀጉር መላጨት፣ ፈትል ማሰር፣ ጥቁር መልበስ የመሳሰሉት ደግሞ የሀዘን መገለጫ መሆናቸውን ጠቁሟል።

ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር የምግብ ዝግጅት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው መሆኑንም ከአልቃሾችና ከሀዘንተኞች ብርታት መስጫነት ጋር አያይዞ ገልፏል። ለቅሶን ይፋ በማውጣት በኩልም ባህላዊ የመዘፈን መሳሪያዎች ትልቅ ሚና እንዳላቸው አስረድቷል።

የለቅሶ ክዋኔውን በማሳየት በኩል እስከአሁን ቅኝት በተደረገባቸው ጥናቶች የላቀ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

አስቴር አንጀሎ (1997)፤ "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ርዕስ ጥናቷን አቅርባለች። በጥናቷም የጋሞ ብሔረሰብን የለቅሶ ስርዓትና ከግጥሞቹ የሚታዩ ይዘቶችን ትንተና አቅርባለች።

በብሔረሰቡ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት ከእድሜ ከፆታና ከሌሎች ማህበራዊ ደረጃዎች አንፃር እንዴት እንደሚከናወን በዝርዝር አሳይታለች። ሂደቱንም ከስርዓተ ግንዘት፣ የሬሳ ሳጥን ዝግጅት እስከ ግብዓተ መሬት ያለውን ክንውን ሂደት አሳይታለች። በለቅሶው ላይ የሚደረደሩ ግጥሞችንም ይዘትና በማን እንደሚቀርቡ ጠቁማለች።

አስቴር የጥናቷ ትኩረት በሆነው የቁጫ ወረዳ ላይ ተመስርታ የጋሞን ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት አፈፃፀም እንዲሁም የሚደረደሩ ግጥሞች ይዘትን ወጥነት በመደምደሚያዋ ገልፃለች። ይሁንና አንደኛ ወረዳውን ለምን እንደመረጠችው (የጋሞ ህዝብ በስፋት የሚገኝበት፣ የጋሞ ህዝብ ባህል ሳይበረዝ የሚታይበት፣ ... ወዘተ) አለመጠቆሟ በአስቴር ጥናት እንደ ክፍተት የሚታይ ነው።

አስቱር ከጥናቷ ውጤት በመነሳት የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ጠቃሚና ጎጂ (እራስን መጉዳት፣ ሀዘን ማብዛት፣ ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር የተያያዙ ወጭዎች ወዘተ.) በማሳየት ጎጀዎችን ለማስወገድ ጠቃሚዎቹን ደግሞ ለማስቀጠል በብሔረሰቡ በትጋት እንዲሰራ በማሳሰብ ጥናቷን ቋጭታለች።

ካሳው ደሳለው (1997)፤ "የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘትና ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል። በጥናቱም በደብረሲና ከሚገኙ ቦታዎች ውስጥ በለቅሶ ስርዓታቸው የተለዩ ናቸው ያላቸውን አስራ ሦስት ቀበሌዎች መሰረት በማድረግ መረጃን እንደሰበሰበ ገልፏል። በተጨማሪም በወረዳው የሚገኝ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታዮችን የለቅሶ ስርዓትና የክርስትና እምነት ተከታዮች የሚደረድሩትን የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና በማድረግ አቅርቧል። ይሁን እንጂ የእስልምና ተከታዮችን ለምን እንዳላካተተ በተጨማሪም የክርስትና እምነት ተከታዮችን ብሎ ትኩረቱ ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞችን መሆኑ እንደ ክፍተት የሚታዩ ናቸው።

ካሳው በጥናቱ የወረዳውን የለቅሶ ስርዓት ከቅድመ ሞት እስከ ቀብር ያለውን ክንውን አሳይቷል። በዚህም የግንዘት ስርዓትና ለግንዘት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን፣ ለለቀስተኛ የሚሆን የምግብ ዝግጅትን፣ የቀብር ስርዓት በተጨማሪም የፀሎት ሁኔታዎችን በእስልምና እንዲሁም በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ዘርዘር ባለ መልኩ አቅርቧል።

ለሚች የሚደረግ መታሰቢያና ተገኳር መሰረቱ ሃይማኖታዊ ቢሆንም በህብረተሰቡ የተለያዩ ባህላዊ /ልማዳዊ/ ክንውኖችን የሚያካሄድ መሆኑን በጥናቱ አሳይቷል። ከመታሰቢያ ድግሱ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ጉዳት መታሰብ እንዳለበትም አመላክቷል።

በመጨረሻም ለሚች የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ትንተና አቅርቦ ጥናቱን ቋጭቷል።

ተሾመ ሙሉጌታ (1998)፤ "በቤኒሻንጉል ጉሙዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነስርዓት በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት አላማ አድርጎ የተነሳው በወረዳው የለቅሶ ክንውኑ ከማህበራዊ ደረጃ አንባር የሚካሄድ የለቅሶ ስነስርዓትና የሙሾ ግጥሞችን ማስተዋወቅ በመሆኑ የለቅሶ ግጥሞችን ይዘትም ተመልክቷል። በዚህም መሠረት የሙሾ ግጥሞቹ በዘፈን መልክ የሚቀርቡ መሆናቸውን አሳይቷል።

ተሸመ በተጠቀሰው ወረዳ አንድ ሰው ህመሙ ፀንቶ ሳለ ኑዛዜ እንዲያከናውን የሚደረግ መሆኑን ገልፏል። ኑዛዜውን ደግሞ ሽማግሌዎች፣ ወዳጅ ዘመዶች ሁሉ ቆመው የሚቀበሉ መሆኑን አስረድተዋል። የሟች ነፍስ እንደወጣችም ቦርዴ የሚባል ባህላዊ መጠጥ የሚዘጋጅ መሆኑን (ቀድሞ ካልተዘጋጀ) ገልፏል።

የለቅሶ ስርዓቱ እንደ ሟች እድሜና ጀግንነት የሚለያይ መሆኑን አስረድታል።

የቀብር ጉድጓድ ዝግጅትን አስመልክቶ ደግሞ የቀብር ቦታ የሚዘጋጀው ከሟች መኖሪያ ቤት አካባቢ ሲሆን እንደሚችል በተጨማሪም ማንኛውም ሰው በፈለገውና በመረጠው ቦታ መቀበር እንደሚችል በጥናቱ ገልፏል።

ከቀብር መልስ ያለውን ስነስርዓት እና የምግብ የመጠጥ ሁኔታንም ሰፋ ባለ ሁኔታ አብራታል። በዚህም በብሔረሰቡ የሚከናወን የመታሰቢያ ዝግጅትና በውስጥ ያካተታቸውን ጉዳዮች ጭምር በፎቶ አስደግፎ አቅርቧል።

በመጨረሻም ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የአንድ ሰው ሞትን ተከትሎ የሚመጡ ጎጂ ባህሎችን (የሟችን ቤት ማቃጠል፣ የሟችን ወንድም እንዲያገባት ማድረግ ወዘተ. በብሔረሰቡ የሚሰጣቸው ትርጉምና የሚተገበሩበትን ምክንያት በመግለጽ የሚወገዙበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት የይሁንታ ሀሳብ በማቅረቡ የተለየ ጥንካሬ የሚሰጠው ጥናት ይመስለኛል።

እስከ አሁን ቅኝት ከተደረገባቸው ጥናቶች በለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀም ላይ የሚታዩ ጎጂ ባህሎችን ጉዳታቸውን በማሳየት እንዲገዱና እንዲቀሩ ሀሳብ በማቅረብ በኩል ደሳለው (1997)፣ ተሸመ መሉጌታ (1998)፣ አስቴር አንጀሎ (1997) የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ሞገስ ሚካኤል (2002)፤ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚረግ የቀብር ሥነሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፋከራና ክዋኔው" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ ትኩረት ወይም ዓብይ ጉዳይ የጀግና ለቅሶ ስርዓት ነው።

የሞገስ ጥናት በአምስት ምዕራፍ የተከፋፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች እንዲሁም የጥናቱን ጠቀሜታና የጥናቱን ወሰን የያዘ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የተዛማጅ

ጥናቶች ቅኝት የተደረገበት እንዲሁም በጥናቱ የተነሱ ጉዳዮች የንድፈ ሀሳብ መሠረት የተያዘበት ነው። ሦስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ትኩረት የሆነው አካባቢ ዳራ መግለጫ የተሰጠበት ነው። አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱ ዋና አካል ሲሆን በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርዓት እንዲሁም በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና አጠቃላይ ክዋኔው የተተነተነበት ነው። በዚህ መሰረትም የሞገስ ዋና ትኩረት የሆነው የጀግና ቀብር እና በስርዓቱ ላይ የሚካሄዱ ቀረርቶዎች እና ፉከራ ነው። በዚህም በማህበረሰቡ በጀግና ወግ የቀብር ስነስርዓታቸው የሚፈፀምላቸው አዳኞች፣ ከጠላት ጋር የተዋጉ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጠንካራ ገበሬዎችን ብዙ የሚያመርቱ ወይም (የልማት አርበኞች) የሚሰኙት በጀግና ደንብ የሚቀበሩ መሆኑን አሳይቷል። በቀብር ስርዓቱ ወቅትም ለጀግና አይለቀስም የጀግና ሞት ሰርጉ ነውና የሚባል ልማድ መኖሩን ገልፃል።

ሞገስ በጥናቱ ለእያንዳንዱ ድርጊትና ክንውን ፍቺና ትርጉም በመፈለግና ይህንንም በማሳየት ረገድ አላማውን አሳክቷል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ድርጊት በዝርዝር በማሳየትም ጥሩ መረጃ የሚሰጥ ጥናት በማቅረብ በኩል የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የፉክራና የቀረርቶ ግጥሞችን በይዘት ከፋፍሎ በአባሪነት ማስቀመጡ ቃላዊ ጥበቦችን /ስነቃልን/ በመሰነድ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

ሞገስ ለጥናት በመረጠው አካባቢ የሚደረግን የቀብር ስነስርዓትና በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው ብሎ በርዕሱ ያስቀመጠውን በምንም ምክንያት በጀግኖች የቀብር ስነስርዓት ላይ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉክራ ክዋኔ ነጥሎ እንደተመለከተ አልገለፀም። በጥናቱ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮን የቀብር ስነስርዓት ነው የተመለከተው፤ ነገር ግን ይህን ለማድረጉ ምክንያት አለማስቀመጡ ወይም በዚህኛው እምነት ተከታዮች ላይ ብቻ አተኩራለሁ ብሎ ወሰን አለማበጀቱ በጥናቱ የታዩ ክፍተቶች ናቸው።

በአጠቃላይ በጥናቱ ከግንዘት፣ ከፍትሀት፣ ከቀብር አቅጣጫ ወዘተ. ጋር በተያያዘ የሚፈፅመው እርስ በእርስ የሚጣረሱ ልማዳዊና ሃይማኖታዊ ተግባራት የሚከናወኑ መሆኑን አሳይቷል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ቅኝት በተደረገባቸው ጥናታዊ ፅሑፎች ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ክፍተቶች መካከል ከርዕስ መስፋት የተነሳ የተሳሳተ ማጠቃለያ የመድረስ ችግር በግልፅ ታይቷል። ምክንያቱም ለጥናቱ በተመረጠው ማህበረሰብ የተለያዩ ልማዶችና ወጎች እንዲሁም እምነቶችና ፍልስፍና ሊኖሩ ስለሚችሉ አንድ እና ወጥ የሆነ የለቅሶ ስርዓት

ይኖራቸዋል ወደሚል ድምዳሜ መድረሱ ከወሰን ግልፅ አለመሆን የመነጨ ነው። ከዚህ በተለየ ለጥናት የመረጡት ማህበረሰብ የተለያዩ ልማዶችና ወጎች እንዳሉት እንዲሁም የተለያዩ የእምነት ተከታዮች እንደሚኖሩበት ያጤኑም አልጠፉም። ለዚህ ደግሞ ወርቁ ማንደፍሮ (1987) የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችን የለቅሶ ስርዓት የሚመለከት መሆኑን በመግለፅ እና ካሳው ደሳለው (1997) የጥናቱ ትኩረት ሆነው በተመረጡ ወረዳዎች የሚኖሩ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታዮችን የለቅሶ ስርዓት እንዲሁም የክርስትና እምነት ተከታዮችን የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ተንትኖ አቅቧል። ምንም እንኳን የክርስትና እምነት በውስጡ ብዙና የተለያዩ ሃይማኖቶች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን የእርሱ ትኩረት የትኛው እንደሆነ ግልፅ ባያደርግም። በተጨማሪም ወርቅነሽ ደምለው (1992) ባቀረበችው ጥናት ትኩረቷ የክርስትና እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ገልፃለች። የየትኛው ክርስትና እምነት እንደሆነ ግልፅ አላደረገችም ነገር ግን በጥናቷ የተመለከተችው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችን ነው።

በአብዛኛዎቹ የጥናት ዕሁፎች የለቅሶ ስርዓት አፈፃፀምን በማህበረሰቡ ከሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ አንፃር አይተዋል። ይሁንና ለምን እንዲህ (ለሴት፣ ለወንድ፣ ለህፃን፣ ለወጣት፣ ለአዛውንት፣ ለጀግና፣ ለሀብታም) በመከፋፈል ለማየት እንደተነሱ አልገለፁም። የሙሾ ግጥሞቹንም ለወንድም፣ ለአባት፣ ለእናት፣ ለጀግና ወዘተ. የተገጠሙ በማለት በመከፋፈል አስቀምጠዋል። ነገር ግን የሙሾ ግጥሞቹን ለመተንተን በምን መስፈርትና ምክንያት እንደቻሉ ያለመግለፁ ችግር በእጅጉ ተስተውሏል። ከዚህ በተጨማሪም የሙሾ ግጥሞቹ የትና መቼ የተገኙ መሆናቸውን ያልገለፁም አሉ። ይህ ደግሞ አብዛኞቹ የጥናት አቅራቢዎች "ስነቃል በዘመን መለዋወጥ ሳይጠፋ ይሰበሰብና ይጠና" የሚል ይሁንታ ቢያቀርቡም እንደመረጃነት ለማገልገል መቼ ምን በማን ይባል ወይም ይነገር ነበር፤ እንዲሁም እንዴት ይከወን ነበር ለሚሉ ጥያቄዎች የተሟላ መረጃ አለማስቀመጣቸውን የተረዱ አይመስሉም።

በጥናቶቹ በዋነኝነት ተንፀባርቆ የተገኘው ችግር በተለይም ክዋኔን ለማጥናት የተነሱት ላይ በግልፅ እንደሚታየው። ይህም በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ክንውኖችን፣ የመከወኛ ቁሶችን እንዲሁም ሃይማኖታዊና ባህላዊ ድርጊቶችን እንዴት እንደሚከወኑ ከመንገር በዘለለ ትዕምርታዊ ፋይዳቸውን እንዲሁም አንድ ድርጊት ለምን እንደሚከወን አላሳዩም። ሞገስ ሚካኤል (2002) ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ለእያንዳንዱ ድርጊትና ክንውን ትርጉምና ፍቺ

የተለያዩ መረጃዎችን በመጠቀም አንድምታቸውን አሳይታል። በዚህም የተለየ ጥንካሬ አይቼበታለሁ።

በሁሉም አጥኝዎች ቁሶች፣ የሚች አልባሳት፣ ሚች በህይወት ዘመኑ የተጠቀመባቸው መገልገያዎች ለማስለቀሻ ይሆኑ ዘንድ የሚወጡ መሆናቸውን ቢናገሩም በአውዱ የተወጡትን ፋይዳ ጠለቅ ብሎም አንድምታቸውን በማሳየት በኩል ክፍተት ይታይባቸዋል።

ጥናቱ ከሌሎች ጥናት የለቅሶ ስርዓትን ትኩረት አድርገው ከተካሄዱ ጥናቶች ጋር የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔን በማንሳታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳስሎ አላቸው። ከዘላለም ኢዮብ፣ አየለ መሎሬና አስቴር አንጀሎ ጥናቶች ውስጥ የተገለፁት አንዳንድ ክንውኖች ምንም እንኳን ከተጠኘው ብሔረሰብ ጋር የቋንቋና የባህል ልዩነት ቢኖርም በጥናቶቹ የተገለፀው ስርዓቶች ለምሳሌ በግንዘት፣ በቀብር አፈፃፀም፣ የመከወኛ ቁሶች ወዘተ. በኩል ተመሳሳይነት አለው።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ቅኝት ከተደረገባቸው ጥናቶች ጋር ዝምድና ቢኖርም ልዩነትም እንዳለ እመኑ ነው። ይህ ጥናት የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና፣ የለቅሶ ስርዓትና የቀረርቶ ወይም የፉከራ ሁኔታን ካነሱት እንዲሁም የጀግና የለቅሶ ስርዓት ላይ ብቻ ካተኮሩት ጥናቶች ይለያል። ይሁንና የለቅሶ ሥርዓቱን በማየታቸው ከኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው።

በለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ ጥናቶች በክንውን ወቅት ስለሚወጡ ቁሶች እና ስለ ቀብር ስርዓት እንዲሁም ስለመታሰቢያ ዝግጅት (አርባ፣ ሰማኒያና መት አመት የመሳሰሉት) አንስተዋል። ይህ ጥናትም ስለመከወኛ ቁሶች ምንነትና ፋይዳ እንዲሁም ስለቀብር ስርዓት የሚያነሳ መሆኑ በያመሳስለውም ጥናቱ በተጠኚው ብሔረሰብ የመታሰቢያ ዝግጅት የሚባለውን ድህረ ቀብር ክንውን አይጨምርም። ይልቁንም በብሔረሰቡ ስልጣን ያላቸው ሰዎች ሲሞቱ ስልጣኑን የተረከበው ሰው የሚያደርገውን ከሀዘን የመንፃት ፕሮግራም ማጥናት አንዱ ትኩረት በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች ልዩ የሚያደርግ ነጥብ ነው።

በማህበረሰቡ የሚደረግ የለቅሶ ስነስርዓት ከተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች አንፃር እንዴት ይከወናል የሚለውም ሌላው የጥናቱ ትኩረት ነው። ሞገስ ሚካኤል፣ ንጉሴ አክሊሉና ወርቅነሽ ደምለው በጥናታቸው የጀግና ለቅሶ ክዋኔና የሚደረደሩ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች፣ ለጀግና ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞችና የጀግና ለቅሶ ግጥሞችን እንደ ቅደም ተከተላቸው አይተዋ። ከማህበራዊ ደረጃ ውስጥ ጀግንነት እንደ አንድ ነጥብ አንስተው

በማየታቸው ብንመሳሰልም የሚደረደሩ ግጥሞችን እንዲሁም የሚከወኑ ፉከራና ቀረርቶዎችን በጥልቀት የማልመለከት በመሆኑ እንለያያለን። ከዚህ ባለፈ ሌሎች ማህበራዊ ደረጃዎች (የጎሳ መሪ፣ ባለቃልቻ፣ ሀብታም፣ ድሃ፣ ወንድ ሴት፣ ህፃን፣ እናት፣ አባት፣ አዛውንት ወዘተ.) ሲሞቱ የለቅሶ ስርዓት ክንውኑ ምን እንደሚመስል ማሳየት ሌላው ተግባሬ በመሆኑ ልዩነት አለን።

3. ማህበረ ባህላዊ ዳራ ምልከታ

3.1 መልከዓምድራዊ ገጽታ

የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት የሰፈሩበት አካባቢ ቆላ፣ ደጋና ወይናደጋ በተሰኙ አየር ንብረቶች የተከፋፈለ ነው። በመኢኒት ሻሻ 15% ወይናደጋ 85% ቆላማ አየር ንብረት የሚገኝ መሆኑን በተጨማሪም ዓመታዊ የዝናብ መጠን 850 ሚ/ሊ፣ የሙቀት መጠን ከ29-33^{0}c የሚገኝ ሲሆን የወረዳው የቆዳ ስፋትም 277, 100 ሄ/ር መሆኑን ከወረዳው ያገኘሁት ያልታተመ ፅሁፍ ያስረዳል።

የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ 16,881 ሄ/ር የቆዳስፋት አለው። ዓመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን ዝቅተኛው 15.1^{0}ሴ ነው። ዓመታዊ የዝናብ መጠን ዝቅተኛው 400 ሚ/ሊ. እና ከፍተኛው 2000 ሚ.ሊ.ትር ሲሆን አየር ንብረቱም ደጋ 52% ወይናደጋ 5% ነው።የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ 16,881 ሄ/ር የቆዳስፋት አለው። ዓመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን ዝቅተኛው 15.1^{0}ሴ ከፍተኛው 27% ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠን ዝቅተኛው 400 ሚ/ሊ. እና ከፍተኛው 2000 ሚ.ሊ.ትር ሲሆን አየር ንብረቱም ደጋ 52% ወይናደጋ 5% ቆላ 43% እንደሆነ (በደ.ብ.ብሀ.ክ.መንግስት የልማት ጥናት ዶክመንት፤ 1999፣ 125) ይጠቁማል።

በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙ መኢኒቶች በመልከዓምድራዊ አቀማመጣቸው ሥያሜያቸውም እንደሚለያይ "The highland me'init are called Tishana and the law land me'init are called bodi and or Goldeya" (አወቀ፤ 2007፣110) ያስረዳል።

የብሔረሰቡ የቤት አሰራርም በአካባቢው እንደሚገኝ አየር ንብረት የተወሰነ ነው። በአብዛኛው ቁመቱ አጠር ያለና በስፋት ረገድም ጠበብያለ በአካባቢው ከሚገኝ እንጨት ተሰርቶ በሳር ወይም በገለባ የሚሸፈን ነው።አያይዞም ቤት የመስራት ድርሻ የሴቶች መሆኑን (የደ.ብ.ብ.ሕ.ፕሮፋይል፤ 2001፣65) ያስርዳል።

3.2 ቋንቋ

የመኢኒት ብሔረሰብ ቋንቋ መኢንተኛ በመባል ይታወቃል። "ብሔረሰቡ "መኢንትኛ" ቋንቋን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ይናገራል።" (የደ.ብ.ብ.ህ.ፕሮፋይል፤ 2001፣65) "መኢኒትኛ" የተሰኘው ቋንቋ ቦዲ እና ትሸና የተሰኙ ሁለት ነገር ግን በእጅጉ የተቀራረቡ ዘየጮች አሉት

ቋንቋው በአባይ ሰሀራዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ እና በቤንች ማጂ ዞን ከሚነገሩ የሱርሚክ ቋንቋዎች መካከል አንዱ መሆኑን (Abbink, 1988:78፣ 1991:4) ያስረዳሉ። በተመሳሳይ "... *The language of me'init belongs to east Sudanic nailo Saharan language, especfically to the south east surmic language sub family with surma zilimamo or bale mursi, muguji and kawegu" (አወቀ፣2007፣110)*

በሚል ስለብሔረሰቡ የቋንቋ ቤተሰብ የተገለፀውን መረጃ እናገኛለን። (የደ.ብ.ብ.ህ.ፕሮፋይል 2001፣65)። ሞገስ 1995ን ዋቢ በማድረግም ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መረጃ አስፍሯል። በተጨማሪም ሱርማ፣ ሙርሲ፣ ባሌሲና ካውጉ ብሄረሰቦች ጋር እርስ በእርስ ለመግባባት እንደሚችሉና በርካታ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶቻቸው ተመሳሳይነት እንዳላቸው አያይዞ ያስረዳል።

ለቋንቋው በአሁኑ ሰዓት የራሱ ፊደል እንዲኖረው ለማስቻል የተለያዩ ጥናቶችና የሙከራ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

3.3 የመኢኒት ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር

በዚህ ንዑስ ርዕስ የመኢኒት ብሔረሰብ አመጣጥ (origin) እና አሰፋፈሩን በተመለከተ መግለጫዎች የሚቀርቡበት ነው። መረጃዎች የተገኙት ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ከሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላት፣ከተለያዩ በብሔረሰቡ ላይ ከተጠኑ ጥናቶች እንዲሁም ከተለያዩ መጻህፍት ነው።

እንደ ብሔረሰቡ አባላት አገላለፅ "መኢኒት" የሚለው ቃል ሰው ነኝ ማለት ነው። ይህ ስያሜ የመጣው ደግሞ ከብኔረሸቡ አመጣጥና ከአሰፋፈሩ ጋር ተያይዞ ነው። የመኢኒት ብሔረሰብ አመጣጥን አስመልክቶ የብሔረሰቡ አባላት በመጀመሪያ ፈልሰው የመጡት ከጎረቤት ሀገር ኬንያ ነው የሚል አፈታሪክ መኖሩን ይሁንና በውል ተመርምሮና ታውቆ የተቀመጠ መረጃ አለመኖሩን (ዳንኤል፣1984፣2) ይጠቁማል። በሌላ በኩል ጥንት የኦሞ ወንዝን ተሻግሮ "ቱሉም" በሚባል የቤንች ማጂ ዞን እንደሰፈረ በብሔረሰቡ ታሪክ አዋቂ አዛውንቶች የሚነገር ትውፊት አለ። የብሔረሰቡን ጥንት አመጣጥ እና አሰፋፈር አቶ ታቶ ማርደሮ የተባሉ የጎማ ቀበሌ ነዋሪ ያሉትን እንመልከት፡-

ከቅድመ አያቶቻችን እንደሰማነው ብሔረሰቡ ፊልሶ የመጣው ከደቡብ አሞ ቆጫ ከሚባል ቦታ ወይም ከደቡብ አሞ ወንዝ አካባቢ ነው። እኛ ስንመጣ እዛው አካባቢ በብሔረሰቡ አጠራር ችሪም የሚባል ጎሳ አለ። ከወንዝ ማዶ እንደገና ደግሞ መላ የሚባሉና እስከአሁንም መኢንተኛ የሚናገሩ አሉ። (14/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)

"መኢንት" ማለትም "ሰውነኝ" ማለት ነው። ይህ ስያሜ ደግሞ በድሮ ጊዜ ፊልሰን ከመጣንበት ከአሞ ወንዝ አካባቢ ሰዎች እኛን እንደሰው አያዩንም ነበር ለዛም ነው ይህ ስያሜ ለራሳችን የሰጠነው። የሚል ምላሽ ከተለያዩ መረጃ አቀባዮቼ አግኝቻለሁ። በአሁኑ ጊዜ የመኢኒት ብሔረሰብ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ አስራሦስት ዞኖች መካከል አንዱ በሆነው በቤንች ማጂ ዞን ሰፍሮ ይገኛል። የቤንች ማጂ ዞን በደቡብ ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ አስራሦስት ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን በሰሜን ከሸኮ ዞን፣ በደቡብ ከኬንያ፣ በምዕራብ ከሱዳንና በምስራቅ ከከፋ ዞን ጋር ይዋሰናል። በዞኑ ቤንች፣ ዲዚ፣ መኢኒት፣ ሸኮ፣ ሱርማና ዝልማሙ (ባሌ) የተሰኙ ስድስት ብሔረሰቦች ይኖራሉ። (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል፤ 64፣2001)

ከላይ እንደተመለከተው የመኢኒት ብሔረሰብ በቤንች ማጂ ዞን ከሚገኙ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው። በብሔረሰቡ የዞኑ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ክፍል በመያዝ በአብዛኛው መኢኒት ሻሻና መኢኒት ጎልድያ በተሰኙ ሁለት ወረዳዎች ሰፍሮ ይገኛል (አወቀ፤2007፣110)፣ (የደ.ብ.ብ.ህ.ፕሮፋይል፤ 2001፣65)። ከተጠቀሱት ሁለት ወረዳዎች በተጨማሪ በተወሰነ ደረጃ በከፋ ዞን፣ በዴቻ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ በርካታ መንደሮች ይገኛሉ።

ብሔረሰቡ በዋነኛነት በሚኖርባቸው ወረዳዎች ውስጥ የከፍኞ፣ የቤንችና የአማራ ማህበረሰብ አባላት በተለያዩ መጠን ከብሔረሰቡ ጋር በስብጥር ይኖራሉ። በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት የብሔረሰቡ ህዝብ ብዛት 151.489 መሆኑን (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይ፤ 2001፣65) ይጠቁማ። በሌላ በኩል በብሔረሰቡ በዋነኛነት በሰፈረባቸው በመኢኒት ጎልድያ 89, 481 እና በመኢኒት ሻሻ ደግሞ 35, 264 እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች፡- በድሬዳዋ፣ በሱማሌ በሀረርና በአፋር ክልል በተለያዩ ቦታዎች የሰፈሩ እንዳሉ በመጠቆም በአጠቃላይ የብሔረሰቡ ህዝብ ብዛት 15, 568 የሚገመት መሆኑን የሚያሳየው ከመኢኒት ጉልድያ ባህልና ማስታወቂያ የተገኘው ያልታተመ መረጃ ነው።

ለጥናቱ የተመረጡት ሁለት ወረዳዎች ከአዲስ አበባና ከክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ ያላቸውን ርቀት ስንመለከት መኢኒት ጎልድያ ከሀዋሳ 915 ኪ.ሜ ላይ ይገኛል። ከአዲስ አበባ ደግሞ

645.28 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። መኢኒት ሻሻ ወረዳ 945 ኪ.ሜትር ከሀዋሳ እንዲሁም 675.28 ኪ.ሜ ከአዲስ አበባ ርቀት ላይ ይገኛል።

የመኢኒት ብሔረሰብ በሰሜን ቤንች፣ በምዕራብ ሸኮ በደቡብ ማጂ (ዲዚ) እና ካውጉ፣ በምስራቅ ደግሞ ናያ ባስኬቶና ጨራ ያዋስኑታል። በብሔረሰቡ ሻልሺ፣ ማጂና፣ ለማ፣ኮያ፣ ጋርዎ፣ ደንጋ፣ ጆና፣ ቦሊ፣ ጊስማሮ እና ኩታ በመባል የሚታወቁ አቢይ ጎሳዎች ሲኖሩ በእነዚህ ጎሳዎች ስር ንኡሳን ጎሳዎች የሚገኙ መሆኑን (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል ፤ 2001፣65) ያስረዳል። በብሔረሰቡ በአጠቃላይ የሚገኙ ጎሳዎችን ቁጥር አስመልክቶ ከመኢኒት ጎልድያ ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ከ64 የሚበልጡ መሆናቸውን ያሳያል።

3.4 የኢኮኖሚ መሠረት

ለጥናት የተመረጡት ብሔረሰቡ በዋናነት በሰፈረባቸው ወረዳዎች አየር ንብረት ደጋ፣ ወይናደጋ፣ ቆላ መሆኑን ከየወረዳዎቹ የተገኙ የፅሁፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት ከአያሌ አመታት በፊት አሁን ወደሰፈሩባቸው አካባቢዎች ከመምጣታቸው በፊት በዋነኛነት መተዳደሪያቸው ከብት እርባታ ሲሆን ቀስ በቀስ ባደረጓቸው እንቅስቃሴዎች አሁን በሰፈሩበት አካባቢ መኖር ከጀመሩ በኋላ ግን የእርሻ ስራን ዋና የገቢ ምንጭ በማድረግ ኑሯቸውን መምራት እንደጀመሩ (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል፤ 2001፣65) ያስረዳ ል። ይህን የኢኮኖሚ ምንጭ ለውጥ አስመልክቶ በምክንያትነት የቀረበውን ስንመለከት

> *In the past the me'nit were cattle herding people. As me'nit oral tradition syas tsetse fly killed all their cattle in the 19th century; so they were forced to shift to cultivation, currently the me'init are shifting caltivators. (አወቀ፤ 2007፣111)*

ጥቅሱ የመኢኒት ብሔረሰብ የኢኮኖሚ መሠረት ከከብት እርባታ ወደ እርሻ ስራ በምን ምክንያት እንደተለወጠ ያሳያል። ይሁን እና በብሔረሰቡ አሁንም ድረስ የብዙ ከብቶች ባለቤት መሆን የሀብት መመዘኛ ነው። በአጠቃላይም ከብቶችን ከማህበራዊ አኗኗራቸውና ከባህላቸው ጋር በተቆራኘ የኢኮኖሚ አቋማቸውን የሚያዩበት ነው። ከዚህ ባለፈ "... የህይወታቸው ጠንካራ መሠረት አድርገው የሚቆጥሩበት ከጥንት ጀምሮ በቆየው ከብት የመውደዱ ልማድ አላቸው። ብሔረሰቡ ከብቶችን ለጥሎሽ፣ ለሀዘን፣ ለአምልኮአዊ እርድ፣ ለካሳ ክፍያ፣ ለሀብት መለኪያና ማህበራዊ ከበሬታን ለማጎናፀፍ እንዲሁም ለምግብነት ስጋን

ይጠቀማሉ።" (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል፤ 2001፣65) ይህን ሀሳብ አስመልክቶ "Livestock ... symbolic significance is highly valued by the me'enit." (አወቀ፤ 2007፣110) በማለት ያስረዳል። በዚህም ብሔረሰቡ ከእርሻ ሥራ ጎን ለጎን የከብት እርባታን ከሚያካሂዱበት ምክንያት አንዱን ጠቅሷል። ይሁን እንጂ "some clans do not eat chicken, sheep and antolopes because, they believes, these will shed their teeth" (አወቀ፤ 2007፣111) በማለት አንዳንድ ጎሳዎች ስጋ የማይበሉ መሆናቸውን ጠቁሟል። ይህም የእውነተኛ መኢኒቶች መገለጫ መሆኑ በጎሳዎቹ ዘንድ ይታመንበታል።

ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ በዋና የገቢ ምንጭነት የሚያገለግለው የእርሻ ሥራ ነው። የእርሻ ሥራዎችን የሚያከናውኑት ቦታ በመቀያየር በብሔረሰቡ አጠራር "ወሌ" በተሰኘ የመቆፈሪያ መሳሪያ ነው።" (ዳንኤል፤ 1984፣4) በበሬ ማረስ ቢጀመርም እጅግም ያልተለመደ መሆኑን (አወቀ፤ 2007፣111) ሲገልፅ በዚህም የተነሳ በአካባቢው በሰፈሩ አማሮች "እንደ ኋላቀር" እንቆጠራለን ብለው እንደሚያስቡ (Abbink, 1991:6) ገልፀዋል። ይሁን እንጂ በብሔረሰቡ ገብስ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ ቅመማ ቅመም፣ ጎመን፣ ቡና፣ ሽንኩርትና ማር ለቤት ውስጥ ፍጆታና አልፎ አልፎም ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች መሆናቸውን (አወቀ፤ 2007፣111) እና (Abbink, 1991:6) በስፋት ገልፀዋል።

3.5 የአለባበስና የአመጋገብ ሥርዓት

የመኢኒት ብሔረሰብ የባህል መገለጫ የሆኑ አልባሳትና የምግብ አይነቶች አሉት። ብሔረሰቡ በማንነቱን መገለጫ ምግቦችን አዘጋጅቶ ይመገባል። አልባሳቱንም ሰርቶ እና ሸምኖ ይለብሳል።

3.5.1 የአለባበስ ሥርዓት

ባህል የሚለወጥ የሚሻሻል ጭራሹንም የሚጠፋበት ጊዜ አለ። በብሔረሰቡ አለባበስ ላይም የምናስተውለው ይህንኑ ነው።

> *... ቀድሞ ጊዜ ለልብስነት የሚጠቀሙት የእንጨት ቅርፊ፣ የከብት ቆዳ፣ የዱር አራዊት በተለይም የሚዳቋ ቆዳን በማለስለስ ለልብስነት ይጠቀሙ ነበር። ሴቶቹ ደግሞ በብሄረሰቡ አጠራር `ቤልሽት` ከተባለ የእንጨት ልጥ በመሳጥ በቀጫጭን ገምደው ይሸነሽኑትና በሀፍረተ ሰጋቸው ትክክል ከፊት ለፊት ወገባቸው ላይ*

ያስፋታል። ከኋላ ግን ምንም የሚሸፈን ነገር የለም። በአሁኑ ጊዜ ግን ከሌላ አካባቢ ከመጡ ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ሳቢያ ትምህርት በመቅሰም አቡጀዲ ጨርቅን አገልድመው ከላይ ራቁት በመሆን ይስተዋላሉ (ዳንኤል፤ 1984፣5)።

ይህ የቀድሞ አለባበስ ለውጥ በአሁኑ ጊዜም በለውጥ ሂደት ውስጥ ይገኛል። እንደቀድሞው ሁሉ ከአካባቢው ቁሶችና ከቆዳ የተሰሩ ልብሶች እየቀሩ በምትካቸው "ቲሸርት" እና የአቡጀዲ ግልድም ተተክቷል። በተለያዩ ቀበሌ ማህበራት እንዲሁም በገበያ ቀናት በተዘዋወርኩበት ወቅትም ያርጋገጥኩት ይህንኑ ነው።

"me'en have not escaped the impact of Amhara material culture and customs in aeed several me'en have clear arpirations of becoming like the amhara and have guicuny adopted clothing new crops tools of other material items. (Abbink, 1991:7) በብሔረሰቡ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ያደረጉት እኒህ ምሁር እንደሚያስረዱት የመኢኒት ብሔረሰብ ከአለባበስ እና ከአጋጌጥ በተጨማሪ በተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችም ለውጥ እንዳሳየ ይገልፃሉ። ነገር ግን መኢኒቶች ጥንት ከተለያዩ የእንጨት ቅርፊቶች ከቆዳ፣ ከሳር እና ከመሳሰሉት አልባሳትን በመስራት ይገለገሉ ነበር። መጫሚያቸውን ከጎሽ ቆዳ የተሰራ ሰንደል ጫማ ያደርጋሉ። (የደ.ብ.ብ.ህ.ፕሮፋይል፤ 2001፣68) መኢኒቶች ልብሳቸውን ብቻ ሳይሆን ጌጣጌጦችን ከተለያዩ ቁሳቁሶች በመስራት ያጌጣሉ። አጋጌጣቸው የየግለሰቦችን ማህበራዊ ደረጃም የሚያንፀባርቅ ነው።

ክንዳቸው ላይ የቀጭኔ ጭራ ያስራሉ። ወገባቸውን "ክኤራ" በተሰኘ የእንጨት ሚደ ያበጥራሉ። አዳኞች የተለያዩ እንስሳት አጥንትና ጥርስ ወይም ጎፈር ለጀግንነታቸው መለያነት ያደርጋሉ። ወንዶች ለመቀመጫነት፣ ሲደክማቸውም አረፍ ለማለት እና ለትራስነት እንዲሆናቸው መቻካም በመያዝ ይንቀሳቀሳሉ። ልጃገረዶች "ጀመብላች" የተባለ ክዳቃ፣ ክብረት፣ ክመደብ፣ ክቆዳ የተሠራ አልባሳት ይለብሳሉ። (የደ.ብ.ብ.ህ.ፕሮፋይል፤ 2001፣65)።

የመኢኒት ብሔረሰብ አባል የሆኑ ወጣቶችም ይሁኑ በእድሜ ከፍያሉ በፀጉር አቆራረጥ ስልታቸው የተለያዩ ቅርፆችን በማስያዝ ይቆረጣሉ። እንዲሁም ሹሩባ የመሰራት ባህልም አላቸው።

በመኢኒት ወንድም ሆነ ሴት እንደ አስፈላጊነቱ ፀጉራቸውን ስሩን በመከርከም ሹሩባ ይሰራሉ። ለጋብቻ የታጨች ልጃገረድም ቅቤና አፈር በመቀላቀል ትቀባለች አምባርና ወሌ በማድረግ ደማቅና የሚያብለጨልጭ ጥላሸት በመቀባት ትዋባለች። የተለያዩ ብረቶችን በራሳቸው በጀርአቸውና በእግራቸው ላይ በማድረግ ይዋባሉ። (ዳንኤል፤ 1984፣6)።

3.5.2 የአመጋገብ ሥርዓት

በብሔረሰቡ የሚታወቁ ባህላዊ ምግቦች ከተለያዩ አዝዕርት እና አትክልቶች ይዘጋጃሉ። ለምግብነት በመዋል ደረጃ በቆሎና ማሽላን የሚስተካከል የለም። እኒህ የአገዳ እህሎች ለተለያዩ ምግቦች ዝግጅት ያገለግላሉ። ለምሳሌ ያህልም ገንፎ፣ ቂጣ፣ በበሶ መልክ የሚዘጋጁ ምግቦች ተጠቃሽ ናቸው።ምግብ በማዘጋጀት በኩል ሴቶች ትልቅ ሚና አላቸው።

> *በአመጋገብ ረገድ ብሔረሰቡ ከእህል፣ ከቅጠላቅጠል እና ከሥራ ሥር የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት ይጠቀማል። ከተለያዩ የእህል ዘሮች በሴቶች አማካኝነት ተወቅጦና በድንጋይ ወፍጮ ተፈጭቶ ገንፎ ተገንፍቶ ይበላል። ከእንሰት ተክል ቆጮ በማዘጋጀት ሲጠቀሙ ከባህላዊ መጠጣቸው ደግሞ "ሻሌ" ቦርዴ ወይም ጠላ ተጠቃሽ ነው። (የደ.ብ.ብ.ህ ፕሮፋይል፣ 2002፣68)*

መኢኒቶች ለምግቦቻቸው ማባያነት ጎመን እና ጥሬ ወተትን ይጠቀማሉ። በብሔረሰቡ ስጋ የሚበላው ተጠብሶ ወይም ተቀቅሎ እንጂ ጥሬ ስጋ አይበላም። ከእንስሳት ሁሉ ግን የበግ ስጋ ጭራሹን እንደማይበላና ቆዳውም ለመቀመጫነት የማያገለግል መሆኑን ለዚህም ምክንያቱ "ቃልቻ ይከለክላል" የሚል መሆኑን (ዳንኤል፣ 1984፣4) ባካሄደው ጥናት ገልጿል። ነገር ግን በምልከታ ያረጋገጥኩት ከዚህ የተለየ ነው። በግ ለእርቅ ማስፈፀሚያነት የሚያገለግል ስጋውም እንደ እርቁ ሁኔታ ወይም አይነት የሚበላበትና የማይበላበት አጋጣሚ መኖሩን ነው። ይህንም አቶ በድሉ ካሳ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *በሌላ ወገን ለምሳሌ ከገዳሙት ውጪ በሆነ ምክንያት በተከሰተ ወገ ላይ የእርቁ ስርዓት በሬና በግ በድንጋይ ተቀጥቅጦ ይገደልና ስጋው ይበላል። በውርስ ጋብቻ ላይ የተወረሰችው ሴት የሚያገባት ሰው በቁብ ፍየል ወይም በቁብ በግ ደም ያጥባታል። ስጋውን ከአጣቢውና ከታጣቢዋ ወገን ውጭ የሆኑ ሰዎች ይበላሉ። በጓ ወይም ፍየሏ የምትገደለው በዱላ ተቀጥቅጣ ነው። በገዳሙት የሚፈጠር ወገ ደግሞ በድንጋይ ተቀጥቅጦ በተገደለ በግ ደም ሴቷ ትታጠብና የመንፃት ስርዓቱ ይፈፀምለታል። ስጋው ግን አይበላም። ምክያቱም ስጋው ላይ የታጣቢዋ ሀጢያት አርፏል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ነገር ግን ባለቃልቻዎች የበግ ስጋ አይበሉም።* (15/08/2003 ባቹማ ቀበሌ) በማለት ገልፀዋል።

የብሔረሰቡን ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች አስመልክተው ከላይ የተገለፁት መረጃ አቀባይ የበቆሎ ገንፎ፣ ከበቆሎና ከአደንዛሬ የሚዘጋጅ ንፍሮ የሚዘወተር ሲሆን በማባያነትም ጎመን ወተትና ሥጋን የሚጠቀሙ መሆናቸውን እንዲሁም ከበቆሎ የሚዘጋጅ "በጢስ" የሚሰኝ ምግብ እንደሚያዘጋጁ ገልፀውልኛል። በመጠጥ በኩልም ቦርዴ የሚሰኝ ከበቆሎ የሚዘጋጅ፣ "ጮንቃ" ወይም ሻሜታ፣ ከማር የሚሰራ "በኬ" እንዲሁም "ቡንጡላ" ወይም ጨሞ የተሰኙ

ባህላዊ መጠጦችን ለዘወትር እና ለተለያዩ በዓላት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች አዘጋጅተው የሚጠቀሙ መሆኑን ነግረውኛል።

3.6 የዕደጥበብ ሙያና ሙያተኞች

"... The me'en are self sufficient in the production of almost all of these material objects. Among the me'en there is no dependence on other people for material goods ..." (Abbink, 1999:35) በጥቅሱ እንደተመለከተው መኢኒቶች የተለያዩ የዕደጥበብ ውጤቶችን በማምረት ከጥገኝነት የተላቀቁ መሆናቸውን እንረዳለን። በዚህም የብሔረሰቡ አባለት ከአካባቢው በሚገኙ ጥሬ እቃዎች የተለያዩ ባህላዊ መሳሪያዎችን ይሰራሉ። ከእነዚህም መካከል "የብረት ማዕድን ቆፍሮ በማውጣትና በማንጠር "ጎደታ" ወይም መቆፈሪያ፣ "ወደ" ወይንም ማጭድ፣ "ወራ" ወይንም ቆንጨራ እና የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን በመስራት ይጠቅማሉ። ከሸክላ፣ ከሰንደዶ፣ ከቀንድ፣ ከቅልና ከተለያዩ እንጨቶች ለተለያዩ ግልጋሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን ይሰራሉ።" (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል፣ 2001፣68)

በመኢኒት ብሔረሰብ የተለያዩ የዕደጥበብ ውጤቶችን ላቅ ባለሁኔታ የሚሰሩ የእጅ ባለሙያዎች በእጅጉ ይገለላሉ። ከእነዚህ ሰዎች ጋር በጋብቻም ይሁን በሌላ አይነት ማህበራዊ አጋጣሚ ግንኙነት አይፈጥሩም። ይህ ደግሞ በአብዛኛው ማህበረሰቡና ባህል እንደሚታመነው "ሰው ይበላሉ" ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ሰው ሲሞት ለሦስት ወራት ያህል በመቃብሩ ላይ መጠበቂያ ቤት ተሰርቶ ጥበቃ ይደረጋል። ምክንያቱም እኒህ ሙያተኞች በሟች መቃብር አካባቢ ሄደው ሟችን በማሞገስና በማሞካሸት "አስነስተው" ይወስዱና ይበሉታል የሚል እምነት በመኖሩ መሆኑን የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል።

3.7 ማህበራዊ ህይወት

3.7.1 የጋብቻ ሥርዓት

በብሔረሰቡ ሦስት አይነት የጋብቻ ሁኔታዎች አሉ። እነሱም በቤተሰብ መካከል በሚፈጠር ስምምነት የሚከናወን ጋብቻ ወይም "ጋመን" በጠለፋ የሚፈፀም ጋብቻ ወይም "ቀረን ጎርቤት" የውርስ ጋብቻ ወይም "ቀነስኤ" ናቸው። አንድ ሰው (ወንድ)በነዚህ የጋብቻ

ሁኔታዎች እንደ ሀብትና ንብረቱ መጠን ብዙ ሚስቶች ማግባት የሚችልበት ሁኔታ አለ (አወቀ፤ 2007፣111)። የጋብቻ አፈፃፀም ሁኔታዎችን አስመልክቶ የተቀመጡ መረጃዎች የሚሉትን እንመልከት፡-

> *በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ለሴቷ ቤተሰብ ወንዱ ከ7-12 ከብቶች እንዲሁም ለመሸራዋ እስከ 500 ብር ጥሎሽ ይሰጣል። አግቢውና የአግቢው ቤተሰብ አቅም ካላቸው የጥሎሽ መጠን ከ15-30 ከብት ሊደርስ ይችላል። በጠለፋ ለሚፈፀም ጋብቻ የጠለፋው ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ሽማግሌዎች ከልጅቷ ቤተሰብ ጋር ተነጋግረው ስምምነት ላይ ከደረሱ ሁለት ከብት ጥሎሽ እንዲሰጥ ያደርጋል። ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ ተጨማሪ ከብት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ። ሦስተኛው የጋብቻ አይነት የውርስ ጋብቻ ነው። እንዲህ አይነቱ ጋብቻ የሚፈፀመው ታላቅ ወንድም በሞት ሲለይ ታናሽ የታላቁን ሚስት እና ሀብት በመውረስ ልጆችን እንዲንከባከብና ሌላ ባዕድ ገብቶ በሚች ሀብትና ንብረት እንዳይጠቀም ለመከላከል ታስቦ የሚፈፀም ነው። በብሔረሰቡ ወንድ ልጅ ለጥሎሽ የሚሆን በቂ ከብት ካለውና ሀብታም ከሆነ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይችላል (የደ.ብ.ብ.ሀ.ፕሮፋይል፤ 2001፣67)።*

የብሔረሰቡ የኑሮ ሁኔታና የአኗኗር ዘይቤ በጋብቻ ህይወታቸው ላይ የሚያመጣው ለውጥ መኖሩንና ይህን ለውጥ በምን መልኩ እንደሚያስተናግዱት ለመረዳት ያስችል ዘንድ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፡-

> *Because of their geographic mobility, the me'init has dispersed settlements. In each dispersed settlement each family (man his wife/wever and children) has separate compound with many huts. The compound of each family is in most cases, chosenclose to the ancestrah area or in arineage territory. On the other hand, marriage with other lineage groups, duits enables to establish socio-economic ties and alliance between different lineag groups. (አወቀ፤ 2007፣112)*

አንድ የመኢኒት ወንድ እድሜውና ሀብቱ እስከፈቀደ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይችላል። በሚስቶቹ መካከል የመናናቅና የመቀናናት መንፈስ የለም። ይልቁንም ሴቶቹ አንድ ሰው በባለቤትነት እንዳገባቸው በግልጽ እያወቁ በእርሻ ቦታቸው በአንድ ላይ ሆነው በመቆፈር፤ በማረም ሌላም ስራ በመስራትና በመተጋገዝ ተፈቃቅረውና ተከባብረው በአንድነት ይኖራሉ።

አባወራው በተለያዩ ምክንያቶች ተጨማሪ ሚስት ሊያገባም ይችላል። ከነዚህ ምክንያቶች መካከል የቀድሞ ሚስቱ መሀን የሆነች እንደሆነ ነው። ይህች ሴት መሀን መሆኗ ከተረጋገጠ በማህበረሰቡ ከፍተኛ የሆነ ልጅ የመውለድ ፍላጎት በመኖሩ ባሏ የጥሎሽ ከብትና ብር ባይኖረውም ለእሷ የተጣለላትን ከቤተሰቦቿ በመውሰድ ሌላ ሚስት እንዲያገባ ታደርጋለች።

ሌላው ምክንያት ደግሞ የሚስት እድሜ ነው። እማወራዋ ካረጀች ባሏ ሌላ ወጣት ሚስት እንዲያገባ ታደርጋለች። ለትዳር ትሆነዋለች ብላ የመረጠቻትን ሴት ቢቻል በስምምነት ካልተቻለ ደግሞ በኂይል (በማስጠለፍ) ለባሏ ትድርለታለች። ከዚህ በኋላ ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት (በጠለፋ ከተፈፀመ) ሽማግሌ ተልኮ የጥሎሽ ከብት ተጥሎ ትዳሩ እውን እንዲሆን የራሷን ሚና ትጫወታለች። ቀደም ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሚስቶች መካከል የሚፈጠር አሉታዊ ስሜት የለም። ይልቁንም ባል ሚስቶቹ ጋር የሚሄደው በየተራ በመሆኑ ለባለተራዋ ሚስት ሌሎቹ ስራ በመስራት (ቤት በማፅዳት፣ ውሃ በመቅዳት ወዘተ) ያግዟታል።

በብሔረሰቡ የጋብቻ ሥርዓት አንድሰው አባል በምንም መልኩ ከራሱ ጎሳ ማግባት አይችለም።በባህሉም አይፈቀድም። እንዲያውም ለጋብቻ የተመረጠችውን ልጅ ከማወቅ ቀጥሎ የመጀመሪያው ጥያቄ የማን ጎሳ አባል መሆኗን ማጣራት ነው። "እኛ ሰዎች ነን ሰው እንዴት እህቱን ወይም ወንድሙን ያገባል; የጎሳችንን አባል እንደ እህትና ወንድማችን ነው የምንቆጥረው። በርግጥ የሌሎች ጎሳ አባላትም እናከብራን አንንቅም። ለጋብቻ ግን ከእኛ ጎሳ አባል ውጭ የሆነ ሰውን ነው የምንመርጠው።" (አቢያ ኬሬሌጁ 20/08/2003 ዓ.ም ሻሻ) ይህንን ሀሳብ የተለያ መረጃ አቀባዮቹም ያረጋገጡት ነገር ነው።

3.7.2 ጥርስ ነቀላ (ኬት)

ይህ ሥርዓት ማህበራዊ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና አለው። በዚህ አጋጣሚ ወጣቶች የመተዋወቅና የመተጫጨት እድል የሚፈጠርበት በመሆኑ በእጅጉ የሚናፈቅና በድምቀት የሚከበር በዓል ነው።

የጥርስ ማውለቅ ስርዓቱ የሚካሄደው ለሁለቱም ፆታ ነው። አንዲት ሴት ጥርሷ የሚወልቅበት ከዚህ እስከ እዚህ ባለው የዕድሜ ክልል ተብሎ ሳይሆን የሰውነት ለውጧን መሠረት በማድረግ ነው። ይህም በሰውነት መዳበር፣ የጡት ማጎጥጎጥና ሌላም የወጣትነት ፀባይ ማሳየትን ተከትሎ ነው።

> *የወጣቷ አባል መዳበር ለጋብቻ መድረሷን ይገልፃል የሚል አመለካከት ስላለ፣ ቤተሰቧ ክጥንት በወረሱት ባህል መሠረት ልጃችን ለትዳር ደርሳለች በሚል ሁለት የፊት ጥርሶቿን (የታችኛውን) በባህላዊ መሳሪያ ያስነቅላሉ። በዚህ ጊዜ ብዙ ደም ይፈሳታል። ነገር ግን ጨርቅና የተለያዩ ቅጠሎችን በአሳት እያቃጠሉ ቁስሉን በመተኮስ ደሙን ያቆሙታል። ልጅቷም የቁስሉ ስሜት ስለሚሰማት አፏን ገጥማ*

ትቆያለች። እንጂ ለማናገርም ሆነ ለመዝፈን አትችልም። ይሁንና በወቅቱ የሚካሄደው የጓደኞቿ ጭፈራና ለጋብቻ መድረሷ ... ስነልቦናዊ ርካታን ስለሚሰጣት የቱሰሉን ህመም በመጠኑ በመርሳት ስቃዩ ይቀልላታል። ... ስርዓቱ ሰብል መሰብሰቢያ ወቅቶች ላይ ይከናወናል (ዳንኤል፣ 1984፣22)።

በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚ ጥርሷ የሚነቀልላት ወጣት ለትዳር መድረስ፣ ከልጅነት ኃላፊነትን ወደመሸከም የተሸጋገረች መሆኑ የሚገለፅበት እንዲሁም ለስርዓቱ ማድመቂያነት የተለያዩ ወጣቶች ባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ የሚያካሂዱበት ነው። ለስርዓቱ ማስፈፀሚያነት የሚዘጋጀው መጠጥ በብዛረሰቡ ተወዳጅነት ያለውና ከበቆሎ የሚዘጋጀው "ሻሌ" የተሰኘው መጠጥ ነው። በበዓሉ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎች ተወስነውና ተመርጠው አይጠሩም። ነገር ግን በአካባቢው ድግስ መኖሩን ያወቁ ሁሉ መሳተፍ ይችላሉ። በዚህም የልጅቷን ወግ ማዕረግ በዘፈንና በጭፈራ ያጅቡታል።

እንደ ሴቶቹ ሁሉ የወንዶችም ጥርስ ነቀላ በከፍተኛ ድግስ ይታጀባል። የስርዓቱ አፈፃፀም የወጣቱን የሰውነት ለውጥ መሰረት ያደረገ ነው።

ይህን ስርዓት መከወን የወጣቶቹን ለኃላፊነትና ለትዳር መድረስ ከማሳየት የዘለለ አላማም እንዳለው የተለያዩ መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል። ይህንኑ አስመልክተው አቶ ብርሃኑ ቸኮባ ሰው ሲታመም ምግብ የመብላት ፍላጎትና አቅም ላይኖረው ይችላል። በዚህ ጊዜ ሲሞትብን ይችላል። ነገር ግን ጥርሱ የተነቀለ እንደሆነ ማርና ወተት በመቀላቀል በሽምበቆ አድርገን በወለቀው ጥርሱ በኩል ወደጉሮሮው እንዲገባ እናደርጋለን። በዚህ ሰዓትም ብርታት ያገኛል። (12/08/2003 ባቹማ) በማለት ገልፀውልኛል።

3.7.3 የለቅሶ ሥርዓት (ሮዋ)

በመኢኒት ብሔረሰብ ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው አጋጣሚዎች መካከል የለቅሶ ሥርዓት አነዱና ዋነኛው ነው።በብሔረሰቡ ባህል መሠረት የለቅሶ የሚከናወነው የሟችን ማለሰብ ማህበራዊ ስለጣንና እድሜ መሠረት በማድረግ ነው። በዚህ መሠረት አዋቂ ሲሞት የሚከወን የለቅሶ ሥርዓት በህፃናት ሞት ላይ ወይም በወጣቶች አይታይም። በመሆኑም አዋቂ ወይም ትልቅ ሰው ሲሞት የቀብር ሥርዓቱ ከፍተኛ ድግስ ተደግሶ እየተበላና እየተጠጣ ይካሄዳል። ለስርዓቱ ማስፈፀሚያነት እና የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለማስኬጃ ከሌሎች አጋጣሚዎች ከሚደረገው በተለየ መልኩ በድንጋይ ተቀጠቀጦ በሬ፣ኮርማና ጥጃ ይገደላል። ስጋውንም ለቀስተኛው (ሀዘንተኛው) እየበላ ሀዘኑን ይገልፃል። ይህንንም (አወቀ፣

2007፣113)፣ (የደ.ብ.ብ.ህ. ፕሮፋይል፤2001፣69ይገልፃል። የለቅሶ ሥርዓቱ የሚከናወነው በዘፈን ነው። ለማድመቂያነትም የተለያዩ ቁሶችን ይጠቀማሉ። ከነዚህ ቁሶች ውስጥ በእግር የሚደረግ ቃጭል፣ ጡሩንባ ወዘተ. ይጠቀሳሉ።

የአዋቂ(የእድሜ ባለጸጋዎች)፣ ኮሙሩትና ኔሬይ የቀብር ሥርዓታቸው የሚፈፀመው በድንጋይ ተቀጥቅጦ በተገደለ የበሬ ቆዳ አስክሬኑ ከተከፈነ በኋላ ነው። ህፃናት ሲሞቱ ደግሞ በልብስ ይከፈናሉ።

3.8 እምነት

የመኢኒት ብሔረሰብ "ኔሬይ" በሚል የሚጠራ እምነትንያምናሉ። ቃልቻ ወይም በብሔረሰቡ አጠራር "ኔሬይ" በብሔረሰቡ እምነት መሠረት "ከድርቅ፣ ከፀብ፣ ከወረርሽኝና ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ አደጋዎች በመጠበቅ ዘመኑ የተድላና የፍስሃ እንዲሆን ከብቶች እንዲረቡና በሽታ እንዳያጠቃቸው በአጠቃላይም ሰላም እንዲኖር የሚያደርግ ነው" ተብሎ ይታመናል።

በተጨማሪም ቃልቻ ወይም ኔሬይ "ሁሉን ነገር ማየት የሚችል ነው"። "ከቃልቻ ሊሰወር የሚችል ነገር የለም" ተብሎ ይታመናል።

የተጠኘውን ማህበረሰብ እምነት መሠረት አስመልክቶ ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች ጥያቄዎችን አቅርቤ ያገኘሁት ምላሽ ይህ የቃልቻ እምነት የመጣው ከጥንት አያት ቅድመ አያቶች መሆኑና አሁን ከሰፈሩበት ቦታ በፊት በነበሩትም የሚያምኑበት መሆኑን ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች በተለይም (አማኞች ብለው ነው የነገሩኝ) በስፋት ህዝቡን እየቀየሩት መሆኑን ገልፀውልኛል። ከዚህ ባለፈ በቁጥር አናሳ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኦርቶዶክስ ክረስትና እምነት የተቀበሉም እንዳሉ ተነግሮኛል።

3.9 ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት

በመኢኒት ብሔረሰብ አንድ ግጭት አለዚያም በባህሉ የማይፈቀድ ተግባር ተፈፅሞ ቢገኝ ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት እንዲካሄድ የሚያደርጉበት የራሳቸው ልምድ አላቸው።

> *"በብሔረሰቡ አባላት መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች የተነሳ የሰው ህይወት ቢጠፋ ዳኝነት የሚቀመጡትና ውሳኔ የሚሰጡት ከገዳይና ከሟች ወገኖች ጋር የሥጋ*

ዝምድናና ትስስር የሌላቸው ገለልተኛ ሸማግሌዎች ናቸው። በእርቁ ሂደት የገዳይ ቤተሰቦች ልጃገረድና የክብት ካሳ ለሟች ወገን ያቀርባሉ። ለሟች ወገን የሚሰጠው የደም ካሳ ሰባት ክብት ሲሆን በመጀመሪያው ቀን ሶስት ብቻ ነው። ከቀብር በኋላ የገዳይና የሟች ወገኖች በወንዝ ዳር የማሸላ ገንፎ ይቀርብላቸዋል። ክብት ታርዶ የወተት አንድቱን ሁለቱም ወገኖች በሁለቱ የተለያዩ አቅጣጫዎች ጫፍና ጫፉን በጥርሳቸው ወጥረው እንዲይዙ ከተደረገ በኋላ እኩል ቦታ በሸማግሌዎች ተቆርጦ ድርሻ ድርሻቸውን እንዲበሉ በማድረግ የዕርቅ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል። ቀሪው አራት ክብትም ለሟች ወገን ወዲያውኑ ይሰጣል" (የደ.ብ.ብ.ሀ. ፕሮፋይል፣ 2001፣66)

እርቅን በማስፈፀም ረገድ ሸማግሌዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ ገዳይ ለሟች መቀበሪያ የሚሆን ክብት እስካልሰጠ ድረስ ሟች አይቀበርም። የሟች ወገኖችም የገዳይን ካሳ አባል እየፈሰጉ በመግደል ግጭቱ እየተባባሰ ይሄዳል። ይህን ግጭት ቶሎ ለማቆም የገዳይ ቤተሰቦች መቀበሪያ ክብትና ሽማግሌ ይዘው ወደሟች ቤተሰቦች መሄድ አለባቸው።

በእርቅ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ የተለያዩ ድርጊቶች የተለያዩ ትዕምርቶች አሏቸው። የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች በእርቅ ስርዓቱ ላይ የማሽላ ገንፎ ነው የሚበሉት። ለገዳይ ቤተሰቦች በካሳነት አንዲት ልጃገረድም ትሰጣለች። ካሳ በብሔረሰቡ አጠራር "አሻ" ይባላል። በአሻ የተሰጠችውን ልጃገረድ የሟች ወንድም ያገባታል ትወልዳለች። ማሽላም አንድ ጊዜ አፍርቶ አይደርቅም እያለመለመ ሌላ ፍሬ ያፈራል። የሟች በአካል ቢለይም ልጃገረዷ ይህወት ስለሰጠች ዘሩ ቀጥሏል የሚል ትርጉም ይሰጡታል።

በብሔረሰቡ ሸማግሌዎች ከሚፈቱ ቅራኔዎች መካከል በገዘሙት የወደቁ ሰዎች ጉዳይ ነው። ከትዳር ውጭ መሄድ በባህሉ የተወገዘ ነው። አንዲት ሴት ከትዳሯ ውጭ ወዳም ይሁን ተገዳ ከሌላ ወንድ ጋር ጾታዊ ግንኙነት ብትፈፅም ለባሏ ምግብ አትሰራም፣ ውሀም አትቀዳም ቤት መግባትም አትችለም። ነገር ግን ማንም አያየኝም ብላ የዘወትር ስራዋን በቤትና በዱር ብታከናውን "ቃልቻ ይቆጣል" እናም "ሆዷን ነፍቶ ይገድላታል"። ልጅ እኳን ብትወልድ "ፊንጢጣው የወጣ ይሆናል" የሚል እምነት በመኖሩ። ለባሏ እከሌ እንዲህ አድርጎኛል ብላ ትናገራለች። ባልም ተደፍሬአለሁ በሚል ሌላ ጠብ እንዳይፈጥር ነገሩን ሸማግሌዎች ይይዙታል። ሴቲቱና ያባለጋት ሰው በሸማግሌዎች ፊት ቆመው ሁለተኛ አናደርግም በሚል ከተማማሉ በኋላ ለእርቁ ማስፈፀሚያነት በተቀጠቀጠ በግ ደም በግ ታጥባ ትነሳለች። የዚህ በግ ስጋም የመንፃት ሥርዓት ወይም ማጠብ የተከናወነላቸው ሰዎች "ሀጢያት አርፎበታል" በሚል እምነት አይበላም።

3.10 ባህላዊ አስተዳደር

የመኢኒት ብሔረሰብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ባህላዊ አስተዳደርና የዳኝነት ባህላዊ ተቋማት አሉት፡፡ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮችን አጣምረው የሚሰሩና ሥልጣን ያላቸው አካላትም አሉ፡፡

> *እነዚህ መንፈሳዊና ባህላዊ የአስተዳደር ሥልጣን አካላት የሚሰየሙት በህብረተሰቡ በሚመረጡ የጎሳ መሪዎችና ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በጎሳ መሪዎች እና በአንጋፋ የአገር ሽማግሌዎች ይሁንታ እና አመኔታ አግኝተው ለሥልጣን የሚበቁበት ኔሬይ ቃልቻዎች በመባል ይታወቃሉ (የደ.ብ.ብ.ሀ.ፓሮፋይል፣ 2001፣66)፡፡*

እነዚህ አካላት ወይም ኔሬይ በእያንዳንዱ ጎሳ ይገኛሉ፡፡ በየጎሳው መካከል ለሚፈጠሩ ፀቦችና ቅራኔዎች ታይተው ዳኝነት የሚሰጠው በአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ነው፡፡ ከኔሬይ ወይም ከቃልቻ ቀጥሎ በስልጣን እርከን ላይ የሚገኙት የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ በተሰጣቸው ሥልጣንም የተጣላን በማስታረቅ በዳይ ለተበዳይ ባጠፋው ጥፋት ልክ በሸንጎ ካሳ እንዲከፍል በመወሰን እርቁን ያስፈፅማሉ፡፡ በዚህም ለባህላዊ ሥርዓቱ ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ስራን ይሰራሉ፡፡

ባለቃልቻው ወይም "ኔሬይ" አንድ ጊዜ ከተሾመና ሥልጣን ከያዘ ስልጣኑን የሚያስረክበው ወይም መንፈሱ ወደሌላ የሚሻገረው በሞት ሲለይ ብቻ ነው፡፡

> *የባህላዊ አስተዳደሩ የስልጣን ዘመን የዕድሜ ልክ ሲሆን ቃልቻው (የእምነት መሪው) ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ሥልጣኑን የሚወርሰው የሚቹ መንፈስ ያረፈበት ወንድ ልጅ ነው፡፡ የሚች መንፈስ በልጁ ላይ ማረፉ የሚረጋገጠው የሚቹ መንፈስ በልጁ ላይ አርፎ ያስገዘፈው ወይም ያንቀጠቀጠው ወይም ያስፈራው እንደሆነ ነው፡፡ አለበለዚያ ግን የሚች ወንድ ልጅ በመሆኑ ብቻ የአባላቱን ስልጣን አይወርስም፡፡ የሚች መንፈስ ያረፈበት ልጅ ተለይቶ እስኪታወቅ ድረስ የቀብር ሥርዓቱ አይፈፀምም፡፡ የቃልቻው መንፈስ ያረፈበት ልጅ ተለይቶ እንደታወቀ አስክሬኑ ይቀበራል፡፡ ... ለቀስተኛው ወደ ቀብር ሲሄድ እርሱ ግን እቤት አካባቢ ዱስ ነገር ተሰርቶለት ከሽማግሌዎች ጋር ይቀመጣል (የደ.ብ.ብ.ሀ. ፓሮፋይል፣2001፣6)፡፡*

ከሶስት ወር በኋላ በድንጋይ ተቀጥቅጦ በተገደለ ከብት ደም ታጥቦ ወደቤት ይገባል፡፡ ከዚህ በኋላ ወራሽ ህዘኑን ጨርሶ እራሱን በማንፃት ህዝቡን ለመምራት ብቁና ዝግጁ ነው፡፡ ተብሎ ስለሚታመን መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ተግባሩን አጣምሮ ወደ ተልዕኮው ይሰማራል፡፡

ማህበረሰቡም ሾሞ የሸለመው ባለቃልቻ ወይም "ሌሬይ" በሞት ስለተለየ ሌላ አልሻም ወደሚል ማፈንገጥ ሳይሄድ የስልጣን ወራሹን ልክ እንደቀዳሚው ሁሉ ይቀበላል። አዲሱ ባለቃልቻም የሚያስተዳድረውን ህዝብ በማዘዝና በመምራት ኃላፊነቱን ይወጣል። ህዝቡም ትዕዛዙን በመቀበል ወደ ተግባር በመተርጎም በሙሉ ፈቃደኝነት ያገለግላል። ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ለቃልቻ ያለውን ቦታ ያሳያል።

በብሔረሰቡ ዘንድ ቃልቻ ከፍተኛ ተቀባይነትና እምነት ያለው ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ የተለያዩ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ባለቃልቻ ሰው ከሞት ስልጣኑን የሚረከብ እስኪገኝ ድረስ አይቀበርም። ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ እምነት "ጠባቂና መሪ" የሆነው መንፈስ አብሮ እንዳይቀበር ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ነው። ሌላው ማሳያ በትዳር ላይ የባለገች ሴት ወይም ወንድ ቢኖሩ ጉዳዩን በሚስጥር መያዝ አይቻልም። ምክንያቱም "ቃልቻ ስለሚያውቅ ተቆጥቶ ይገድላል" ሴቷም ጥፋቷን ደብቃ ከባሏ ልጅ ብትወልድ ፊንጢጣው የወጣ ልጅ ትወልዳለች የሚል እምነት በመኖሩ ነው። እነዚህና ሌሎች የእምነትና የከበሬታ መግለጫዎች ስረአቶች ለባህላዊ አስተዳደሪዎቹ በብሔረሰቡ ያለን ትልቅ ቦታ የሚያሳይ ነው።

4. የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት አከዋወን ትንተና

በመኢኒት ብሔረሰብ ለቅሶ "ሮዋ" በሚል ይጠራል። ሥርዓቱም በብሔረሰቡ ዘንድ ትልቅ ትኩረትና ሽፋን ከሚሰጣቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ የለቅሶ ሥርዓት በሚች ማህበራዊ ደረጃ ተከፋፍሎ ይከናወናል። ለዚህም እድሜ እና በማህበረሰቡ የሚሰጥ ስልጣን ወሳኝ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ሚች የሞተው በሰው ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱን ይወስነዋል። የሀዘን አገላለፅ መንገዱም እነዚህን ጉዳዮች መሠረት ባደረገ መልኩ ይካሄዳል።

በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥርዓቱ በሚች ማህበራዊ ደረጃ ተከፋፍሎ የሚካሄድ ይሁን እንጂ በማንኛውም የለቅሶ ሥርዓት ሦስት ሂደቶች ይታያሉ። እነሱም ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ቀብር ክንውኖች በማለት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

4.1 የለቅሶ ሥርዓት አከዋወን

4.1.1 በዕድሜ

4.1.1.1 ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ ሄዋን ለደረሱ

በብሔረሰቡ ልጅ እንደ ፀጋ የሚቆጠር በመሆኑ ልጆች ሲወለዱ ከፍተኛ ደስታ ይሆናል። በመኢኒቶች ዘንድ በተለይ የተወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ ከፍተኛ ፈንጠዝያ ይሆናል። ጥይት ይተኮሳል። ደስታው እጥፍ ድርብ ነው። ሴት ከሆነች ደግሞ አባቷ ለጥሎሽ ያወጣው ገንዘብ ተተካ በሚል በከፍተኛ ደስታ ይቀበሏታል።

ከዚህ በኋላ አድገው ለአቅመ አዳም/ሄዋን ሲበቁ ደስታው እጥፍ ድርብ ይሆናል። ንብረት ለማፍራት ትዳር ለመያዝ እና ልጅ ለመውለድ መድረሳቸውን ለመግለፅም የጥርስ ነቀላወይም"ኬት" ሥርዓት ይከናወንላቸዋል። ይህ ሥርዓት በከፍተኛ ድግስ፣ በጭፍራና በዘፈን የሚደምቅ ነው። ይህ የእድሜ ክልል ወጣቶች ከቤተሰብ ሽክምነት የሚላቀቁበት ነው። በዚህም አባትና እናት[6] የአጎት ልጆችና አጎቶች ሁሉ ይደሰታሉ። ለብዙ ቁምነገርም ይታጫሉ። ይህን ተስፋ በተግባር ሳያሳዩ ወንዱ ጥሎሽ ሰጥቶ አግብቶ ልጅ ሳይወልድ እንዲሁም ሴቷ ባል አግብታ ጥሎሽ ሳታመጣ ሞት ቢቀድም ሀዘኑ እጅግ የበረታ ይሆናል።

[6] ይህንን አገላለፅ ብዙ ቦታ ተጠቅሜበታለሁ። ግልጋሎቱም ዘመድ አዝማድ ለማለት ነው። ቃሉን እንዳለ ዘመድ አዝማድ ያልኩ እንደሆነ በብሔረሰቡ ባህል ገምድና በአባት በኩል የሚቆጠር መሆኑን አያሳይልኝም ብዬ ነው።

ምክንያቱም ልጅ ወልዶ እራስን ከመተካት በላይ ለወላጆች፣ ለአጎቶችና ለአጎት ልጆችም የሚያከራው ወንድ ልጁ ጥሎሽ ሰጥቶ ሚስት ማግባት፤ እንዲሁም ለሴት ቤተሰብ ጥሎሽ እና አማች ማግኘት ነውና። ይህንን አለም ሳያዩ ሞት ቢመጣ ሀዘኑ እጅግ የመረረ በመሆኑ የለቅሶ ተሳታፊው ሁሉ ተግባር ማልቀስ ይሆናል። አቶ ሴላ ባለኮሮ የተባሉ መረጃ አቀባይ "ከህፃንነት እስከ አቀመ ሄዋን/አዳም ደርሶ ለሞተ ምርር አድርገን ነው የምናለቅሰው። ምክንያቱም ይህን አለም አይቶ ስላልጠገበ በለቅሶ ብቻ ነው የምናሳልፈው።" በማለት ገልፀውልኛል (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌለች ቀበሌ)።

በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ክንውኖችን እንደሚከተለው በዝርዝር ለማየት ይቻላል።

4.1.1.1.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት

ታማሚው ህመሙ ፀንቶ እንደማይድን ከተገመተ በባህሉ መሰረት የምግብ ዝግጅት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። ለለቅሶ ሥርዓት ማስፈፀሚያነት የሚዘጋጅ ምግብ በመጠንም በአይነትም ከወትሮው የተለየ ነው። ሀዘንተኞች የቀብር ሥርዓቱን አስፈፅመው ከቅርብ ዘመድ በስተቀር ወደየመጡበት ስለሚሄዱ የምግቡ መጠንም ይህንኑ ባገናዘበ መልኩ ይዘጋጃል። ለሀዘን የሚዘጋጅ ምግብን አስመልክተው ወ/ሮ ምይና እኛኝ የሰጡት መረጃ *"በእርግጥ እኛ ቤት ውስጥ ለዘውትር የምንበላው ገንፎ ነው። ለለቅሶ ግን ከዚህ ባሻገር ለሚመጡ እንግዶች ንፍሮ ይቀቀላል። ጨው ወይም ቡንጡላ ለሚጠጡት ይሰጣቸዋል። ቦርዴም እናዘጋጃለን። አብዛኛውን ግን ንፍሮ ነው የሚንሰጠው። (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌሊች ቀበሌ) የሚል ነው።*

እነዚህ ምግቦችና መጠጦች ለሀዘንተኛው መሸኛ ይዘጋጃሉ። ምግብና መጠጡ መቼና የት እንደሚቀርብ አቶ ኢፋይ ቦመ የተባሉ መረጃ አቀባይ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል።

> *በለቅሶው ቤት ውስጥ ያደሩም ካሉ ንፍሮና ጨው (ቡንጡላ) ይሰጣሉ። ጉርጓድ መቆፈር ሲጀመርም ይቀርባል። እንደየአመጣጣቸው ቅደም ተከተል በርከት ብለው ለመጡት በእቃ እያደረግን እንሰጣቸዋለን።(13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌሊች ቀበሌ)*

በቅድመ ሞት የሚዘጋጅ ሌላው ተግባር አለ። ይህም ሚች በጠና ታሞ እያለ ሰዎች እንዲጠበቁት ይደረጋል። ጠባቂዎቹ በዚህ ጊዜ ወተት ይዘው ነው የሚጠብቁት። እነዚህ ሰዎች የታማሚውን መሞት አለመሞት የማረጋገጥ ተግባር ይወጣሉ።

4.1.1.1.2 ጊዜ ሞት ዝግጅት

ታማሚው ነፍሱ ስትወጣ "የመጨረሻ ስንቁን እንዲይዝ" በሚል እምነት አስከሬኑን ሲጠብቁት የነበሩት ሰዎች ወተት በአፍ በመጨመር ዘቅዝቀው ያስቀምጡታል።

በዚህ ጊዜ የሟች እናትና አባት በከፍተኛ ሀዘን አምርረው በማልቀስ ጎረቤቶች እንዲሰባሰቡ ያደርጋሉ። ይህ ለቅሶ ጎረቤት እንዲሰማና እንዲሰባሰብ ለማስቻል የሚያደርግ ነው። ከዚህ በኋላ ለቅሶቸው በቀስታ እንዲካሄድ ይደረጋል።

ቀጣዩ ተግባር የግንዘት ሥርዓት ነው። ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን የደሱ ሟቾች የሚገነዙት በልብስ ነው። ስርዓቱም በቤተሰቦቻቸው ይፈፀማል። በተጠቀሰው የእድሜ ክልል የሚገኙ ሟቾች በሞቱ ማግስት ስለሚቀበሩ ጠባቂዎች መሞታቸውን ባረጋገጡ ጊዜ ወዲያው የግንዘት ሥርዓቱ ይካሄዳል።

የግንዘት ስርዓቱም በቅድሚያ አስከሬኑ ከእንጨት በተሰራ አልጋ ላይ በመዘርጋት እይኑ እንዲከደን ይደረጋል። እጁን በመዘርጋት ወደ ብልቱ አምጥተው ያስቀምጣሉ። ይህ ሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ አስከሬኑን በሀረግ ዙሪያውን በመጠምጠም በልብስ ጠቅልለው ያስቀምጣሉ። ከዚህ በኋላ ቀጣዩ ሥራ "ቢራች" ወይም ሬሳ ሳጥን ዝግጅት ነው።

የሬሳ ሳጥኑ የሚዘጋጀው ብዙ ጊዜ ኮርች ከሚባል እንጨት ነው። ካልተገኘ ግን በአካባቢው ከሚገኝ ማንኛውም እንጨት ይዘጋጃል። አሰራሩም የሬሳ ሳጥን ለመስሪያነት የተመረጠው እንጨት ከተቆረጠ በኋላ ሁለት ቦታ ተሰንጥቆ እንዲቦረቦር ይደረጋል። አስፈላጊውን ያህል በመጥረቢያ ከጎረጎደ በኋላ አስከሬኑ ወዳለበት ያመጡታል። ከዚያም በጨርቅ የተጠቀለለውን አስከሬን በውስጡ ያስገቡና ክፍተት እንዳይኖረውና እንዳይንሸራተት በቀጭን እንጨት እየተደረገ ዙሪያውን በቢስማር ይመቱታል። ፈሳሽና ሽታም እንዳያመጣ ክፍተቶቹ በእበትና በጭቃ ይመርጋል። ከዚህ በኋላ አስከሬኑን ልብስ አልብሰው ያስቀምጡታል። ቤቱ በሀዘንተኛ ሰዎች ስለሚሞላ እስኪቀበር ድረስ ሀዘንተኞችም በሳጥኑ ላይ ይቀመጡበታል።

የግንዘት ሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ለቅሶውን ለዘመድ አዝማድ መንገር ነው። ይህ ተግባራዊ የሚሆነው በአካባቢው ባሉ ልጆች ነው። ለሚላኩት ልጆች እዚህ እዚህ ቀበሌ እገሌ የሚባል ሰው ሞቷልና ኑና አልቅሱ ብለው እንዲነግሩ ይታዘዛሉ። ቤተዘመድ በለቅሶ

ቤት ከተሰበሰበ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ቀድሞ ለቅሶ ቢጀመርም እጅግም የደመቀ ሳይሆን በቀስታ የሚለቀስ ስለሆነ በይፋ ለቅሶው ይጀመራል።

ለቅሶውን በማስጀመር ረገድ የሚች አባትና እናት ትልቅ ሚና አላቸው። እነሱን ተክትሎ ሌላው የለቅሶ ተሳታፊ ሁሉ ሀዘኑን በማልቀስ፤ በመጮህ ይገልፃል። ለቅሶውን የሰመ ለዎችም እያለቀሱ ይመጣሉ ።

የቀብር ቦታውን በመምረጥ የጉድጓድ ቁፋሮ የሚካሄደውም በዚሁ ወቅት ነው። በብሔረሰቡ ባህል የቀብር ቦታ በመኖሪያ ቤት አካባቢ ወይም ግቢ ውስጥ ይዘጋጃል። ይህ ደግሞ አስከሬኑን ለመጠበቅ እንዲችሉ እንዲሁም "ሚች በቦታው ነው የተቀበረው የትም አልቀረም" የሚል ትርጉምም ይሰጠዋል። የቀብር ቦታው የሚመረጠው በሚች ቤተሰቦች ነው። አቅጣጫው ግን ለየትኛውም ሚች ተመሳሳይ ነው። ይህን ሀሳብ አስመልክተው አቶ ሴላ ባለካሮ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *በእኛ ባህል የተመረጠ ቦታ ወይም ቤተክርስቲያን የለም። በሚቹ በር ላይ የቀብር ሥርዓቱ ይፈፀማል። እሬሳውን የምናወጣውም ፊት ሳይሞት በገባበት በር ሳይሆን በሌላ በር ወይም በሌላ በኩል ቤቱን በማፍረስ ነው የምናወጣው። ከዛም እዛው እንቀብረዋለን። የቀብር አቅጣጫውም በማንኛውም የእድሜ ክልልና ፆታ ተመሳሳይ ነው። ይህም ጭንቅላታቸውን ወደ ምዕራብ እግራቸውን ወደ ምስራቅ አድርገን እንቀብራለን (13/08/2003 ቢያጊሊኝ ቀበሌ) ።*

የቀብሩ አቅጣጫ "በታ ጠልቋል ሞቷል አናገኘውም" የሚል ትርጉም ያለው መሆኑን እንዲሁም አስከሬኑ በአዲስ በር የሚወጣው ደግሞ ሚች በመሆኑ ህያዋን በሚገለገሉበት በር በአንድነት አይወጣም። ከቤተሰቡ ተነጥሏል ወደ አዲስ አለም ሄዷል የሚል ትርጉም አለው። ይህን ደግሞ አቶ ታቶ ማርደሮ፤ እንዲሁም ወ/ሮ አረጋሽ ቦኤች የተባሉ የጎማ ቀበሌ ነዋሪዎች ነግረውኛል።

ሚች ህይወቱ ባለፈ በሁለተኛው ቀን ለቀብር የተመረጠው ቦታ ላይ የጉድጓድ ቁፋሮ ይካሄዳል። በዚህ ስራ ማንኛውም ወንድ መሳተፍ ይችላል። ከዛም የሚች ቤተዘመዶች በስም እየተጠሩ አስከሬኑን ተሸክመው እንዲያመጡ ይደረጋል።

አስከሬኑ በሁለት ወፍራም እንጨቶች ለጋራ በመያዝ በአዲሱ በር አውጥተው ወደ ቀብር ቦታ ያመጡታል። ከዛም ጉድጓዱ ውስጥ አራት ሰዎች ይገቡና የሬሳ ሳጥኑን ይቀበላሉ። አስከሬኑ ወደጉድጓድ የሚገባው በገመድ ታስሮ ነው። የገመዱን ጫፍ በጉድጓዱ ዙሪያ ያሉ ሰዎች በመያዝ እንዳይወድቅ በማድረግ ወደ ጉድጓዱ ያስገባሉ። ከዚህ በኋላ ሳጥኑ ለብሶት

የነበረው ልብስ ይገፈፍና ወደ ውጭ ይጣላል። ከዚያ አፈር የመመለስ ስርዓት ይከናወናል። በዚህ ጊዜ የለቅሶ ተሳታፊዎች እጅግ በመረረ መልኩ ያለቅሳሉ። መሬት ላይ በመንበርከክ፣ እጅን እራስ ላይ በማድረግ እና በመወራጨት ያለቅሳሉ። የመጨረሻ በመሆኑ እያዘኑ የተሰማቸውን በለቅሶ ይገልፃሉ። በመቃብሩ ላይ ምንም ምልክት አይደረግም። ገና ነው አለም አላየም ያለ እድሜው የተቀጨ ነው ለማለት።

4.1.1.1.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች

ሟች በልጅነት በመቀጨቱ ሀዘኑ ለሦስት ወራት ይዘልቃል። በዚህ ጊዜ ሀዘንተኛው ሁሉ (የሟች ቤተሰቦች) ፀጉሩን ይላጫል።

ከቀብር በኋላ ወይም በቀብሩ ማግስት በመቃብሩ ላይ ጎጆ በመስራት ቤተሰቦቹ እስከ ሦስት ወራት ያህል መቃብሩን ይጠብቃሉ። ይህንንም የሚያደርጉት "ቃምጡት" ወይም ሰው የሚበላ ሰው ቆፍሮ አውጥቶ ይበላዋል የሚል እምነት ስላለ መሆኑን የተሰያዩ መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል። ጎጆው የሚሰራው በቤተሰቦችና በሀዘንተኞች ነው። አቶ ጆሮ ዘሪሁን የሬሳ መጠበቂያ ዳሱን አስመልክተው

> *ዳሱ የሚቆየው ለሦስት ወራት ያህል ነው። እስከ አንድ ወር ድረስ ሁሉም ቤተዘመድ ያድራል። ከአንድ ወር በኋላ በፊረቃ ነው የምናድረው። ሴቶች ግን ከአስር ቀን በኋላ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። እኛ ግን በተራ በተራ እንጠብቃለን። ይህ ደግሞ ስራችንን እንዳያስተጓጉለን ያደርጋል (14/08/2003 ጨበራ ቀበሌ) በማለት ገልፀዋል።*

የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆ ከሦስት ወራት በኋላ ይፈርሳል። በዚህ ጊዜ ቦርዴ ወይም ሻሎ በማዘጋጀት ድግስ በማድረግ ጎጆውን ያፈርሱና በገላጣ ቦታ ላይ (በሌላ እዕዋት ላይ አደጋ እንዳይደርስ) ያቃጥሉታል። ከዚያም አመዱን ይበትኑታል። ከዚህ ቀን ጀምሮ ሀዘኑ ይረሳል። ይህ የመጨረሻ የስንብት ፕሮግራም ነው። አቶ ብርሀኑ ወርቁ የተባሉ መረጃ አቀባይ የክንውኖችን ሁኔታ አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ፡-

> *የአስከሬን መጠበቂያ ዳሱ ከፈረሰ በኋላ ባህላዊ መጠጥ አለን ቦርዴ ይባላል። እሱን አዘጋጅተን በቀብሩ ላይ ተገኝተው የነበሩ ሰዎች በሙሉ ይገኙና ተቃምሰን አንድ በአንድ ዳሱን እያፈረሰንን ራቅ ወዳለ ቦታ ይዘን በመሄድ እናቃጥላለን። በተናጠል ወይም አንዱ ወስዶ አንዱ ሳይወስድ ቢቀር ጠላት ይመጣብናል የሚል እምነት ስላለን አንድ ላይ ሆነን እንደቀበርን እሱንም አንድ ላይ ማፍረስ አለብን። ስለዚህ ቦርዴ ጠጥተን የመጨረሻ ስንብት እናደርጋለን። (15/08/2003 ዓ.ም ባቸማ) በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።*

ሳጆው የተሰራበት እንጨትም ሆነ ሳር ማቃጠል በባህሉ የተለመደ ተግባር ነው። ከልማዳዊ ተግባርነቱ በዘለለ ካልተቃጠለ የሚች ቤተሰብም ይሁን ማንኛውም ሰው እንጨቱን አንስቶ ለማገዶነት ቢጠቀምበት ሰላም አይሰጥም የሚል እምነት እንዳለም የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ተናግረዋል።

4.1.1.2 ለእድሜ ባለፀጋዎች

በብሔረሰቡ በእድሜ ትልቅ የሆነ ልጆች የወለደ እንዲሁም አማች ያለው ወንድም ይሁን ሴት ሲሞት የሀዘን ሥርዓቱ የሚገለፀው በዘፈንና በጭፈራ ነው። ሚች አለም አይታልና በጭፈራ ነው የሚሸኘው የሚል አመለካከት አለ።

4.1.1.2.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት

ሚች በሀመም ላይ እያለ ይሞታል አይድንም የሚባልበት ደረጃ ሲደርስ ቤተዘመድ ተሰብስቦ አዲስ ቤት ይሰራል። ከዛም ታማሚውን በዚህ አዲስ ቤት ወይም "ጋሀ" ውስጥ ያስገቡታል። ይህ አዲስ ቤት ለሚች "ስታዩን ይቀንስለታል" ምክንያቱም እዚያ ከገባ "አይቀይም ይሞታል" የሚል እምነት አለ። በዚህ ቤት ውስጥም በሽተኛውን የሚጠብቁ ሰዎች እንዲቀመጡ ይደረጋል።

በማህበረሰቡ ዘንድ ቤት ቀልሶ፣ ወልዶና ከብዶ መኖር ማህበራዊ ከበሬታን ያስገኛል። ይህን ከበሬታ ለማግኘት የታደለ ሰው ሲሞት የሀዘን ሥርዓቱ የሚገለፀው በጭፈራ ነው። በአለባበስ በኩልም ሀዘናቸውን ለመግለፅ እንዲሁም ለጭፍራው ማስኬጃነት የሚያገለግሉ አልባሳትን ጌጣጌጦችንና ሌሎች የመከወኛ ቁሶች ሁሉ ይይዛሉ። ይህ አጋጣሚ ለሚች ያለን ክብር የሚገለፅበት፣ የሚች ታሪክና ገድል በስፋት የሚዘከርበት ተሳታፊዎችም ለሚች ያላቸውን አመለካከት በጭፈራና በዘፈን የሚገልጹበት ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በብሔረሰቡ ባህል መሰረት የዕድሜ ባለፀጋነት ማህበራዊ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው። ሽማግሌነት በብሄረሰቡ በአስታራቂነት በባህል አዋቂነት እና በተለያዩ ማህበራዊ መሰረቶች ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል። ይሁን እንጂ በእድሜ የበለፀጉ ሰዎች ሲሞቱ ሀዘን የሚገለፀው በጭፈራና በዘፈን ነው። ነገር ግን የሚለቀስበት ወቅትም አለ። ይህም የሚች ነፍስ መወጣጂ ሲረጋገጥ እና ግበዓተ መሬቱ በሚፈፀምበት ወቅት ነው። ይህን

በምልታ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ከነዚህ ጊዜያት ውጭ ማንኛውም የለቅሶ ተሳታፊ እየፎከረ (ቡራሊዳይ)፣ ሚችን እያሞገሰ (ካክሲዳይ) እንዲሁም ከበሮ፣ በጡሩንባ እና በቃጭል በመታጀብ እየጨፈረ፣ ሲደክመውም ከተዘጋጀው ምግብና መጠጥ እየተመገበ ሀዘኑን ይገልፃል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት አለም አይተው፣ አማች አግኝተው በተድላና በደስታ ኖረው በማረፋቸው ነው። በዚህ የእድሜ ደረጃ ደርሰው ከአለም ሲለዩ የተለያዩ ክንውኖች ይካሄዳሉ። የሚች ቤተሰቦች፣ አማቾችና አጎቶች ሀዘናቸውን የሚገልፁት ከብት በመቀጥቀጥ ነው።

የአዲሱ ቤት መገንባት በብሔረሰቡ ሚች ወደ አዲስ አለም የሚሄድ መሆኑን የሚያመለክት ትርጉምም አለው። ታማሚውን የሚጠብቁት ልጆቹ አልያም አጎትና የአጎት ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ። በሚጠብቁበት ወቅት ወተት አጠገባቸው ይዘው ይቀመጣሉ። ሚች ነፍሱ ከስጋው መለየቷ "ሲረጋገጥ የመጨረሻ ስንቅ" በማለት ለማጠጣት ነው።

አዲሱ ቤት ወይም በብሔረሰቡ አጠራር "ጋሀ" የሚሰራውና ቦታው የሚመረጠው በታማሚው ልጆች፣ አጎትና የአጎት ልጆች ስምምነት ነው። አቶ መልኬ ኬላጌ የተባሉ መረጃ አቀባይ አዲሱን ቤት አሰራር አላማ አስመልክተው፦

> *ለትልቅ ሰው በመጀመሪያ ዘመዶቹ ተሰብስበው መጥተው አዲስ ቤት ይሰራሉ። አዲሱ ቤት መገለጫ የሰውየውን ትልቅነት ያመለክታል። ከዚህ ባሻገር በጠና የታመመ ከሆነ እንዲይሰቃይና ቶሎ እንዲሞት ይሆናል ብለን እናምናለን። ሌላው የዚህ ቤት መሰራት ታማሚው ከነበረበት አለም ወደ ሌላ አዲስ አለም የሚሄድ መሆኑንም ለማመልከት ነው። (17/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)*

ታማሚው በኖሩበት ቤት ሞተው አስከሬናቸውም ከዚሁ ቤት መውጣት የለበትም። ይህ በባህሉ የማይፈቀድ በማህበረሰቡ ባህል የሚወገዝ ነው።"...ሰውየውን ገዝ ብለው እዛው በኖረበት ቤት ቢሞትና እዛው ቢቀበር የሚች ልጆች ይወቀሳሉ። ቤተሰባቸውን በደንብ ያልቀበሩ ተብለው በባህሉ ከፍተኛ ትችትና ማግለል ይደርስባቸዋል።" (ገዚ ከማሁ)

ለአዛውንት ሚቾች የሚሰራው አዲስ ቤት ከማህበረሰቡ እምነት ጋርም ተያያዥነት አለው። የመኢኒት ብሔረሰብ የሚከተለው የቃልቻ እምነትን ነው። ባለቃልቻዎች በብሔረሰቡ ከፍተኛ የከበሬታና የእምነት ደረጃ አላቸው። በመሆኑም አስከሬን አጠገብ አይጠጉም። አስከሬን በድን ነው እራሱን ማዘዝ የማይችል የረከሰ ነው ተብሎ ስለሚታመን። ከማንኛውም ሰው ቤት ገብተው ምግብ እና መጠጥ ለመጠቀም የሚችሉት የቤቱ እቃዎች ንፁህ ሲሆኑ ብቻ ነው። ንፅህናው ደግሞ የሚገለፀው በተለይም ትልቅ ሰው ሲሞት የአስከሬኑ እንፋሎት በእቃዎቹ

ላይ ካላረፈ እና ትልቅ ሰው እቤት ውስጥ ካልሞተ ነው። እንደአጋጣሚ ሞቶ ቢገኝ በዚህ ቤት ባለቃልቻዎች የሚስተናገዱበት ከሦስት ወር በኋላ ይሆናል። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚች መንፈስ ወጥቷል ተብሎ ስለሚታመን።

ሌላው የአዲሱ ቤት መገንባት ምክንያት ሚች በድንገት እንኳን (ታሞ ህመመ ለሞት ያደርሰዋል ተብሎ ባልተገመተበት) መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ሞቶ ቢገኝ ለሚች ልጆች "ሰላም አይሰጥም" የሚል እምነት በመኖሩ ነው። ይህ እንዴት ሊገለፅ እንደሚችል የተጠየቁ መረጃ አቀባዮች መካከል አቶ ዋየች ጃሻ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡-

> *ለሚች ልጆችና ቤተሰቦች ሰላም አይሰጥም። ምክንያቱም ትልቅ ሰው ስለሆነ መንፈሱ ከቤቱ ውስጥ ቶሎ አይወጣም። ለዚህ ነው የሚረብሸው። በቃ ልጆቹን ማታ ማታ ቅዠት ያስቸግራቸዋል። በህልም ያስጨንቃቸዋል። ያስጮሀቸዋል። ስለዚህ አዲስ ቤት የሚሰራውና ታማሚው ወደዛ እንዲሄድ የሚደረግበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። (14/08/2003 ዓ.ም ዱማ ቀበሌ) የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።*

በብሔረሰቡ አሁን አሁን የቀረ ነገር ግን በድሮ ጊዜ ያደርጉት የነበረ የለቅሶ ስርዓት እንዳለ የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል። ሚች በተለይ በእድሜ የገፉ እንደሆነ የሚች መንፈስ ለቋሚዎች ጥሩ አይሆንም በሚል እምነት ቤተሰቦቹ አካባቢውን ለቀው ለአንድ አመት ይሄዳሉ። ይህ ደግሞ አዛውንቱ በሞተበት አካባቢ መኖር "ለጤና ጠንቅ ነው" በሚል እምነት ቀደም ሲል የሚተገበር ነገር ግን አሁን መሉ በመሉ የቀረ ሥርዓት መሆኑን መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል።

አስከሬን የሚወጣበት አዲስ ቤት ውስጥ የሚች የመጀመሪያ ልጅ ይኖራል። የመጀመሪያ ልጁ ወንድ ባይሆን እንኳን ሴት ልጁ እዛ አትኖርም። አጎት ወይም የአጎት ልጅ ይኖርበታል። የሚች ወንድ ልጅም ብዙ ሚስቶች ቢኖሩት ደግሞ የመጀመሪያ ሚስቱ እና እሱ ብቻ ናቸው የሚኖሩበት።

በቅድመ ሞት ዝግጅት ውስጥ የምናገኘው ሌላው ሥርዓት የኑዛዜ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት በአዲሱ ቤት ወይም በድሮው ቤት ውስጥ ሊከናወን ይችላል። ሥርዓቱንም እንዲያስፈፅመ የቤተዘመድ ሽማግሌዎች ይመረጣሉ። በተመረጡት ሽማግሌዎች አማካኝነት ታማሚው ሀብት ንብረቱን ለልጆቹ እንዲሁም ለአጎትና ለአጎቶቹ ልጆች እንዲያስተላልፍ ይደረጋል። በዚህ ወቅት ታማሚው ብድር ካለበት፣ ሌላ ሰው ላይም ንብረት ካለው፣ ለቃልቻ የተሳለው ነገር ካለ፣ እንዲሁም በቃልቻ እንዲከፍል የታዘዘው ነገር ካለ ሁሉንም ይናዘዛል።

ልጆቹ እንዲከፍሉም ያዛል። ያበደረውንም እንዲቀበሉና እንዲጠቀሙበት ይናገራል። የኑዛዜ ሥርዓቱን አስመልክተው አቶ ሴላ ባላካሮ የሰጡኝ መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፦

> *የኑዛዜ ቃል አለ። ሟች የሚናዘዘው ለልጆቹ ነው። ልጆቹም ትንንሽም ትልልቆችም ካሉ እንደኔ ሆናችሁ እያረሳችሁና እየሰራችሁ አብሷቸው። እነሱም ንብረቱ ላይ ተቀምጠው ይኑሩ። የኔን ስም የሚያስጠሩ ስለሆነ በደንብ አድርጋችሁ አሳድጓቸው ብሎ ለታላላቆች ይናዘዝላቸዋል።* (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌሊች ቀበሌ)

ይሁን እንጂ በብሔረሰቡ የሟች ሴት ልጅ ንብረት አትወርስም። ንብረት የመውረስና የማስተዳደር ሥልጣን ለወንድ ልጆች ብቻ የተፈቀደ ነው። በዚህም መሠረት ሴት ልጅ የአባቷንም ሆነ የባሏን ንብረት አትወርስም። ምክንያቱም ሴት ሴላ ታገባለች ንብረቷንም ትወስዳለች ስለሚባል አባቷ ሲሞት እናቷን የሚወርስ ንብረቱን ይወርሳል። ምናልባት የሟች ሴት ልጅ ያላገባች ከሆነ የእናቷ ወራሽ ለልጅቷ የሚሰጠውን ጥሎሽ ይቀበላል። የሟች ሚስት ባሏ ሲሞት የባሏ ወንድም ወይም ሴላ ዘመድ ይወርሳታል። የውርስ ጋብቻ በብሔረሰቡ ከሚከናወኑ የጋብቻ ሥርዓቶች መካከል አንዱ መሆኑን ልብ ይሏል።

4.1.1.2.2 ጊዜ ሞት ዝግጅት

በዚህ ወቅት በስፋት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የምግብ ዝግጅት አንዱ ነው። ለሀዘኑ ማስፈፀሚያነት የሚያገለግሉ ምግቦችና መጠጦች ይዘጋጃሉ። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የሟች ቤተሰቦች፣ ዘመዶች፣ አማቾችና ሟችን የሚያውቁ ሁሉ በጭፍራ ያሳልፋሉ። ለዚህ ስርዓት ማስፈፀሚያነት ደግሞ በስፍተኛ ደረጃ የምግብ ዝግጅት ይደረጋል።



ምስል 1፦ ለለቅሶ ሥርዓት ማስፈፀሚያነት የሚሆን ምግብ ዝግጅትን የሚያሳይ

ምግቡና መጠጡ የሚዘጋጀው በሚች ቤተሰቦች ብቻ አይደለም የሚች ጎረቤቶችም ጨሞ ወይም "ቡንጡላ" እንዲሁም ለንፍሮ የሚያገለግል በቆሎ ጠጅ፣ ቦርዴና የመሳሰሉትን በማዋጣት የመተጋገዝ ልማድ አላቸው። ይህን የምብ ዝግጅት እስኪሟላ የግንዘት ሥርዓቱ አይካሄድም። ይህ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ሚች ህይወቱ ካለፉበት ቀን ጀምሮ ከሦስት እስከ አራት ቀን (ብዙ ጊዜ ሦስት ቀን) ሊወሰድ ይችላል። ይህን ያህል ቀን ተፈልጎ ተገዝቶና፣ ከዘመድ ከጎረቤት ተሰብስቦም ለለቅሶው ማስፈፀሚያነት አይበቃም ተብሎ ከታመነ የሚወሰድ እርምጃ አለ። አቶ ጆሮ የተባሉ መረጃ አቀባይ የሰጡኝ መረጃ ይህንኑ የሚያመለክት ነው።

ይህ አሁን እየሰራን ያለነው ምግብ አሁን ያዘጋጀነው ከቤተዘመድ በአጠቃላይ ተሰብስቦ ነው የሚዘጋጀው። አሁን ከሩቅም ሆነ ከቅርብ ለመጡት ሀዘንተኞች የበቆሎ ንፍሮ እና ቡንጡላ (ጨም) አፍልተን እንሰጣቸዋለን። ይህ የሚሰበሰበው ከቤተዘመድ ስለሆነ ከጎረቤቶችም እንሰበስባለን። ቡናውን እንዲሁም ለንፍሮ የሚያገለግለውን በቆሎም ያመጡልናል። ይህ ሁሉ ተጠቅመን ለሀዘንተኞች ማስተናገጃ እናደርጋለን። ሀዘንተኞች ከቀብር በኋላም ብዙ ቀናት እየጨፈሩ የሚቆዩ ስለሆነ የምግብ ዝግጅቱ በጣም በስፋት ነው የሚካሄደው። ስለዚህ አሁን ዛሬ የሞተው ሰው በድርቅ ጊዜ ቢሆን የሞተው ምርት ስለማይኖር ድሮ ድሮ እንቀብርም ነገር አሁን አሁን ግን እንቀብርና ምርት ሲደርስ የጭፈራ ስርዓቱን እንፈፅማለን። (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌልች ቀበሌ)

በመኢኒት ብሔረሰብ ለትልቅ ሰው በሽምግልናው በባህል አዋቂነቱ እንዲሁም ወልዶ ከብዶ አማችም ያየ በመሆኑ ትልቅ ክብር ይሰጠዋል። ይህ ደግሞ በለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀሙ ላይም የሚታይ ነው።





ምስል 2: በሥርዓቱ ላይ የተዘጋጀ ምግብና መጠጥ ሲመገቡ የሚያሳይ

ይህን አለም ያየ ትልቅ ሰው እንደ ወጣቶች ሁሉ በትንሽ ድግስ አይቀበርም በመሆኑም ድግሱ በጣም የታሰበበት ይሆናል። ሚች የእህል ምርት በቀነሰበት ወቅት ቢያርፍ አይቀበርም። አቶ ካሳ ከበደ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *አስከሬኑን በጨርቅና በኩብት ቆዳ ጠቅልለን በተዘጋጀው የሬሳ ሳጥን ውስጥ እናስገባለን። ከዚያም የሬሳ ሳጥኑን በእንጨትና በቢስማር ክፍተት እንዳይኖረው እንመታለን። ከዚህ በኋላ የአስከሬን ሳጥኑ የሚዘጋጀው አንድ እንጨት ለሁለት ሰንጥቆ በመሆኑ እነዚህ ሁለት ፍልፍል እንደ አገዳ ያሉ ናቸው ሁለት በደንብ ግጥም እንዲልና ምንም ፈሳሽ እንዳያመጣ በጭቃና በእበት እንመርጋለን። ከዚህ በኋላ መሬት እንቆፍርና ጠባብ ጉድጓድ እናዘጋጃለን። ከዚህ በኋላ ሸምበቆ ወይም ቀርከሀ አምጥተን የአስከሬን ሳጥኑን በዛች ቀርከሀ መጠን እንበሳና እንሰካዋለን። ከዛ በቀጥታ ቀርከሀውን ወደተቆፈረው ጉድጓድ አስገብተን አስከሬን የያዘውን ሳጥን እንቀመጥበታለን። ቀርከሀው ወይም ሸምበቆው ከአስከሬኑ የሚወጣውን ፈሳሽ ወደ ጉድጓዱ ስለሚያስተላልፈው በበሽታ እንዳንታወክ ያደርጋል። (20/08/2003 ዓ.ም ጀምሮ ቀበሌ)*

በማለት እህል እስኪገኝ ድረስ አስከሬኑን ባህላዊ በሆነ መልኩ እንዴት ሊቆይ እንደሚችል ገልፀዋል። አስከሬኑ የሚቆይበትን ጊዜና በዚህ ጊዜ ውስጥም የሚካሄዱ ተግባራትን ደግሞ አቶ መልኬ ኬላጌ እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> *አስከሬኑ ከሦስት ወር እስከ አንድ አመት ሳይቀበር ይቆያል። ይህ የሚሆነው ለለቅሶው ማስፈፀሚያ የሚሆን ድግስ መደገሻ እህል እስኪገኝ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ የሟች ልጅ እርሻም ያርስና ንግድም ይሄድና የሚያስፈልገውን አሟልቶ ዘመድ በሙሉ እንዲሰበሰብ አድርጎ የቀብር ስርዓቱን ያስፈፅማል። (15/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)*

ከምግብ ዝግጅት በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የግንዘት ሥርዓት ነው። ግንዘቱ በየትኛውም ማህበራዊ ደረጃ ለሚገኝ ሟች የሚከሄደው በቀን ሲሆን የተወሰነ ሰአት ግን የለውም። በብሔረሰቡ በቀድሞ ጊዜ የሚጠቀሙበት የአገናነዝ ሥርዓት ነበር ይህም አስከሬኑን ቁጢጥ አድርጎ በማስቀመጥ ወንድ ከሆነ ብልቱን "ኮርባ" በሚባል ማሰሪያ ያስሩታል። ሴት ከሆነች ደግሞ በፍየል ቆዳ ሀፍረተ ስጋዋ ይሸፈንና ወደ ላይ ተደርጎ ወገቧ ላይ ይታሰራል። የመጀመሪያ ልጅ በድንጋይ ቀጥቅጦ በተገደለው ከብት ቆዳ ጠቅልለው በማሰር ይገንዙታል። ከዚህ በኋላ በክብ ጉድጓድ ውስጥ የመቅበር ሥርዓት ይካሄዳል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ የአገናነዝ የቀብር ሥርዓት መቅረቱን የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ተናግረዋል። ከነዚህም መካከል አቶ ብርሃኑ ወርቁ፡-

> *በድሮ ጊዜ ያው አገናነዙ ለየት ይላል። በኩብት ቆዳ አድርገን ሟችን ቁጭ በማድረግ በቆዳው ጠቅልለን ነው የምንቀብረው። ጉድጓዱም ክብ ነው። በአሁኑ ጊዜ በተለይም ከደርግ ዘመን ወዲህ እየተለመደ የመጣው አቀባበር በተቦረቦረ እንጨት ውስጥ*

በጨርቅና በስብት ቆዳ የተገነዘውን አስክሬን እናስገባለን። አስክሬኑን በጀርባው እንደተኛ ሰው አድርገን ነው የምገንዘው። ወንድ ከሆነ ብልቱን "ኮርባ" በሚሰኝ ማሰሪያ እናስረዋለን ዘሩ እንዳይፈስ። ሴት ከሆነች ደግሞ በፍየል ቆዳ በማድረግ ወደላይ በማምጣት ከወገቧ ላይ በማሰር በልብስ ጠቅልለን በቆዳ አድርገን እንገንዘለን። ከዛም ቢራች ወይም የሬሳ ሳጥን ውስጥ እናስገባና እንቀብራለን። (17/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)

ግንዘቱ የሚፈፀመው በሟች ልጅ ወይም ወንድም ነው። ሟች ልጅና ወንድም ከሌለው አጎት ይገንዘዋል። እነዚህ ሁሉ ከሌሉት ደግሞ አማች ሊገንዘው ይችላል። በባህሉ መሠረት ለሟች የተጠቀሰውን ዝምድና የማያሟላ ሊገንዝ አይችልም። ሴት ከሆነችም በሴት ልጇ ወይም በእናቷ ትገነዛለች። ሴት ወንድን ወንድ ደግሞ ሴትን መገነዝ በባህሉ አይፈቀድም። ምክንያቱም፦ " የመተፋፈርና የመፈራራት ችግር ስለሚያመጣ ነው።በዋነኛነት ግን ሟችን የሚገንዘው ከውጭ በመጣ ባዕድ ሊሆን አይገባም ምክያቱም እነዚህ ዘረቢሶች አስክሬናቸውን እንኳን የሚገንዝላቸው ያጡ የሚል ስድብና ነቀፌታን ያመጣል።" (ዚኒ ከማሁ)

በብሔረሰቡ በተለይም በእድሜ የገፉ አዛውንቶች ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ሟችን የሚገንዘው በመጀመሪያ ወንድ ልጅ አሊያም በአጎትና በአጎት ልጅ በተቀጠቀጠ ከብት ቆዳ ነው። ይህ ደግሞ የሟች ማህበራዊ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ለመግለፅ ነው። የዚህ ከብት አንገትም አስክሬኑ በተቀመጠበት ቤት የውጭ አጥር በር ላይ ይሰቀላል።ይህም በብሔረሰቡ ሟችን በዚህ ከብት ቆዳ ነው የቀበርነው የሚል መልዕክት አለው። ሌሎች በስረአቱ ላይ የተቀጠቀጡ ከብቶች አነገትም በአጥሩ ላይ ይቀመጣሉ ።ይህ ደግሞ ለተሳታፊዎቹ የሟችን የከበሬታ ቦታ እነዲረዱ ያደረርጋል ።

ወ/ሮ ጋቸሁ ሞላባ የተባሉ መረጃ አቀባይ በብሔረሰቡ የትልቅ ሰውን በተለይም የሴት አዛውንትን የግንዘት ሥርዓት አፈፃፀም አስመልክተው፦

በእኛ ባህል ሴት ስትሞት በመጀመሪያ ትንሽ አልቅሰን አልጋ ተሰርቶ አልጋ ላይ አስክሬኑን እናስቀምጣለን ሴት ነው የሚገንዛት። ልጇ ካለች ልጇ ከሌለችም እናቷ ካልሆነም እህት ልትገንዝ ትችላለች። በመጀመሪያ እንደ ሞተች አፏን ግጥም እናደርግና ፊቷን በሻሽ እናስራታለን። ከዚህ በኋላ አዲስ በታረደች ፍየል ቆዳ ሀፍረተ ስጋዋን በመሸፈን ወገቧ ላይ እናስራለን። በመቀጠል በልብስ እንጠቀልላታለን። ከዛም የሟች ወንድ ልጅ ወይም አጎት ቀጥቅጦ በመጀመሪያ በገደለው ከብት ቆዳ እንጠቀልላትና በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ እናስገባለን (14/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)።

በማለት ገልፀውልኛል። ሀፍረተ ስጋዋ በፍየል ቆዳ የሚሸፈነው ከሰውነት የሚወጣ ፈሳሽ የለቅሶ ተሳታፊውን እንዳያውክ ሲሆን። በስብት ቆዳ መጠቅለሉ ደግሞ ከበሬታን፣ ታላቅነትን

እና የእድሜ ባለፀጋነትን የሚያሳይ መሆኑንም ገልፀውልኛል። በስርዓተ ግንዘት ወቅት የወንድ ብልት በኮርባ የሚታሰረው የዘር ፍሬው "የትም እንዳይፈስ" ለማድረግ ነው። የዘር ፍሬው ከፈሰሰ ለሚች ልጆች "ጥሩ አይሆንም፤ ሁሉም ይሞታሉ" የሚል እምነት በመኖሩ እንዲሁም በክብት ቆዳ መጠቅለሉ የሚችን ክብር የሚያሳይ መሆኑን አቶ ብርሀኑ ወርቁ፣ አቶ ወልደየስ ዶሌ እንዲሁም አቶ ኬለጊ ማናቻ የተሰኙ መረጃ አቀባዮች ተናግረዋል።

ከዚህ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ለዘመድ ለቅሶን የመናገር ሥራ ነው።ይህ ስረአት የሚፈጸመው የግነዘት ስረአቱ በተፈጸመ ማግስት ነው። በብሔረሰቡ አንድ ትልቅ ሰው ታሞ ወደ አዲስ ቤት እንዲገባ በተደረገበት ወቅት ታማሚው ሊሞት ነው በቃ አይድንም የሚል መልዕክት ስላለው በአካባቢው የሚኖሩ ሁሉ ይህን ይረዳሉ። ይሁን እንጂ ለዘመድ የመንገር ስርዓቱ የሚፈፀመው ሚች ከተገነዘ በኋላ ነው። አቶ በድሉ ካሳ የመርዶ ስረአቱን አፈጻጸም አስመልክተው

> *በሌላ አካባቢ ሞትን በመፍራት የማርዳት ሁኔታው ሁሉ የሚፈራበት ነገር አለ። ነገር ግን ሞት ከመጣ በመኢኒቶች ዘንድ ፍርሃት የለም። በግልፅ እንናገራለን። ሰውየው አረፈ ተገላገለ ነው የምንለው። ፈጣሪ የፈጠረውን ነፍስ ፈጣሪ ወሰደው ብለን እናምናለን። ስለዚህ ወደ ዘመድ አዝማድ በአካባቢው የሚገኙ ልጆችን በመላክ እንዲሰማ እናደርጋለን። (18/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ) በማለት ተናግረዋል።*

በየትኛውም የእድሜ ክልል አሊያም የየትኛውም ስልጣን ባለቤት የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ ለቅሶውን ለዘመድ ለመናገር ብዙ ጊዜ ልጆች ይመረጣሉ። ይህም በብሔረሰቡ የሚገኙ ቀበሌ ማህበራትና መንደሮች ተራርቀው ስለተመሰረቱ በፍጥነት ሄደው እንዲናገሩ በማሰብ ነው።ለቅሶው ይፋ ከወጣ በኋላ ሀዘንተኞች በዚሁ እለት በመምጣት የስራ ክፍፍል ያደረጋሉ።

በልቅሶ ላይ እንዲሳተፉ የተጠሩት ቤተዘመዶች በሽማግሌዎችና በሚች ቤተሰቦች አማካይነት የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰጡ ይደረጋል። በዚህም መሠረት የሚች ሴት ልጆች ወደተለያየ ሳሳ ስለሚያገቡ ከቤታቸው ለቀብር ሲመጡ ዘፈን ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል። ሴት ክብት መቀጥቀጥ ስለማትችል ወይም በባህሉ ስለማይፈቀድላት ዘፈን ታመጣለች። አቶ ሲሚንቶ ሽማቻ የተባሉ መረጃ አቀባይ፡-

> *ሴት ክብት መቀጥቀጥ አትችልም ይህ የቀብሩ ሥርዓት ላይ ነው የሚካሄደው። ዘፈኑ ላይ የሚች ልጅም ትሁን የሚች የወንድም ልጅ ውጭ ያገባች ከሆነ ቁጥራቸውም ለምሳሌ ሀያ (20) ቢደርስ ሁሉም ከባሎቻቸው ሳሳ ዘፈን ይዘው ይመጣሉ። ከዛም ዘፍነው ሀዘናቸውን በዘፈን ገልፀው እንዲሄዱ ይደረጋል። በለቅሶው*

ላይ ዘፈን ይዛ ሳትመጣ ብትቀር ዐብ ይፈጠራል። ገምድናም የሚቆራረጥበት ሁኔታ አለ (14/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)።

በማለት የሚች ወገን ሴቶች እና የሚች ሴት ልጆችን ሚና ገልፀዋል። የሚች ወንድ ልጆች እና አማቾች እንዲሁም አጎቶችና የአጎት ልጆችም በቀብሩ ላይ የሚቀጠቀጡ ከብቶችን እንዲያመጡ ይደረጋል። ምክንያቱም የብሔረሰቡ አባላት የእድሜ ባለፀጋዎች ሲሞቱ ሀዘናቸውን የሚገልፁት ከብት በመቀጥቀጥ እንዲሁም በዘፈንና በጭፈራ በመሆኑ ነው። ማንኛውም የመኢኒት ብሔረሰብ ተወላጅ ዘመድ ሲሞትበት ያለውን ፍቅርና ሀዘኑን የሚገልፀው የከብቱን ግንባር በድንጋይ ቀጥቅጦ በመግደል ነው። ብዙውን ጊዜ ለአንድ ሰው የሚገደለው የከብት ብዛት የሚወሰነው በሚች ያገቡ ሴት ልጆች ፣ወንድ ልጆቹ፣ አጎትና የአጎት ልጆች ብዛት ነው።

የሚች ልጆችና ዘመዶች ዘፈኑንና የሚቀጠቀጡ ከብቶችን ይዘው ሲመጡ ቀደም ብሎ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ የሚያቀርብላቸው ሰውም የሚመደበው በዚሁ ወቅት ነው። ሌሎች ዘመዶች ደግሞ ለጭፈራ እና የሚችን ማህበራዊ ደረጃ ሊያሳዩ የሚችሉ ቁሶችን ከያሉበት ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል። በዚህም "ሴላ" ወይም ሲላ የምትባል ወፍጭራ፣ ካባ፣ ጡሩንባ ወይም "ፔሌች"፣ ጋሻ ወይንም "ሎዋን"፣ ጦር ወይም "ሊያች" በእግር ላይ የሚደረግ ቃጭል ወይም "ይሻ" ጠመንጃ፣የጉሬዛ ወይም የዝንጀሮ ፀጉር እና የመሳሰሉት የመከወኛ ቁሶች ይዘው ይመጣሉ።የቀብር ጉድጓድ የትና በማን እንደሚቆፈር በሚች ቤተሰብ የሚወሰነውም በዚሁ ወቅት ነው።

ከዚህ በኋላ የመቃብር"ጆንግ"ቁፋሮ ይካሄዳል። የመቃብር ጉድጓድ የሚቆፈረው በሬሳ ሳጥኑ ልክ በመሆኑ የሬሳ ሳጥኑን በመለካት ከአዲሱ ቤት በር ፊት ለፊት ላይ ይቆፈራል። የቀብሩ ጥልቀት ከ1.50-2.00 ሜትር ሊደርስ ይችላል። ከዚህ በኋላ የሚች ልጆች እና በቀብሩ ላይ ከብት የሚቀጠቅጡ ሁሉ ጥቁር ካባ በመልበስ በእግራቸው ቃጭል በማድረግ፣ ጦር እና ዘንግ በመያዝ የሲላ ላባውን ከጉሬዛው ፀጉር ጋር አድርገው ጭንቅላታቸው ላይ በማድረግ ይዘጋጃሉ። ሴቶችም ጥቁር ካባ እና "ጆን" በመባል የሚጠራ በዘፈን ወቅት የሚለበስ ከፍየል ቆዳ የተሰራ ልብስ በልብሳቸው ላይ በማሸረጥ ጋሻ በመያዝ ለዘፈን ይዘጋጃሉ። የቀሩት የሚች ቤተዘመዶች ጥይት፣ ጡሩንባ ወይም ፔሌች እና የመሳሰሉትን ቁሶች ይይዛሉ።



ምስል 3፡ የቀብር ጉድጓድ ሲቆፈር የሚያሳይ



ምስል 4፡ የቀብር ጉድጓድ ከተቆፈረ በኋላ

ጭፍራው የሚጀመረው አስከሬኑ ያለበትን ቤት ሦስት ጊዜ በመዞር ነው። ይህን ለምን እንደሚፈፅሙ አቶ ሜሪጊት ታምራት የተባሉ መረጃ አቀባይ

ጭፈራው አስከሬን የተቀመጠበትን ቤት ሦስት ጊዜ በመዞር ነው የሚጀመረው። ይህ ደግሞ አንድ ሰው ወይም ሚቹ ሳይገነዝ ሦስት ቀን ማቆየት በባህሉ የተለመደ በመሆኑ ሚች ባለው ክብር የተነሳ ለሦስት ቀን ሳይገነዝ መቆየቱን ለመጠቆም ነው። (20/08/2003/ዓ.ም ጅሙ ቀበሌ)

በማለት ገልፀዋል። ለጭፍራ እና ለዘፈን የሚመጣው የለቅሶ ተሳታፊ ላይ በእድሜ ወይም በፆታ ክልክልና ገደብ አይጣልም። በዚህም መሠረት የሀዘን መግለጫ ካባ እንዲሁም "ይሻ" ወይም ቃጭል በእግራቸው ያደረጉ በጭንቅላታቸው ላይ ደግሞ የጉሬዛ ወይንም የገሸንጆሮ ፀጉር እና የሲላ ላባ ወይንም "ሴላ" ያደረጉ እንዲሁም ዘንግ ወይም "ሊያች" እና ጡሩንባ ወይም "ፔሎች" እና ጋሻ ወይም "ሉዋን" የያዙ የሚች ቤተዘመዶች ጋር አብረው በመዝፈን እና በመጨፈር ይሳተፉሉ።



ምስል 5፡ የሀዘን መግለጫ ጭፈራ ከመጀመሩ በፊት አስከሬኑ ያለበትን ቤት ሲዞሩ የሚያሳይ



ምስል 6፡ ሀዘንተኞች የክክሲዳይ ሲያቀርቡ የሚያሳይ

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የመከወኛ ቁሶች የሚይዘውና የሚያደርገው ለሚች የቅርብ ዝምድና ያለው ሲሆን እያንዳንዱ ቁስም በአውዱ እና ከአውዱ ውጭ በብሔረሰቡ የተሰጠው ትርጉም አለ። ይህንን አስመልክተው አቶ ጥላሁን አይችሉ የተባሉ መረጃ አቀባይ

ይህ ጭንቅላቱ ላይ ያደርግሁት ሴላ ይባላል። የወፍ ላባ ነው። የሚደረገው ለጭፈራ ድምቀት ነው። ይህ ደግሞ ጡሩንባ ወይም በእኛ ቋንቋ "ፔሌች" ይባላል። ከቀርከሀ የተሰራ ነው። ለዘፈኑ ማድመቂያ ይሆናል። ይህን ጡሩንባ የሰማ ሁሉ የሞተው ሰው በጭፈራ እየተገለፀ ነው ብሎ ይረዳል። "ሊያች" የሚባለው ይህ ዘንግ ደግሞ የሚያዘው በሚች የቅርብ ዘመድ በልጆቹ እና በቀብሩ አለት ከብት በቀጠቀጡት ሁሉ ነው። (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌለች ቀበሌ)



ምስል 7፡ የሐዘን መግለጫ ቁሳችን የያዙ ተሳታፊዎችን የሚያሳይ

እነዚህ ቁሶች የሀዘን ጭፈራ ከማድመቅ በዘለለ የየግለሰቦቹን ማንነት የማሳወቅ ሚናም አላቸው። ካባ አድርጎ፣ ዘንግ ወይም ፔሌች ይዞ፣ እንዲሁም "ሴላ" ወይም የሲላ ላባ በጭንቅላቱ አድርጎ በየትኛውም ቦታ ቢንቀሳቀስ፣ ይህ ሰው የቅርብ ዘመድ እንደሞተውና በቀብሩም ላይ ከብት የቀጠቀጠ መሆኑ ይታወቃል። በጭፈራው መካከል ከብት ይዘው የመጡ የሚች ዘመዶች ሁለት ሰዎች ከቀኝና ከግራ ሆነው ጆሮና ቀንዱን የያዙትን ከብት በድንጋይ ግንባሩን እስኪወድቅ ድረስ ይቀጠቅጡታል። ይህን በቢያጌሊች ቀበሌ 13/08/2003 ዓ.ም ለመመልከት ችያለሁ። ከብቶቹ ከወደቁ በኋላ ወንዶች በግራ እጃቸው ስር ወይም ቅጠል ይጥሉባቸዋል። የእነዚህን ተግባራት (የከብት የሚቀጠቀጥበትና በግራ እጅ ሳር የመጣሉን ሁኔታ) ለምን እንደሚያደርጉ ለጠየኩት ጥያቄ የተለያየና እርስ በእርሱ የሚጣረስ ምላሽ ነው ያገኘሁት። አቶ ታቶ ማርዶሮ የተባሉ መረጃ አቀባይ

ለሞተ ሰው ሲሆን ቀጥቅጠን ነው የምንገድለው። ይህም ሰውየው ስለሞተ ነው። ለቃልቻ መስዋዕት ስናቀርብ ግን ቃልቻው በህይወት ያለ ስለሆነ ክብቱን ሳናርድ በህይወቱ አፍንጫውን በእንጨት ከመሬት ጋር አጣብቀን እንገፈዋለን።ለሞተ ሰው ግን በድንጋይ ቀጥቅጠን ነው የምንገድለው። ሳር የምንጥለው ደግሞ አንጀቱ እንዲያምር ነው።(15/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)

አቶ ኢፍይቡሙ ደግሞ "ዝምድናችንን፣ ተቆርቋሪነታችንን እና የሚችን ክብር የምንገልፀው ክብት በመቀጥቀጥ ስለሆነ ነው ። በሞተው ክብት ላይ ሳር የምንጥለው ደግሞ ባህል ስለሆነ ነው"። በማለት (13/08/2003 ዓ.ም ቢያጌሊች ቀበሌ) ምላሽ ሰጥተውኛል። አቶ ችሩ አሩት የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ

ለሞተ ሰው በድንጋይ ቀጥቅጠን ነው የምንገድለው። ይህ ደግሞ ሚች ስለሞተ ነው። አይታረድም በእምነታችንም አይፈቀድም። ከዚህ በኋላ ግን አንገቱን በጦር ወግተን በሾርቃ ደሙን ቀድተን በሚች መቃብር ላይ እናፈሳለን። ስጋው ደግሞ ተጠብሶና ተቀቅሎ ሀዘንተኛው ይመገባል። በተቀጠቀጡት ክብቶች ላይ በግራ እጅ ሳር ወይም ቅጠል የሚጥል ሰው የተለየ ነው። እሱም ሚስቱ እርጉዝ የሆነችበት ነው። ይህም ደግሞ ክብቶቹ ቶሎ እንዲሞቱ ያደርጋል የሚል እምነት ስላለን ነው። (20/08/2003 ዓ.ም መኢኒት ሻሻ ወረዳ)

በማለት መረጃ ሰጥተዋል። ተቀጥቅጠው የተገደሉት ክብቶች ቶሎ ካልሞቱ ሲንቀሳቀሱ ደማቸው ወደሆዳቸው ፈሶ አንጀታቸውን ሊነካው ይችላል። ስለዚህ ቶሎ እንዲሞቱ በግራ እጅ ሳር ወይም ቅጠል ይጣልባቸዋል ያሉኝ ደግሞ አቶ ጓንጊ ቢደንጊ ናቸው።

የሚቀጠቀጡት ክብቶች አንጀታቸው በግልፅ እንዲታይና እንዲያምር የሚያደርግ ነው ብለን ስለምናምን ነው። የሚቀጠቀጡ ክብቶች አንጀታቸው ታይቶ ትንበያ ይካሄዳል። ሞራውም ክብት አምጥቶ ለቀጠቀጠው ሰው ሚስት በአንገቷ ይደረግላታል። ይህ ደግሞ እኛም ለክብርህ ክብት ቀጥቅጠንልሃል የሚል ነው። (21/08/2003 ዓ.ም ጀመ ቀበሌ)

ከላይ እንደተመለከተው ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች እንደተናገሩት ክብት የመቀጥቀጡ ስርዓት ለክብር፣ ለዝምድና መግለጫ እንዲሁም ለሀዘን መግለጫ የሚከወን ነው። በዚህ ጊዜ ሌላው የሚከናወነው ተግባር በዋነኛነት ጭፈራ ነው። ይህም በሴቶች እና በወንዶች ለየብቻ እንዲሁም በአንድነት ይከውናሉ። ሴቶች ለሟች ያላቸውን መገላ በከበሮ በመታጀብ የሚቀርብበት ስልት በብሔረሰቡ አጠራር "ካክሲዳይ" ይባላል። የወንዶችና ሴቶች በአንድነት የሚከውነት ደግሞ "ኮክሰዳይ" (ምስል 6ን ይመልከቱ) በመባል ይጠራል። እንዲሁም ክብት በቀጠቀጡ ሰዓት ክብቱ የሚያሰማውን ድምጽ ተከትለው "ቦረሊዳይ" ወይም ፉከራ ይከወናሉ። ሴቶች ጋሻ ወይም ሎዋን ይዘው ካባ ለብሰው እንዲሁም ጆን ወይም ከፍየል ቆዳ የተሰራ ልብስ አሸርጠው ፀጉራቸውን ቀይ አፈር ወይም "ወኤች" ባጎሎ ለውሰው በመቀባት

እና የተለያዩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በመያዝ ክብ በመስራት (ክብ ሁለትም ሦስትም ሊሆን ይችላል) ይዘፍናሉ። ወንዶችም በፊናቸው ጥይት በመተኮስ እና ጡሩንባ በመንፋት ቤቱንና ግቢውን በመዞር

መኢኒትኛ	አማርኛ
ባርቴ ከረን ከዳሚ	አባቴ አፈር ይቅለልህ
ባድያኛ ዘልፈይ ከበድ	እኔ አለሁ ልጅህ
ባድያኛ ጠረበጅ ቱማ	በጠጠርማው በራ ቀብርህ
ክእኘየኝ ስጠራጌ	ይኸው ፈጽሜዋለሁ
ባድያንኛ ከነጀርጌ	ሚች የኔ አባት ገዳይ ነው
ባዲያንቼ ችምወርኬ	አርሶ አደር ገበሬ ነበር
ቀበል	ረሃብ የማያስደርስ

ሚች ሴት ብትሆን ደግሞ

መኢኒተኛ	አማርኛ
ሸማይ ዴ ጋይ	እናቴ ያለኝን አሟጥጬ
ከቼማጌኝ ሴኛ ስዩ	ለቀብርሽ አውየዋለሁኝና
ኦ ከጋጅ ከቸማጌኛ	ከዚህ በኋላ ሰርቼ እንድናር
ግላሎች ናይ ሃይድያቼ	እድሉን ስጪኝ

በማለት በከፍተኛ ድምቀት ይዘፍናሉ ይጨፍራሉ።



ምስል 8፡ በመከወኛ ቁሶች ታጅበው የሙገሳ ዘፈን ሲያቀርቡ የሚያሳይ

በዚህ ወቅት አስከሬኑን ወደቀብር ቦታ የሚያመጡ ሰዎች ስም እየተጠራ እንዲያመጡ ይደረጋል። አስከሬኑ ከአዲስ ቤት የሚወጣው በአዲስ በር ነው። ሚች ከህያዋን ጋር አንድነት የለውም ተለይቷል በሚል። ከዚህ በኋላ የቀብር ስርዓት ይፈጸማል። ጉድጓዱን መጀመሪያ አፈር በመቀጠል ድንጋይ በመጨረሻም አፈር በማድረግ ይሞሉታል። ይህ ደግሞ የሚችን የህይወት ዘመን ልጅነቱን ወጣትነት እንዲሁም እርጅናውን የሚያሳይ መሆኑን አቶ መልኬ ኬሰጊ ገልፀውልኛል። በዚህ ጊዜ የሚች ቤተሰቦች በተለይም ሴቶቹ አምርረው ያለቅሳሉ። ከቀብር በፊት እቤት ውስጥ ተቀምጠው የነበሩት የሚች ልጅ ሚስቶች ቀና ብለው ሰው ሳያዩ በቀብሩ ዙሪያ ይቆማሉ። ከበሮ እየመቱ እንዲሁም ሚች በህይወት ዘመኑ ቡንጡላ ወይ ጨሞ ይጠጣበት የነበረውን ሾርቃ ወይም የቅል ክፋይ ይዘው አፈር እስኪመለስበት ድረስ ይቆማሉ። ቀና ብለው ካዩ "ቃልቻ ይቆጣና ይገድላቸዋል" የሚል እምነት በመኖሩ።

በመጨረሻም ሚች ትልቅ ሰው በመሆኑ በቀብሩ ላይ አፈርና ድንጋይ ይቆለላል ለምልክትነት ከብቶቹ የተቀጠቀጡበት ድንጋይም በቀብሩ ላይ ይደረጋል። የሚች ቡንጡላ ወይም ጨሞ መጠጫ ሾርቃ ወይም የቅል ክፋይም በቀብሩ ላይ ይደረጋል። በብሔረሰቡ እራሱን የቻለ ሾርቃ የተዘጋጀለት ሰው ትልቅና የተከበረ ነው። በቀብሩ ላይ መቀመጡም የሚችን ትልቅነት የሚያሳይ ነው።

4.1.1.2.3 ድኅረ ቀብር ዝግጅቶች

ይህ ወቅት ቀብር ከተፈጸመ በኋላ የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆ እስከሚፈርስ ባለው ጊዜ የሚደረጉ ክንውኖችን ይመለከታል። ከቀብር በኋላ የሚደረጉ የተለያዩ ክንውኖች አሉ። ሀዘንተኞች ሲደክማቸውም ከተዘጋጀው ምግብና መጠጥ እየተመገቡ ጭፈራቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ጊዜ ተቀጥቅጠው የተገደሉ ከብቶች (ቀድሞ የተገፈፉ ከብቶችም አሉ።) ይገፈፋሉ። ከመገፈፋቸው በፊ በእግራቸው መካከል ጦርና ዘንግ አንድ ሽማግሌ ከብቱን ከቀጠቀጠው ሰው ጋር በመሆን ያዙራሉ። ይህ ደግሞ በብሔረሰቡ አንጀቱ በትክክል እንዲነበብ የሚያደርግ መሆኑ ይታመንበታል። የከብቱን ቆዳ ከገፈፉ በኋላ ስጋውን ለተሳታፊዎች ተጠብሶና ተቀቅሎ እንዲቀርብ ያደርጋሉ። ሚች በቆዳው የተገነዘበትን ከብት ስጋ የሚበሉት የሚች ልጆች ብቻ ናቸው። ወራሽነታቸውን፤ ተተኪነታቸውን ለመግለፅ። በዚህ ወቅት የሚጠበቀው ሌላው ተግባር አንጀት ማንበብ ነው። አቶ ዋየች ጃሻ የተባሉ

አንጀት የማንበብ እውቀት ያላቸው መረጃ አቀባይ የቀብር ሥርዓት ላይ ተገኝተው አንጀት በማንበብ በሚች ቤተሰቦችና ከብቱን በቀጠቀጠው ሰው ላይ ወደፊ ምን ሊመጣ እንደሚችል ሲናገሩ ተመልክቻለሁ።

ከቀብር በኋላ የሚከወነው ሌላው ተግባር የሬሳ መጠበቂያ ጎጆ ሥራ ነው። ይህን ጎጆ የሚሰሩት የሚች ቤተዘመዶች ሲሆኑ የሚሰራውም በቀብሩ ማግስት ነው። ጎጆው የሚሰራው ለየትኛውም ሰው እንደሚደረገው "ቃምጡት" ወይም ቡዳ አስከሬኑን እንዳይወስደው ለመጠበቅ ነው።የሚቆየውም ለሶስት ወራት ነው። ይህን ሀሳብ አስመልክተው አቶ ተፈራ ኮርዲ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆው ለሦስት ወራት ይቆያል። ቤቱ የሚሰራው "ቃምጡት" ወይም ቡዳ ስሚባል ነገር ለመጠበቅ ነው። ቃምጡት ሲመጣ ኃይለኛ ንፋስ ይነፍሳል በአካባቢው ክዛም መቃብሩ ወደታች ይሰረጉዳል ይህ ምልክቱ ነው። ለዚህ ነው ሦስት ወር ሰራ እንኳን ቢኖር በየተራ የምንጠብቀው። (15/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)*

አስከሬኑን የጥበቃ ጊዜና "ቃምጡት" ሲመጣ የሚያሳየውን ምልክት ገልፀዋል። የአስከሬኑን መጠበቂያ ጎጆው ከተሰራበት ጊዜ ጀምሮ በቀብሩ ዙሪያ ጠዋት ጠዋት ቡንጡላ ወይም ጨሞ እንዲሁም ቦርዴ (ካለ) ወተት የመሳሰሉትን ያፈሳሉ። "ከአያኝዋ ነበበይ ከያኝዋ ቲካትበይ ከሜንጊያ ጌችስ"(ስትጠጣ የነበረውን ቡንጡላ ሰጥቼሀለሁ። ቆሌህ ወደኛ እንዳያየን፣ ሰላም ስጠን) በማለት ቀብሩን እየዞሩ ሥርዓቱን ይፈፅማሉ። ቦታውን ለቀው ወደሌላ አካባቢ ቢሄዱም መጀመሪያ ለእናቱ/ለአባቱ በማለት ወደ መሬት ያፈሳሉ። እንዲህ ሳያደርጉ እነሱ አይቀምሱም። "እናንተ እየጠጣችሁ ለኔ ሳትሰጡኝ ቀራችሁ በማለት ይወቅሰናል" ብለው ያምናሉ።

ከሦስት ወር በኋላ እንደ ሚች ልጅ የአቅም ሁኔታ ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ በልቅሶው ላይ የተሳተፉ ሁሉ በመምጣት በጎጆ ማፍረሱ ላይ ይሳተፋሉ። ከዚህ በኋላ ሽኝተንሃል ሰላም አውርድልን በማለት እየዘፈኑና እየጨፈሩ የመጨረሻ ስንብት ያደርጋሉ። ለማስታወሻነትም ዋርካ በመቃብሩ ላይ ይተክላል። ዋርካው ፀድቆ የአቶ /የወ/ሮ እገሌ ቀብር በሚል ታሪክና ይዞታን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማቆየት የሚረዳ ተግባር መሆኑን የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ገልፀዋል ከነዚህም ውስጥ አቶ ኤርምያስ አኛኝ

> *ዋርካ ይተክላል በቀብሩ ላይ። ሲፀድቅ በሚች ስም የእከሌ ዋርካ ተብሎ ነው የሚሰየመው። ለወደፊት ዘርማንዘሮቹ እኛ የእከሌ ዘር ነን ዋርካው እንኳን ይመሰክራል ይላሉ። ሴቶች ልጆችም ባል አግብተው ለወለዷቸው ልጆች የአያታችሁ*

ቀብር እያሉ የአያቶቻቸውን ታሪክም ያስተምሯቸዋል። (13/08/2003 ዓ.ም ቢያኒሊኝ ቀበሌ)

በማለት በቀብሩ ላይ የሚደረግን ማስታወሻ አስመልክተው መረጃ ሰጥተዋል። በዚህ ጊዜ ሚች የተናዘዘው ቃል ተፈፃሚ ይሆናል። ወራሾችም የተሰጡትን ንብረት በማስተዳደር የሚችን ትዕዛዝ መፈፀም ይጀምራሉ።

4.1.2 ባህላዊ ስልጣን

በብሔረሰቡ መንፈሳዊና ባህላዊ አስተዳደር ጉዳዮችን አጣምረው የመስራት ሥልጣን ያላቸው አካላት አሉ። እነዚህ ቃልቻዎች ወይም "ኔሬይ" በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ አላቸው። ስለሆነም በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመፍታትና ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን በማስፈፀም ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው። ይህ በማህበረሰቡ ያላቸው ሚናም የለቅሶ ሥርዓታቸውን ይወስነዋል። የጎሳ መሪዎችም በየጎሳ አባሎች የተለየ ቦታና ክብር ይሰጣቸዋል።

4.1.2.1 ባለቃልቻዎች "ኔሬይ"

የአመኢነት ብሔረሰብ የቃልቻ እምነትን ይከተላል። በመሆኑ ኔሬይን ጠባቂ እና አዋቂ አድርጎ ያምናል። በሽታ ሲከሰት ከዶሮ እስከ ኮርማ ድረስ ለቃልቻ መስዋዕት በማቅረብ ይለማመናል። ሰው ያለአግባብ ቢበደል አቤቱታ የሚያቀርበውም ለሚያምንበት ቃልቻ ነው። ፀብ ቢፈጠርም ፀቡን ከማህበራዊ ሸንጎ ጋር በመተባበር ባለቃልቻዎች ይፈቱታል። የሰረቀ፣ ከትዳሩ ውጭ የባለገ፣ እና የመሳሰሉትን ጥፋቶች የሰራ ሰው ቃልቻ "መጥፎ ፍርድ ይጥልብኛል" ሲል እኔ ክፉ ነገር አድርጌያለሁ በሚል ለሽማግሌዎች ጥፋቱን ምንም ሳይደብቅ ይናገራል። በብሔረሰቡ እምነት ቃልቻ "እንኳን የተሰራውን በልብ ያለውን መርምሮ የሚያውቅ ነው።" በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ቃልቻ አስተዳዳሪና "ጠባቂ ምርት የሚሰጥ የሁሉ ነገር አድራጊ ፈጣሪ" መሆኑ ይታመንበታል። እያንዳንዱ ጎሳም የራሱ ቃልቻ አለው። ታዲያ ይህ ባለቃልቻ ወይም ኔሬይ ሲሞት የለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀሙ ከሌላው ሰው በተለየ ይከወናል። ዝግጅቶቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

4.1.2.1.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት

የአንድ ባለቃልቻ የስልጣን ዘመን የዕድሜ ልክ ነው። ነገር ግን በጠና ቢታመምና ለሞት ቢደርስ አዲስ ቤት አይሰራለትም ቀድሞ በነበረበት ቤት ይሆናል። ቀድሞም የተመረጠ የተከበረ በአጠቃላይም እንደ ልዕለሰብ የሚታይ በመሆኑ ነው። እዛው ቤት ቢሞትም አዲሱ ባለቃልቻ እቤት በመግባት ስራውን የሚጀምረው ከሦስት ወራት በኋላ በመሆኑ የሚች መንፈስ ይወጣል ተብሎ ይታመናል።

4.1.2.1.2 ጊዜ ሞት ዝግጅቶች

ባለቃልቻው ነፍሱ ከስጋው ስትለይ ጠባቂዎቹ መሞቱን ካረጋገጡ በኋላ ለማንኛውም ሰው እንደሚደረገው "የመጨረሻ ስንቅ" በማለት ወተት በአፉ አድርገው ዘቅዝቀው ያስተኙታል። ምንም አይነት የሀዘን ድምጽ ሳይሰማ የሥልጣን ሽግግር (ውርስ) እንዲፈፀም ያደርጋሉ። ሂደቱ ደግሞ የጭፈራ ድምፅ ሳያሰሙ በቃልቻው የሚያምኑ ሁሉ አስከሬኑን በመሀላቸው በማስቀመጥ እያንዳንዳቸው ግራዋ በመያዝ እና በማጨብጨብ በሌላ ሰው ላይ እንዲወርድ ይለማመናሉ። ቃልቻው በሌላ ሰው ላይ እስካልወረዳ ድረስ ቀብሩ ሳይፈፀም 4-6 ቀናት ሊቆይ ይችላል። አቶ አወቀ ፎርሽዋ የተባሉ መረጃ አቀባይ ኔሬይ ሲሞት የውርስ ሥርዓት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ

> *ግራዋ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ይሰጥና ይያዛል። ለቅሶ ወይም ጭፈራ አይካሄድም። ዝም ነው የሚባለው። በጭብጨባ እባክህን ውረድል እና ሬሳውን እንቅበር እየተባለ ይለመናል። ከዚያ ከተሰበሰበው መሀል አንዱን መርጦ እያንቀጠቀጠ ይወስደውና ያንራል። ከዚያ ሟችን እንቀብራለን። (18/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ) በማለት አስረድተዋል።*

አቶ አወቀ ፎርሽዋ አገላለፅ የቃልቻው መንፈስ ከሟች ልጆች ውጭም የሚይዝበት አጋጣሚ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል። ነገር ግን ትክክለኛውንና መንፈሱ ያረፈበትን ሰው እስኪገኝ ድረስ አስከሬኑ አይቀበርም። ምክንያቱም በቃልቻው የሚያምኑ ሁሉ "ያለ መሪና ያለጠባቂ" እንዳይቀሩ ስለሚሰጉ ነው። መንፈሱ ሳይወርድ አስከሬኑ ቢቀበር "የቃልቻው መንፈስ ይጠፋል" የሚል እምነት በመኖሩ።

አቶ ብርሃኑ ወርቁ የተባሉ መረጃ አቀባይ ከእፅዋት ሁሉ ግራዋ የተመረጠበትን ምክንያት ሲገልፅ "ግራዋ ያው ከጥንት ጀምሮ የመጣ ነው። ምልክትነቱ ንፅህና የሚያስገኝ ነው የሚል

ነው። የቃልቻ መጠቀሚያ ሁሉ በግራዋ ይታጠባል" በማለት ገልፀዋል (17/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)።

አቶ ጳውሎስ ክፍሌ የተባሉ መረጃ አቀባይ መንፈሱ ያረፈበትን ሰው እንዴት ማወቅ እንደሚቻል ለቀረበላቸው ጥያቄ

> *በቃልቻ መንፈስ ውርስ ላይ የሚች ልጅ ስለሆነ ብቻ የአባቱን ሥልጣን አይወርስም።የቃልቻው መንፈስ በልጁ ላይ አርፎ ያስገዝፈዋል ወይም ያንቀጠቅጠዋል። ያስጓራዋል። በዚህ ጊዜ እውነተኛ መንፈሱ ያረፈበት ሰው መሆኑ ይታወቃል (17/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)።*

በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። የስልጣን ሽግግሩ ካበቃ በኋላ እንደ አዛውንቶች ተገንዞ የሚቀበረው በታላቅ ወንድምየው በራፍ ላይ ነው። ይህ ደግሞ የቀድሞው ባለቃልቻ የኖረበትን ቤት አዲሱ ባለቃልቻ ስለሚቀመጥበትና አስከሬን ባለበት አካባቢ ቃልቻ ስለማይቀመጥ ነው።

አዲሱ ባለቃልቻ ወይም ወራሽ ወደ ቀብር ቦታ አይሄድም። ጎጆ ተሰርቶለት ከሽማግሌዎች ጋር ይቀመጣል። ወደ ቀብር ቦታ ከሄደ ያረፈበት መንፈስ ይሄዳል። ወራሹም ይሞታል ተብሎ ይታመናል።

ተሳታፊዎች ከዚህ በኋላ ለትልቅ ሰው እንደሚከወነው ሁሉ በተለያዩ የሀዘን መግለጫ ቁሶች በመታጀብና በመጨፈር ሀዘናቸውን ይገልፃሉ። የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ቀድሞ ስለሚደረግ በዚህ ሰዓት እየተመገቡና እየጠጡ ድካማቸውን እያስታገሱ ጭፍራውን ይቀጥላሉ።



ምስል 8፡ የመከወኛ ቁሶችን ለዝግጅቱ ሲያመቻቹ



ምስል፡ 9 የሀዘን ጭፈራ ሲከውኑ

4.1.2.1.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች

በዚህ ጊዜ ለአዲሱ ባለቃልቻ ሚቹ ባለቃልቻ ይጠቀምባቸው የነበሩ አምባር የእግር ጌጥና የአንገት ጨሌዎች ይደረጉለታል። ወራሽነቱን ለማሳወቅ። በቀብሩ ላይም የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆ የሚሰራው በዚህ ወቅት ነው። አዲሱ ወራሽ ከተሰራለት ጎጆ የሚወጣው በሦስት ወሩ ነው። በተመሳሳይ የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆውን አፍርሰው አቃጥለው በቀብሩ ለይ ዋርካ የሚተክሉት በዚሁ ወቅት ነው።

ወራሹ ከዳሱ ወጥቶ ወደቤት የሚገባው ከሦስት ወር በኋላ ነው። በዚህ ጊዜ የተለያዩ ሥርዓቶች ይከናወናሉ። ዳሱ ከመፍረሱ በፊት ከብት በድንጋይ እንዲቀጠቀጥ ይደረግና ከወደቀ በኋላ በስለት ይታረዳል። ወራሹ በከብቱ ደም ይታጠባል በዚህም ወራሹ ከህዘን ራሱን አንፅቷል የሚል እምነት አላቸው። በቀጣይነት ህዝቡን በመንፈሳዊ እና በአስተዳደራዊ ስልጣን ለመምራት ዝግጁ መሆኑን ያሳውቃል። በዚህ ጊዜ ባለቃልቻው የሚናገረውን አቶ ካሳ ከበደ እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> *ከህዘን መንፃት ሥርዓቱ በከብት ደም በመታጠብ ይፈፀማል። ከዚህ በኋላ ወደ ቦታው ይሄዳል። በዚህ ጊዜ ቃልቻው የወረደበት ሰው ይለፈልፋል። አስተርጓሚውም ቃልቻ እንደተናገረው ወደቤታችሁ ሂዱ። በቀጠሮ በመምጣት ድሮ ለሟች መስዋዕት ታቀርቡበት በነበረ ቦታ ላይ እንገናኝ። በማለት የባለቃልቻው መንፈስ የተናገረውን ለእምነቱ ተከታዮች ይናገራል (20/08/2003 ዓ.ም ሻሻ ወረዳ)።*

ህዝቡም በመሉ ፈቃደኝነት ከመሪው የሚሰጡት ትዕዛዞችን በመፈፀም በእምነት እንደቀድሞው ሁሉ መሪያችን፤ ጠባቂያችን በማለት ይቀበሉታል። የታዘዙትንም ተግባራዊ ያደርጋሉ። በዚህ መልኩ የአንድ ባለቃልቻ የለቅሶ ሥርዓት ይጠናቀቃል።

4.1.2.2 የጎሳ መሪ "ኮሙሩት"

በመኢኒት በብሔረሰቡ የጎሳ መሪ ወይም "ኮሙሩት" በሚያስተዳድሯቸው ሰዎች ይከበራሉ። ምክንያቱም የጎሳ መሪዎች "ዝናብ የማዝነብ፣ ምርት እንዲመረትና ከብትም እንዲረባ ለማድረግ ፀሎታቸው የሚሰማላቸው የተመረጡ ሰዎች" መሆናቸው ይታመናልና። አንድ ጎሳ ህልውናው ተጠብቆና ታውቆ እንደ ጎሳ እንዲቆይ የመሪዎቹ ሚና ከፍተኛ ነው። የጎሳ መሪዎቹ የአባላቱን ደህንነትና ሰላም በማስጠበቅ፣ ፀብ ቢፈጠር በሽምግልና ፀቡን እንዲቆም የማድረግ ተግባር አላቸው።

የጎሳ አባላትን የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ከዚህ አለም በሞት ቢለዩ የተለያዩ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ድርጊቶች ይካሄዳሉ። ክንውኖቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

4.1.2.2.1 ቅድመ ሞት ዝግጅት

በዚህ ጊዜ የጎሳ መሪው መታመሙን ያወቁ ቤተሰቦቹ አዲስ ቤት ይሰሩና ይወስዱታል። አዲሱ ቤት የሚሰራበት ቦታ የሚወሰነው በታማሚ የጎሳ መሪ ቤተሰቦች ነው። ይሁን እንጂ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል (ከአዛውንቶች) የተለየና የተመረጠ ቦታ የለውም። ይህን ሀሳብ አስመልክተው አቶ ተፈራ ኮርዲ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *ይህ ቤት የሚሰራውና የሚመረጠው በሚች ቤተሰቦች ነው። አቅጣጫውም በምስራቅ ይሰራል። አስክሬኑ ሲወጣም ከአዲሱ ቤት አዲስ በር በስተምስራቅ በኩል ተሰርቶ ነው። ሲቀበር ግን የሚች እራስ ወደ ምዕራብ ሆኖ ይቀበራል። ይህ ሞቷል ዳግመኛ አንገናኝም የሚል ትርጉም አለው (15/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)።*

በማለት የአዲሱን ቤት አቅጣጫ አመራረጥ እና ይህንንም በማድረግ ረገድ ማን ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ነግረውኛል። የጎሳ መሪው በእድሜ ትንሽ ሊሆኑ እንዲሁም በጎልማሳነት እድሜ ሊገኙ ይችላሉ። ይህ ቢሆንም አዲስ ቤት ተሰርቶ ወደዛ የሚሄዱት ስለእድሜያቸው ትልቅነት ሳይሆን በማህበረሰቡ ያላቸውን ስልጣንና ክብር ለማሳየት ነው።

የጎሳ መሪው በአዲሱ ቤት ከገቡ በኋላ ልጃቸው አለዚያም አጎትና የአጎት ልጆች ይጠብቋቸዋል። መሞታቸው ከተረጋገጠ ወተት በአፋቸው አድርገው አንጋለው ያስተኟቸዋል።

4.1.2.2.2 ጊዜ ሞት ዝግጅት

በዚህ ጊዜ የጎሳ አባላቱን፣ የጎሳ መሪውን ዘመዶች እና የሚችን አማቾች (የሌላ ጎሳ አባል ሆነው በጋብቻ ግን ከሚች ጎሳ ጋር ዝምድና የፈጠሩትን) ሁሉ ለማስተናገድ የሚያስችል ከፍተኛ የሆነ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ይደረጋል። በዚህም ጎረቤቶች፣ ዘመዶችና የሚች ቤተሰቦች ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ከዚህ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የስልጣን ሽግግር ወይም የውርስ ሥርዓት አፈፃፀም ነው። ሚች ሀይወቱ ባለፈበት ወቅት ለኔሬይ እንደሚደረገው ሁሉ ቤተዘመዱና የጎሳው አባላት ምንም ድምፅ ሳያሰሙ ይሰበሰባሉ። ሥርዓቱ በምሽትም በቀንም ሊካሄድ ይችላል። አስክሬኑን

አዛውንት በሚገነዝበት ሥርዓት በልብስና በሚች ልጅ አልያም በአጎት ተቀጥቅጦ በተገደለ ከብት ቆዳ በመገነዝ "ቢራች" ወይም የአስክሬን ሳጥን ውስጥ ያስቀምጣሉ።

ከዚያ በኋላ የውርስ ስርአት ይፈጸማል ።አፈጻጸሙም ቤተዘመድ በመሉ ይሰበሰቡና አይናቸውን እንዲጨፍኑ ይታዘዛሉ። በመቀጠልም በእጃቸው መዳፍ ምንም ሳይዙ እንዲጨብጡ ይደረጋል። በዚህ ጊዜ ሁሉም ሰው የጎሳ መሪያቸውን ፈጣሪያቸው ቶሎ እንዲያሳውቃቸውና ጎሳቸው መሪ እንዲያገኝ ልባዊ ፀሎት ያደርጋሉ። በመካከልም አንድ ሰው የሰዎቹን እጅ እየዘረጋ አይናቸውን ሳይገልጡ ያያል። በብሔረሰቡ ይህ ሰው ቢዋሽና ትክክል ባይናገር "የቃልቻ ቅጣት ይደርስበታል" ተብሎ ስለሚታመን ያገኘውን ነገር ሳይጨምር ሳይቀንስ እንዲሁም ሳያዳላ ይገልፃል። የሰዎቹን እጅ እየዞረ በሚያይበት ወቅት ከሰዎቹ መሀል በአንዱ እጅ ላይ በጠጥ (የበግ ወይም የፍየል እዳሪ)፣ የአዝርዕት ፍሬዎች (ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ወዘተ) እና የተለያዩ የፍራፍሬ አይነቶች በእጁ የተገኘበት ሰው የጎሳ መሪ መሆኑ ይታወቃል። ከዚያ በኋላ ከብት ተቀጥቅጦ ይገደልና አንጀቱን በማንበብ ወራሹ ትክክለኛ ወራሽ ሆኖ የተመረጠ መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣሉ። ወራሽ መሆኑ ከተረጋገጠም በኋላ ሚቹ የጎሳ መሪ በእጃቸው ላይ ሲያደርጉት የነበረውን የጎሳ መሪነት መገለጫ አምባር እና የገዘፈን ጥርስ በአዲሱ የጎሳ መሪ ክንድ ላይ ይደረጋል።

ከዚህ በኋላ አዲሱ የጎሳ መሪ በነባሩ የጎሳ መሪ ስም ነው የሚጠራው። አቶ ኬሬ ሌጅ የተባሉ መረጃ አቀባይ የሻልዋ ጎሳ መሪ ሲሆኑ የስልጣን ሽግግሩን አስመልክተው፦

> *እኔ የሻልዋ ጎሳ መሪ ነኝ ይህን አምባር ያደረኩትም የጎሳ መሪ መሆኔን የሚገልፅ ነው። ስልጣኑን የወረስኩት ከአባቴ ነው። አባቴ እንደሞቱ ቤተዘመድ ተሰብስበን አይናችንን ጨፍነን እጃችንንም ጨብጠን ተቀምጠናል። በዚህ ጊዜ አንድ ሰውየ እየመጣ እጃችንን ያይ ነበርና በዚህ ሰዓት እኔ እጅ ላይ የተለያዩ እህሎችና በጠጥ ተገኝ ከዚህ በኋላ እኔ ተመረጥኩና የአባቴን ቦታ ተክቼ መስራት ጀመርኩ። በእኔም ላይ አባቴ የጎሳ መሪ እንደነበሩ ያደርጉት የነበረ አምባር በሽማግሌዎች ተደረገልኝ። (21/08/2003 ዓ.ም ጀመ. ቀበሌ)*

በማለት ራሳቸውን ዋቢ በማድረግ መረጃ ሰጥተዋል። ከዚህ በኋላ የሚች ዘመዶች አማቾችና ወንድ ልጆች ያመጧቸውን ከብቶች እየቀጠቀጡ ደማቸውን በሾርቃ ሚች መቃብር ላይ እያፈሰሱ የቀብር ሥርዓቱ እንዲፈፀም ይደረጋል። አቶ መንገሻ ወርቁ የተባሉት መረጃ አቀባይ

> *በዚህ ጊዜ እኛ ከብት ቀጥቅጠናል ዘመድ ነን እንላለን ዝምድናችንን እንገልፃለን። ይህ ደግሞ ዘመዶች ነን አንጋባም የሚል ትርጉምም አለው። ይህ ደግሞ የጎላውን አባላት*

ክፍ እንዲል ያደርጋል። አባላቱ ብዙ ከሆኑ ደግሞ ጎሳው በአጠቃላይ የመከበር እድል ያገኛል። ስለሆነም በጎሳ መሪው ለቅሶ ሥርዓት ላይ የሚገኘው ሰውና የሚቀጠቀጠው ክብት ብዛት በጎሳው አባላት እና አባላቱ ከሌላ ጎሳ ጋር ባላቸው የጋብቻ ዝምድና ይወሰናል (15/08/2003 ዓ.ም ድልኩብጣያ ቀበሌ)።

በቀብሩ ላይም ድንጋይና አፈር እንዲሁም የሚች መጠጫ የነበረ ሾርቃ ለምልክትነት ይቀመጣል። ከዚህ በኋላ ለለቅሶው ማስፈፀሚያነት የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ እየተበላና እየተጠጣ ተሳታፊዎች ቡራሊዳይ እያሉ ይቆያሉ። ቡራሊዳይ የሚል ሰው መጀመሪያ የሚያሞግሰው ራሱን ነው። ይህም እኔ ... (የሚች) ዘመድ ጀግና ነኝ ሚችም የጀግና ዘር ነው ለማለት ያስችላቸዋል።



ምስል 10፡ ቡሊንዳይ ሲከውኑ

መኢኒትኛ	አማርኛ	
አኛዳለከ በግቼ ኒሮ	እኔ ገዳይ ፒሮ ክሌመ	(የተራራ ሥም)
ብሉሚ ኮኖመንዳ	ተራራ ላይ ወጥቼ	
ማጭ ኩቱነ ተሪዮ	ጎሽን ወግቶ	
ካንጋዳ	ገዳይ	
በርቱ ትሪጁ ባሲዴ	የአባቱ ጦር ቀደም ሲል	
ወዴ ከአይ ሻንተናበይ	የወረስኩት በጀግንነት	
አዋን አጉት ኮንባሼ	አንበሳና ነብር	
ማጌ በረት ካሳ ኔን	የገደልኩበት ይታወቅልኝ	

በማለት ይፎክራሉ (ቡራሊዳይ) ይላሉ።

4.1.2.2.3 ድህረ ቀብር ዝግጅቶች

የጎሳ መሪዎች ሲሞቱ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል እንደሚደረገው ሁሉ በቀብሩ ላይ የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆ ይሰራል። በጎጆው ውስጥም የሚች ቤተሰቦች እንዲሁም ዘመድ አዝማዶች ሁሉ እስከ ሦስት ወር ድረስ ይጠብቃሉ። የሚች ቤተሰቦችም ቡና፣ ወተት የመሳሰሉትን በብሔረሰቡ የሚታወቁ ባህላዊ መጠጦችን በቀብሩ ዙሪያ ይደፋሉ።

አዲሱ የጎሳ መሪ ተቀጥቅጦ በተገደለ ከብት ደም ታጥቦ ከቀብር ስርዓቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወደስራው መግባቱን ለአባላቱ ያሳውቃል። አባላቱም የጎሳ መሪነት ሥልጣኑን አግኝቶ "ኮመሩት" ሆኗል በማለት ለቀደመው የጎሳ መሪ እንደሚያደርጉት ሁሉ ያደርጋሉ፤ ይቀበሉታል።

ከሦስት ወር በኋላ የሬሳ መጠበቂያው ጎጆ ሲፈርስ በቀብር ሥርዓቱ ላይ የተሳተፉ ሁሉ በመምጣት ለሚች የመጨረሻ ስንብት ከተዘጋጀው ድግስ በመመገብ ጎጆውን አፍርሰው ያቃጥላሉ። ይህም የመጨረሻ ስንብት ይሆናል።

4.2 ከአሚሚት ሁኔታ አንፃር

ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሊለይ ይችላል። ከነዚህ ምክንያቶች መካከል የተለያዩ በሽታዎች፣ የሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ተጠቃሽ ናቸው።እነዚህ ምክንያቶች በሚች የለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀም ላይ የራሳቸው የሆነ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም።

በመኢኒት ብሔረሰብ አንድ ሰው በማንኛውም አይነት በሽታ እና በተፈጥሮ አደጋ ቢሞት በሚች ማህበራዊ ደረጃ መሠረት አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተሟልቶ የለቅሶ ወይም የጭፈራ ሥርዓቱ ይከናወናል። ነገር ግን አንድ የብሔረሰቡ አባል የሆነ በሰው ቢገደል የለቅሶ ሥርዓቱ ከዚህ ቀደም ከተገለፀው የሚለይበት ሁኔታ አለ።

4.2.1 በሰው ለተገደለ

ለመስክ ስራ ከመስክ ረዳቴ ጋር በመሆን ለጥናት በተመረጡት ሁለት ወረዳዎች በመዘዋወር አንዳንድ ሁኔታዎችን እየተመለከትኩ እግረመንገዴንም ማስታወሻ እይዛለሁ። በዚህ ጊዜ በየቀበሌ ገበሬ ማህበራቱ፣ በየወረዳዎቹ ከተማዎች እንዲሁም በተለያዩ መንደሮች ስንዘዋወር

በሁሉም ቦታ ማለት በሚያስችል ሁኔታ ማህበረሰቡ መጠጥ በተለይም ጠጅና ቦርዴን ለፍቅር መግለጫና ለመገናኛ ሲጠቀሙ ተመልክቻለሁ። "ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል" የሚለው ብሂል ትገ ቢለኝ ለመረጃ አቀባዮቼ በመጠጥ ሳቢያ የሚመጡ ግጭቶች ይኖሩ ይሆን የሚል ጥያቄ አቀረብኩ። በዚህም በመጠጥ ተገፋፍቶ ፀብ እንደሚፈጠር ይህ ደግሞ ስር ሰዶ እስከመገዳደል የሚደርስ መሆኑን ገለፁልኝ። አቶ ዋየች ጃሻ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *እኔና ወንድሜ በጨበራ ቀበሌ ጠጅ ሰንጠጣ ቆይተን በማይረባ ነገር ተነጋገርንና በጥፊ መታኝ። እንዴት ታናሼ አይደለህም እኔን እንዴት ትመታኛለህ ብየ በጩቤ ወግቸው ጥዬው ሄድኩ። በዚህ ሰዓት የሰራሁትን በውል አላስታውስም። ብቻ በጩቤ ወግቸዋለሁ። ከዚያ እቤት ሳልገባ እዛው ከተማ አድሬ ጠዋት ስነሬ ሲበርድ ወሬ ሰማሁ። በዚህም ወንድሜ ሀኪም ቤት ሳይደርስ መሞቱን አረጋገጥኩ። ከዚህ በኋላ የመቀበሪያ ከብት እንዲሰጥልኝ አደረግሁ። ይህን ባላደርግ ኖሮማ ሌሎች ወንድሞቼ ሚስቱንና ልጆቼን ይገድሉብኛል። እኔንም ካገኙኝ አይለቁኝም። በኋላም የራሴን ሴት ልጅ በአሻ እና ቀሪ ከብቶቼን ሰጠሁ። እኔንም መንግስት አሰረኝ። (14/08/2003 ዓ.ም ዱማ ቀበሌ)*

በማለት የራሳቸውን ተሞክሮ ዋቢ በማድረግ ገልፀዋል። በብሔረሰቡ አንድ ሰው ከሰው ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ፀብ ውስጥ ሊገባ ይችላል። ለጊዜው የፀቡ መነሻ ወይም ፀቡ ትኩረታችን ባለመሆኑ ከፀቡ በኋላ የሚከተለው የሞት አደጋ ላይ የሚታይ የለቅሶ ሥርዓት ምን መልክ አለው ወደሚለው እንሂድ።

አቶ ኬለጊ ማናቻ የተባሉ መረጃ አቀባይ አንድ ሰው በሰው ቢገደል የለቅሶ ሥርዓቱን አፈፃፀም አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ

> *ሟች የሞተው በሰው ከሆነ "አሻ" ካሳ እስኪከፈል ድረስ አይቀበርም፤ አይለቀስም። ወይም አይጨፈርም። ምክንያቱም ሳይገነዝ በፊት እነዚህ ሥርዓቶች አይፈፀሙም። አሻው ካልተከፈለ የሟች ወገኖች የገዳይ ጎሳ አባል የሆነን ማንኛውንም ሰው ለግድያ ያፈላልጓቸዋል። ስለዚህ አሻው ቶሎ መክፈል አለበት። ከዚህ በኋላ ነው የለቅሶ ሥርዓቱ የሚፈፀመው። "የአሻ" ክፍያውን በአንድ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ የመክፈያ ቀን በሽማግሌዎች ይወሰናል። ከዚህ በኋላ የቀብር ሥርዓቱ ይፈፀማል። (20/08/2003 ዓ.ም ሸርሸር ቀበሌ)* በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

በሰው የተገደ ሰው እንደሞተ አይለቀስም ወይም አይጨፈርም። ይህ ከሆነ የሟችን ዘመዶች የሚያስገምትና የሚያስንቅ ነው። ስለዚህ የገዳይ ወገኖችን ከያሉበት በመፈለግ ለመግደልና ደማቸውን ለመወጣት በከፍተኛ ሁኔታ ይነሳሉ። በዚህ ጊዜ ሟች አይቀበርም። የሟች ቤተሰቦች ባላሰቡትና ባልተዘጋጁበት ወቅት ሰው ስለሞተባቸው ገዳይ በመጀመሪያ የመቀበሪ ከብት በሽማግሌዎችና በጎሳ መሪዎች ወይም በ"ከሙሩት" እንዲሰጥ ይደረጋል። የሟች

ወገኖችም ጉዳዩ በሽማግሌዎች መያዙን ስለሚያውቁ በተሰጠው የመቀበሪያ ክብት ቆዳ አስከሬኑን ይገንዛሉ።የመገነጊያ ልብስ ሳያዘጋጁ ስለሞተባቸው።

ከዚህ በኋላ አስፈላጊውን የምግብና የመጠጥ እንዲሁም የቁሳቁስ ዝግጅት አድርገው እንደሚች ዕድሜ እና የስልጣን ሁኔታ ለቅሶ ወይም ጭፈራ ይጀምራሉ። ቀብሩንም ይፈፅማሉ። በሁለተኛው ቀን የአስከሬን መጠበቂያ ጎጆውን በመስራት ዘመዶች አስከሬኑን ይጠብቃሉ። በሦስተኛው ቀን የገዳይ ወገኖች ለካሳ ወይም "ለአሻ" የሚከፈሉ ቀሪ ክብቶችን እና አንድ ልጃገረድ ይዘው ሽማግሌዎችን በማስቀደም ከወንዝ ማዶ ይሆናሉ። ከወንዝ ወዲህ ደግሞ የሚች ቤተሰቦችና ሽማግሌዎች ይቆማሉ። በዚህ ጊዜ ቀሪ ክብቶቹን እና በካሳ የምትሰጠውን ልጃገረድ የገዳይ ቤተሰቦች ለሚች ቤተሰቦች ይሰጣሉ።

ከዚህ በኋላ ክብት ታርዶ የወተት አንጀቱን ሁለቱም ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጫፍና ጫፍ በጥርሳቸው ወጥረው እንዲይዙ ከተደረገ በኋላ እኩል ቦታ በሽማግሌዎች ተቆርጦ ድርሻቸውን እንዲበሉ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ በግ በማረድ ደሙን ቀድተው በሾርቃ በማድረግ በሁለቱም ወበኞች በኩል ያሉ ሰዎች በአንድ እንዲጠጡ ይደረጋል። ፍፁም የሆነ እርቅ መፈፀማቸውን ለማሳየት የማሽላ ገንፎ የሚቀርበውም በዚሁ ወቅት ነው። በብሔረሰቡ የዘወትር ምግብ ሆኖ የሚያገለግለው የበቆሎ ገንፎ ነው። ለእርቅ ማስፈፀሚያነት የማሽላ ገንፎ የሚቀርበው ማሽላ ከተቆረጠ በኋላ እንደገና የማቀጠል (ከእንደገና የመለምለም) ተፈጥሮ ስላለው፤ በቆሎ ግን አንዴ ከተቆረጠ ስለማያቀጥል ነው። ስለዚህ የማሽላ ገንፎው ትዕምርቱ ሰው ቢሞትም በካሳ ወይም በ"አሻ" በተሰጠችው ልጃገረድ የሚች ዘር ይተካል። ሚችም እንደሞተ አይቆጠርም ምክንያቱም በ"አሻ" የተሰጠችውን ሴት የሚች ወንድም ያገባታልና የሚል ትርጉም ይሰጠዋል።

ከዚህ በኋላ ሦስት ወር ሲሞላ ለማንኛውም ሚች እንደሚደረገው ድግስ ተደግሶ የሬሳ መጠበቂያ ጎጆ እንዲፈርስና እንዲቃጠል በማድረግ የለቅሶ ሥርዓቱ ማሳረጊያ ይሆናል።

4.3 የመኢኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ማህበራዊ ተግባራት

የመኢኒት ብሔረሰብ ለዘመናት ሲከውነው የቆየ እና አሁንም ተግባራዊ እያደረገው ያለው የራሱ ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት አለው። ይህ የለቅሶ ሥርዓት ከማህበረሰቡ እምነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እና አመለካከቱን የሚያንፀባርቅበት ነው። የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔው

ማህበራዊ ኑሮን በማጠናከር እንዲሻሻልና የበለጠ እንዲያድግ የማድረግ ታሪክንና ባህልን ለመጭው ትውልድ የማስተላለፍ እንዲሁም ማህበራዊ ተቋማትን የማጠናከር ጠቀሜታ አለው።

4.3.1 ታሪክን ከማቆየት አንፃር

ፎክሎር በመከወን፣ በመነገር፣ በመዜም እና በመሳሰሉት የመተላለፊያ መንገዶች ከትውልድ ትውልድ ከዘመን ዘመን ይሻገራል። በሂደቱ የተለያዩ ለውጦችን ማስተናገዱም አይቀርም። አንድ የፎክሎር ዘውግ ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች አሁን አሁን ደግሞ በመፃፍ (የተሟላ ክዋኔ የሚያሳይ ባይሆንም) ሲተላለፍ በውስጡ አብሮ ይዞ ከዘመን ዘመን የሚያዛልቃቸው ጉዳዮች አሉ።

ከነዚህ ጉዳዮች መካከል ታሪክ አንዱ ነው። በአንድ ወቅት የተደረገን ጉዳይ፣ ሥልጣኔን፣ ግዛት፣ የተፈፀመን ጀብድ እንዲሁም ድክመትንና የመሳሰሉት ሁነቶች ሁሉ ያለፈውን በመግለፅ የወደፉቱን ለመጠቆም የሚያገለግሉ የታሪክ ክፍሎች ናቸው። እነዚህን ጉዳዮች ለማሳየትና ለመራመድ መሠረት የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

በመሆኑም የመኢኒት ብሔረሰብ ባህል፣ ልማዳዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች እንዲሁም ይዘታን በነበሩበት ፀንተው እንዲቆዩ፤ በመልካምነት የተቀበላቸውንና ያፀደቃቸውን መልካም ምግባራት ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ከሚያደርግባቸው መንገዶች መካከል የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ አንዱ ነው። የለቅሶ ሥርዓቱ ሲከወን ታይቶ የሚተላለፍ ብቻ ሳይሆን በክዋኔ ተሳታፊዎች አእምሮ ውስጥ ዘልቆ ሊገባ የሚችል ጉዳይ በውስጡ ይዟል። በዚህ ወቅት የተለያዩ ቋሚነት ያላቸው ተግባራት (ክዋኔው ካለቀ በኋላም ያንን ክንውን ሊዘክሩ የሚችሉ) ይካሄዳሉ። እኒህ ደግሞ ታሪኩና ማህበራዊ ሥርዓቱ በዘላቂነት እንዲቀጥል የሚያስችሉ ቁም ነገር አላቸው።

በብሔረሰቡ አንድ ሰው ሲሞት የቀብር ሥርዓቱ የሚፈፀመው በግዛቱ ላይ ነው። ማንም በማንም ግዛት ወይም የእርሻ ቦታ መቀበር አይችልም። ሟች የትም አይቀርም አይወድቅም በህይወት ዘመኑ ባቆየው ወይም ባቆዩለት እርስት ይቀበራል። ይህም የአያት የቅድመ አያቱን ቅርስ በመጠበቁ "ያገኘው ዕድል" ነው። የመኢኒት ሴት ባል አግብታ ወደ ሌላ ጎሳ ትሄዳለች። በአጋጣሚ ከቤተሰቦቿ ቤት መጥታ ህይወቷ ቢያልፍ እናትና አባቷ ቤት አትቀበርም።

ምክንያቱም በባህሉ መሠረት ጥሎሹን እንዲመልሱ ስለሚደረግ አስከሬኗን አምጥተው ያስረክባሉ። ይህ ድርጊት ለሚች ልጆችና የልጅ ልጆች የታሪክ መሠረት ከሚጣልባቸው የባህል ተደጋግፎዎች አንዱ መንገድ ነው።

በብሔረሰቡ በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ እድሜው የፈቀደለት ማንኛውም ሰው የተለያዩ ተግባራትን በመከወን ይሳተፋል። ከተግባራቱ መካከልም ለምግብ ማብሰያ የሚሆን እንጨትና ውሃ ማቅረብ፣ ጉድጓድ መቆፈር፣ የቀብር ድንጋይ ማምጣት፣ ሀዘንተኞችን ማስተናገድ እንዲሁም ምግብ ማዘጋጀት ተጠቃሽ ናቸው። ሥርዓቱን በመንቀፍ አሊያም በቸልተኝነት የማይሳተፍ ቢኖር በማህበረሰቡ ዘንድ ይጠላል። አስፈላጊውን ክብርና ሞገስ አይሰጠውም። ለዚህም ነው በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት በከፍተኛ ትኩረትና ግምት የሚካሄደው።

በአንዛሩ ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት የተለያዩ ተግባራትን የሚወጣ ሰው የማህበረሰቡን አመኔታ ከማግኘት በዘለለ ስለባህሉ ስለታሪኩ የሚከወኑ ተግባራትን የማየትና የማወቅ እድልን ያገኛል። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከባህሉ ማፈንገጥ ታሪክ አልባ ያደርጋል። አቶ ተፈራ ከርዳ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *አንድ ትልቅና በብሔረሰቡ ክፍ ያለ ደረጃ ያለው ሰው ቢሞት አስክሬኑ ቶሎ አይቀበርም። ይህ የሚሆነው ለቅሶው ዝም ብሎ በጥቂት ድግስ መካሄድ ስለሌለበት ነው። በትንሽ ድግስ ልጆቹ እንቀብራለን ካሉ ታሪካቸው ይበላሻል። እነዚህ እናትና አባታቸውን በጭፈራና በድግስ ያልቀበሩ ባህል የሚያበላሹ በማለት ይሰደባሉ። ልጆቹም ይህን በመፍራትና የአባት የእናታቸውን ስም ለማስጠበቅ እርሻም ሆነ ንግድ ሄደው የሚያስፈልገውን ያሟላሉ። (15/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ቀበሌ)*

በማለት የሰጡትን መረጃ ስንመለከት የለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀሙ ታሪክን በማቆየት ረገድ ያለውን ትልቅ ሚና እንረዳለን።

በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚች ቤተሰቦች አካባቢያቸውን ለቀው ቢሄዱ የሚች አባታቸው ወይም እናታቸው ታሪክ እንዳይረሳ በማለት አስክሬኑ በተቀበረ ከሦስት ወር በኋላ በቀብሩ ላይ የሚተከል ዋርካ አለ። ይህ ለታሪክ አስረጂነት ይጠቀሙበታል።

ሌላው በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚታይና ታሪክን ለማቆየት የሚረዳ ተግባር አለ። ይኸውም ሚች በተለይም የእድሜ ባለፀጋ እና ብዙ አማቾች ያሉት ከሆነ ሲታመምና ህመሙ ለሞት ያደርሰዋል ተብሎ ሲታመን አዲስ ቤት እንዲገባ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ሚች አስፈላጊው ሁኔታ ተሟልቶ ይቀበራል። አዲሱ ቤት ግን አይፈርስም። የሚች ወንድ ልጅ የመጀመሪያ

ሚስቱን ይዞ ይኖርበታል። ይህ የአስከሬን ማውጫ ቤት ወይም "ጋህ" የሚችን ማህበራዊ ደረጃ የሚያሳይ ነው። ለማንም ሚች ይህ ቤት አይሰራም።

የሚች ልጅም እዚህ ቤት ውስጥ መቀመጡ በአባቱ መቃብር ላይ "ቡንጡላ" ወይም ጨሞ ለማፍሰስ ብቻ አይሆንም። ከዚህ የዘለለ ትርጉም አለው። ይህም የአባቱን ወይም የእናቱን የታላቅነትና ታሪክ ለማቆየት፣ ለመንገርና ለማሳየት የሚጠቅም ነው።

4.3.2 ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅ አንፃር

በዚህ ንዑስ ርዕስ የለቅሶ ሥርዓቱ በብሔረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውን ማህበረ ባህላዊ ተቋማት ለማስጠበቅ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ይዳሰሳል። በመኢኒት ብሔረሰብ ልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ተቋማቱ ማለትም አስተዳደሩ ዳኝነቱ፣ የቤተሰብ ህይወቱ ወዘተ. ሁሉ መሠረት ያደረጉት ባህላዊ እምነቱ ላይ ነው።

በብሔረሰቡ ዘንድ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማቱ (ባህላዊ አስተዳደሩ፣ ባህላዊ ሽምግልናው፣ የቤተሰብ ወይም የትዳር ህይወት ወዘተ.) ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸዋል። በመሆኑም የለቅሶ ሥርዓቱ አከዋወን ይህን ለማስጠበቅም ይካሄዳል።

ሃይማኖታዊ እና አስተዳደራዊ ተግባርትን ለሚወጡት ቃልቻዎች ወይም "ኔይሬ" መስዋዕት የሚቀርብ ከብት ሳይታረድ ቆዳው ይገፈፋል። ይህ ደግሞ ቃልቻው ያለ በመሆኑ ነው። በለቅሶ ሥርዓት ላይ የሚታረደው ከብት ግን በድንጋይ ተቀጥቅጦ ነው የሚገደለው። ይህ ደግሞ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድርጊቶችን ድንበር የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ሃይማኖታዊ ተቋማቱን የማስጠበቅ ተግባር አለው። የተለያዩ መረጃ አቀባዮች በሰጡት መረጃ መሠረት ሰው የቱንም ያህል ትልቅ ቢሆን የቃልቻን ያህል ክብር የለውም። ምክንያቱም ቃልቻ "ሁሉን የሚያደርግ፣ የሚሰጥ፣ የሚነሳ እና የሁሉ ነገር ምክንያት" ነውና።

ቃልቻዎች ወይም "ኔሬይ" የብሔረሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ ህይወትን ይመራሉ። ስለዚህ አንድ ሰው በባህሉ መሠረት ባለቃልቻ ሆኖ ሲመረጥ "ከተራሰው" የተለየ ይሆናል። በዚህም ከተፈጥሮና ከሰው ሰራሽ አደጋ እንደሚታደግ ይታመንበታል።

ተቋሙ የራሱ ሥርዓትና ህግ አለው። እነዚህ ሥርዓቶች ደግሞ እንዳይጣሱና ሀሰናዊ መቃወስ እንዳይፈጠር ይፈለጋል። ምክንያቱም ለመህበረሰቡ የህልውናው ዋስትና የማንቱ

መሠረት ነውና። እነዚህን ሥርዓቶች በማስጠበቅ ረገድ የተለያዩ ክዋኔዎች ይከወናሉ። ከእነዚህ ውስጥም የለቅሶ ሥርዓት አንዱ ነው። በመሆኑም አንድ ባለቃልቻ ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ሥልጣኑ ወይም የቃልቻው መንፈስ በሌላ የተመረጠ ሰው ላይ እስካላረፈ ድረስ ቀብሩ አይካሄድም። የሀዘን ጭፈራ ወይም ለቅሶ አይካሄድም። ይህ ከተደረገ "መንፈሱ ይጠፋል" የቃልቻው ተከታዮችም ያለጠባቂ ይቀራሉ ተቋሙም ይፈርሳል። ስለዚህ የለቅሶ ሥርዓቱ የቃልቻው መንፈስ ወደ ሌላ የተመረጠ ሰው እስኪያርፍ ድረስ አይጀመርም። በዚህ ጊዜም የሚታዩና የሚንባባረቁ ሃይማኖታዊ ክንውኖች ጭብጥም ይህንኑ (ተቋሙን) የማስጠበቅና የማጠናከር ሚና አላቸው።

መንፈሱ የመረጠው ባለቃልቻም ወደቀብር አይሄድም እንዲሁም አስከሬን ወደወጣበት ቤት አይገባም። ይህ "በላዩ ያረፈው መንፈስ ይጠፋል፣ ይሸሻል" ከሚል እምነት የመጣ ነው። እነዚህ ለለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚካሄዱ ተግባራት የባህላዊ እምነቱን ቀጣይነት ከማስጠበቅ አንፃሩም የሚታይ ሚና አላቸው። ምክንያቱም ድርጊቶች የህዝቡ ጠባቂ የሆነውን የቃልቻ መንፈስ እንዳይጠፋና ማህበረሰቡ ያለ መሪ፤ ያለሃይማኖት አባት እንዳይቀር የሚያስችሉ በመሆናቸው።

በመኢኒት ብሔረሰብ የተለያዩ እና በቁጥርም ብዙ ሊባሉ የሚችሉ ጎሳዎች አሉ።እነዚህ ጎሳዎች የራሳቸው አባል እንዳላቸው ሁሉ የራሳቸው መሪና አስተዳዳሪ አላቸው። የጎሳ አስተዳደሩ አባላት በጎሳው አባላት ላይ የመምራትና የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ተቋም ነው። በዚህም በጎሳው ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶችን ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመተባበር እርቅ እንዲፈጠር የማድረግ በአጠቃላይም ለጎሳ አባላቱ ሰላም እንዲመጣ የሚወጡት ተግባርም ትልቅ ግምት ይሰጠዋል።

እንደ ተቋም የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ፣ ሥርዓትና ህግ አለው። እነዚህ የመተዳደሪያ ደንቦችና ሥርዓቶች የተቋሙን ደህንነት ማስጠበቅና ቀጣይነቱን የሚረጋገጥ ተግባር አላቸው። ማህበረሰቡን ከተፈጥሮ እና ከአካባቢው ጋር እንዲሁም በእርስ በርስ ግንኙነት በስምምነት እንዲኖርም ያስችሉታል። እነዚህን ሥርዓቶች መጣስ ደግሞ ከላይ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋርፍቺ የሚፈጥርበትና ህልውናውን የሚያቃውስበት ሁኔታ ይፈጥርበታል። የጎሳ መሪዎች እንደማንኛውም ሰው በሞት ከዚህ አለም ቢለዩ ማህበረሰቡ የለቅሶ ሥርዓቱን አፈፃፀምም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እንደ ተቋም የራሱ ደንብና ሥርዓት ያለው በመሆኑ እነዚህን ሥርዓቶችና ደንቦች ተከትሎ ይተገበራል።

በዚህም መሠረት የውርስ ሥርዓቱ ይፈፀማል። የአዲሱን የጎሳ መሪ ትክክለኛ ተመራጭነት ለማረጋገጥ የክብት አንጀት ይነበባል። በትክክል መመረጡ ሲረጋገጥ አስከሬኑ ይቀበራል። በእነዚህ ሥርዓቶች ያላለፈና ያልተመረጠ ሰው ጎሳ የመምራት ሥልጣን አይሰጠውም። ምክንያቱም ይህን ተቋም ለመምራት የማህበረሰቡ አመኔታ አግኝቶ ተቋሙን ለማስጠበቅ አይችልም። በመሆኑም የብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት አከዋወን ሥርዓት ይህን ማህበራዊ ተቋም ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ እና እንዲጠበቅ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና አለው።

የለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ ትዕይንቶች እንዳሉ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን ካሉት ሟቾች በስተቀር በሌሎች ማህበራዊ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሟቾች ዘመዶች ዝምድናቸውን ለመግለፅ ክብት ይቀጠቅጣሉ። ይህን የማያደርግ ግን ከዝምድና ይገለላል። ምክንያቱም ስምምነት አላከበረምና። አቶ ብርሀኑ ቸኮባ የተባሉ መረጃ አቀባይ ክብት መቀጥቀጥ ዝምድናን እንዴት ሊያጠናክር እንደሚችል ለተጠየቁት ጥያቄ

> *አንድ ሰው ሲሞት ክተለያዩ የጎሳ አባላት ለቀስተኛዎች ይመጣሉ። ሴቶቹ ዘፈን ይዘው ይመጣሉ። ወንዶቹ ደግሞ ክብት ይዘው መጥተው ይቀጠቅጣሉ። ከዛም እኛ እኮ ክብት ቀጥቅጠናል ዘመድ ነን በማለት ዝምድናቸውን ይገልፃሉ። ይህ ደግሞ ዘመዶች ነን አንጋባም የሚል ትርጉምም አለው (11/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ) በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።*

በብሔረሰቡ አንድ ሰው ከራሱ ጎሳ ማግባት አይችልም። ይህ በብሔረሰቡ ባህል የተከለከለ ነው። በአንድ ጎሳ ያሉ አባላት እንደ ዘመድ የሚታዩ በመሆናቸው በዚህ የተነሳ የሚች ልጅ ከሌላ ጎሳ ያገባችው ወንድ በአባቷ ወይም በእናቷ ቀብር ላይ ክብት ይቀጠቀጣል። ይህም ተጋብተናል ዘመድ ነን ዝምድናችንንም በዚህ ክብት እገልፃለሁ የሚል ትርጉም አለው።በዚህም የቤተሰብ ትስስሩ እንዲጨምር ያደርጋል።

ዘር እየበዛ እና የዝምድና ትስስሩ እየሰፋ በሄደ ቁጥር እንደበፊቱ በቅርበት የዘመድን ሁኔታ ለመከታተል የሚያደርግበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህን የዝምድና ቁርኝት ለማጥበቅ በልቅሶ ላይ ክብት መቀጥቀጡ ትልቅ አስተዋጽ አለው።ይህን ሀሳብ አስመልክቶ አቶ መልኬ ኬላጊ

> *ሰው ሲኖር ያገባል ይወልዳል ዘሩም እየበዛና ከድሮው እየጨመረ ይሄዳል። ዘሩ እየበዛ ሲሄድ ደግሞ ዝምድናንና እንደድሮው ለመጠበቅ ክብት እያመጡ መቀጥቀጥ አለባቸው። ይህን ካላደረጉ ግን የዝምድና ሀረጉ እየላላ ይመጣል። ምክንያቱም ክብት የሚቀጠቀጠው ለሟች ያለን ተቆርቋሪነትና ዝምድናን ለመግለፅ በመሆኑ ነው። (15/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ቀበሌ)* በማለት ተናግረዋል።

ሌላው ተጠቃሽ ነጥብ ሚች ልጆቹን ሳያሳድግ ከሞተ ሚስቱንና ልጆቹን ወንድሙ ይወርሳል። ይህ በብሔረሰቡ የተለመደና አመኔታን ያገኘ የጋብቻ ሁኔታ ነው። በሥርዓቱም የተወረሰችውን ሴት የሚያገባት ሰው ቂብ ፍየል ወይም በግ በዱላ ቀጥቅጦ በመግደል በደመ በማጠብ እንድትታደስ ያደርጋታል። ቂብ ፍየል ወይም በግ ያልወለዱ ናቸው። በደም መታጠቢ ደግሞ አዲስና ከማንም እንዳልደረሰች ያደርጋታል ተብሎ ስለሚታመን የሚደረግ ነው። የውርስ ጋብቻው የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት የሚች ልጆችን ልክ እንደራሱ አድርጎ በማሳደግ በኩል ከሚች ወንድም የተሻለ የለም ተብሎ ስለሚታመን ነው። ሴቲ ሌላ ወንድ ካገባች ንብረቷንም ልጆቿንም ይዛ ትሄዳለች ስለዚህ ከሚች ልጆች ጋር ያለ ዝምድና እንዳይላላ የውርስ ጋብቻው ይፈፅማል። ይህ ስርዓት ዝምድናን በማጠናከር በኩል ትልቅ ሚና አለው።

በመኢኒት ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲሞት ዘመድ አዝማድ በአንድ ላይ ተሰብስቦ መቅበር አለበት። በዚህ ምክንያት ሚች በተለይም በሽምግልና እድሜ ያለ ከሆነ ሳይቀበር 5-7 ቀናት ሊቆይ ይችላል።

በአጠቃላይ የመኢኒት ብሔረሰብ መገለጫ ከሆኑት ባህሎች ውስጥ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔው በብሄረሰቡ ትልቅ ቦታና ግምት የሚሰጣቸውን ማህበረ ባህላዊ ተቋማትን በማጠናከር እና በማስቀጠል በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን።

4.3.3 የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት ከመግለፅ አንፃር

የመኢኒት ብሔረሰብ በለቅሶ ሥርዓት ክዋኔው ማንነቱን፣ አመለካከቱንና እምነቱን ይገልፃል። ይህንንም በሥርዓቱ ላይ በሚታዩ የተለያዩ ተግባራት ያሳያል። ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ውስጥ ለዚህ ተግባር ማሳያነት የሚከተሉትን አቀርባለሁ። የለቅሶ ሥርዓት ክንውኑ ከተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች አንፃር ተከፋፍሎና የተለያዩ ተግባራት ታክለውበት ይፈፀማል። ይህም ማህበረሰቡ ከማህበረሰቡ ለወጡት ሰዎችና ተቋማት ያለውን አመለካከት የሚያሳይ ነው።

ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን ደርሰው የሚሞቱ ሰዎች በመሪር ሀዘንና በለቅሶ ይቀበራሉ።በዚህ ማህበራዊ ደረጃ ያሉ የማህበረሰቡ ክፍሎች የአለምን ምንነት ሳይገነዘቡ። አባትነትና እናትነትን ሳያዩ ሀብትና ንብረት ሳያፈሩ በማለፋቸው ተጎድተዋል በሚል አመለካከት የሚከወን ሥርዓት ነው።

ከሀገንነት ጅምሮ እስከ አቅመ አዳም/ሂዋን ደርሰው በሚሞቱበት ጊዜ ምርር አድርገን ነው የምናለቅሰው። ምክንያቱም ይህን አለም አይተው ስላልጠገቡ በለቅሶ ብቻ ነው የምናሳልፈው። ከዚህ በኋላ የቀብር ሥርዓቱ እንደ አዛውንት እና እንደ ሽማግሌ አይቆይም ወዲያው ይቀበራሉ። (እጅጉ ጥላሁን 19/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)

በማለት የሰጡት መረጃ ከላይ በተጠቀሰው የፅድሚ ክልል ውስጥ ላሉ ሰዎች ማህበረሰብ ያለውን አመለካከት የሚያሳይ ነው።

በብሔረሰቡ የእድሜ ባለፀጋዎች፣ ኔፊይ እና ኮሙሩት ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ ይሰጣቸዋል። ይህ በብሔረሰቡ ካላቸው የማስታረቅ ታሪክ የማወቅ፣ ሃይማኖታዊ ስራዎችን የመስራት ወዘተ ተግባራት የመጣ ነው። ማህበረሰቡ ለእነዚህ ተቋማት የመገዛት፣ የመታዘዝና በህግጋታቸው የመመራት ስራ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ እንዲሁም ባለመታዘዝ የሚመጣን ቅጣትና ጥፋትን በእምነት ተቀብሎ ይኖራል። እነዚህ ህግጋቶችና ደንቦች ተግባራዊ ከሚሆኑባቸው ማህበራዊ አጋጣሚዎች መካከል የለቅሶ ሥርዓት አንዱና ዋነኛው ነው።

በለቅሶ ላይ አማቾች እና የሟች ልጆች የሚያመጧቸው ከብቶች ይቀጠቀጣሉ። ይህ ለሟች ያለን ዝምድና እና ቀረቤታን እንዲሁም ሟች ትልቅ መሆኑን ይገልፃል ብለን የምናደርገው ነው። የከብቶቹ ቆዳ ከተገፈፈ በኋላ ስጋውን ለምግብነት እናውለዋለን። ከዚያ የከብቶቹ አንጀት ይነበላል። ይህ ደግሞ ቃልቻ ከተቆጣም፣ ያዘነ ሰው ካለም፣ በሟችና በሟች ቤተሰብ ላይ የሚመጣ ክፉ እና ጥሩ ነገር ካለም ያሳየናል ብለን እናምናለን። በሚተነበይበት ወቅት ለቃልቻ መስዋዕት እንዲቀርብና የመጣው ክፉ ነገር እንዲመለስ የምናደርግበት ጊዜም አለ። አንባቢዎቹ ያው በልምድ ነው የሚሰሩት። ከቀደሙት አባቶች በወረሱት መሠረት። (ዝኒ ከማሁ)

በማለት በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ የሚከናወኑ ድርጊቶች መካከል ከብት መቀጥቀጥ በማህበረሰቡ ዝምድናን ቀረቤታን እንዲሁም የሟችን ማህበራዊ ደረጃ ይገልፃል በሚል አመለካከት የሚተገበር መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ በኋላ የሚካሄደው አንጀት የማንበብና መፃኢ ህይወትን የመተንበይ ስራ ነው። "የተቀጠቀጠው ከብት አንጀት የሚችን ቤተሰብ እንዲሁም ከብት የቀጠቀጠውን ሰው መጥፎና ጥሩ አጋጣሚዎች ያሳያል" የሚል እምነት አለ። ከዚህ በኋላ በብሔረሰቡ እምነት በአንጀቱ ላይ የታየው መጥፎ ነገር እውን እንዳይሆን ለቃልቻ መስዋዕት ማቅረብ፣ የተጣላም ካለ መታረቅ እንዳለበት ይመከራል። ይህን ተግባራዊ በማስደረግ በኩል የሀገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች እንዲሁም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የሟች ቤተሰቦች ከልብ በመነጨ እምነት የተወሰነባቸውን ስጦታና መስዋዕት ያቀርባሉ። በዚህ ድርጊታቸው ይከሰትብናል ብለው የፈሩት አደጋ (የሰው መሞት፣ የአዝመራ መጥፋት፣ የከብት አለመርባት፣ ... ወዘተ.) እንደሚቀር ያምናሉ። ይህ ሥርዓት ከማህበረሰቡ ታሪክ

ጋር እጅግ የተቆራኘና በተግባራዊነቱም ከዘመናት በፊት የነበረ አሁንም አመኔታ ተችሮት የሚተገበር ነው።

ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን ለደረሱ ሚቾች ክብት አይቀጠቀጥም ይህም የሚች ማህበራዊ ደረጃ እና በማህበረሰቡ ያላቸው ክብር ዝቅተኛ በመሆኑ ነው። ይህ የማህበረሰቡ አመለካከት ተቀይሮ ተከብረውና ትልቅ ደረጃ ተሰጥቷቸው የዕድሜ ባለፀጋ ሆነው ባለመሞታቸውም ከፍተኛ የሀዘን ለቅሶ ይደረጋል።

በማንኛውም የሥልጣን እርከን የሚገኝ ሚች ቀብር ላይ አስከሬን መጠበቂያ ጎጆ ይሰራል። ይህ ጎጆ "ቃምጡት" ወይም ቡዳ ከሚባልና አስከሬን ከሚበላ አካል ለመጠበቅ የሚያገለግል ነው። በብሄረሰቡ እምነት "ቃምጡት" አስከሬኑን በማባበልና በማሞገስ አውጥቶ ይበላል። ከዚህ አካል አስከሬኑን ለመጠበቅ በቤታቸው አቅራቢያ በመቅበር እና በቀብሩ ላይ ጎጆ ሰርቶ መጠበቅ መፍትሔ እንደሆነ የታመነና ተግባራዊም የሚደረግ ነው። በቀብር ሥርዓቱ ላይ የሚች ልጅ ሚስቶች ሰው ቀና ብለው እንዳያዩ የሚደረገውም እንዳይሞቱ በሚል እምነት ነው።

የመቀበሪያ ጉድጓድ እጅግ ጥልቀት ያለው ሆኖ መቆፈሩም "ቃምጡት" በቀላሉ አስከሬኑን አውጥቶ እንዳይወስደው ለማድረግ ያስችላል ተብሎ ይታመናል። አስከሬን ለመጠበቂያነት የሚሰራው ጎጆ ከሦስት ወር በኋላ በድግስ ታጅቦ ይፈርሳል። በዚህ ሥርዓት ላይ በቀብሩ የተገኙ ሁሉ እንዲመጡ በባህሉ የተደነገገ ነው። ይህን ባያደርጉ "ጠላት ይመጣብናል" የሚል እምነት ስላላቸው በአንድነት እንደቀበሩት ሁሉ በአንድ ላይ ዳሱን አፍርሰው ያቃጥላሉ። ለሚችም ሰላም ስጠን መንፈስህ በክፉ አይከተታተለን በማለት የመጨረሻ ስንብት ያደርጋሉ። ይህ ድርጊት የሚች መንፈስ በቤተሰቦቹ ላይ አንዳችም የመረበሽ እና የመጨነቅ ብሎም የህመምና የአደጋ ስጋት እንዳያደርስ ያደርጋል በሚል እምነት የሚከናወን ነው። በባህሉ ከዚህ ሰዓት በኋላ ሀዘን እንዳለቀ ከዚህ በኋላ ማዘን እንደማይገባ ይታመናል።

ሌላው በሥርዓቱ ላይ የሚከወን ተግባር በደም የመንፃት ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ከሥርዓትነቱ በስተጀርባ የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት የሚያሳይ ነው። በማህበረሰቡ አንድ ባለቃልቻ ወይም የጎሳ መሪ ቢሞት የውርስ ሥርዓቱ እስካልተፈፀመ ድረስ የቀብር፣ የለቅሶ ወይም የጭፈራ ሥርዓቶች አይጀምሩም።እነዚህ አካላት የማህበረሰቡ የበላይ ጠባቂ ከመሆን የዘለለ ኃላፊነት ያላቸው ናቸው። ይህን ኃላፊነት የሚሸከም ሌላ አካል እስካልተገኘ

ድረስ ማህበረሰቡ ያለጠባቂ ይቀራል በሚል እምነት ቀደም ብለው የተረዘረዘሩት ስርዓቶች አይከናወኑም።

የተለያዩ የፀሎት፣ና የልመና ሥርዓቶች ተፈፅመው የቃልቻውም ይሁን የጎሳ መሪው ወራሾች ከታወቁ በኋላ በደም በመታጠብ የመንፃት ሥርዓት እንዲፈፀሙ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ በተከታዮቻቸው አመኔታን እና ይሁንታን አግኝተው ስራቸውን በይፋ ይጀምራሉ። ይህን በደም የመታጠብ ሥርዓት አስመለክተው አቶ ደምሴ ዘውዴ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> *ውሃ በተለያዩ ነገሮች ሊቆሽሽና ሊበከል ይችላል። ስለዚህ በተለያዩ መጥፎና ጥሩ ተግባራት ላይ ተሰማርቶ የቆየው ሰው አሁን ወራሽነቱ ተረጋግጦ በከብት ደም መታጠብና መንፃት አለበት። ከብት በጀሮ የሚገባ ክፉ ነገር አሊያም በክፉ የሚወጣ ኃጢያት የለበትም። ለዚህ ነው በከብት ደም ታጥበው የሚነፁት። (19/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)*

በማለት በከብት ደም የመንፃት ሥርዓቱ የሚፈፀምበትን ምክንያት አስረድተዋል። አዲሱ ባለቃልቻ ወይም የጎሳ መሪ በዚህ ሥርዓት እስካለለፈ ድረስ ስራ መጀመርና ህዝቡን ማስተዳደር አይችሉም። መንፈሱ ይሸረጥበታል (ይሰወርበታል)። ለጎሳ መሪውም ፀሎትና ልመናው አይሰማለትም ተብሎ ይታመናል። ከሁሉም የሚበልጠውና የሚልቀው አሳሳቢ ጉዳይ ግን የማህበረሰቡ ካለጠባቂና ካለመሪ መቅረት፣ በዚህም ለተለያዩ "ችግሮች የሚጋለጥ" በመሆኑ ነው። ከዚህም የተነሳ ሥርዓቱ እንዲፈፀም የግድ ይሆናል። አዲሱ ባለቃልቻ የእከሌን ቃልቻ ወርሷል ይባላል። የጎሳ መሪው ደግሞ ቀድሞ ጎሳውን ይመራው በነበረው ሰው ስም እንዲጠራ ይደረጋል። ይህ ደግሞ የማህበረሰቡን እምነት እንደቀድሞው ሁሉ ለመሳብ ያስችላል።

በመኢኒት ብሔረሰብ አንድ በእድሜ የገፋ የማህበረሰቡ አባል በሞት ቢለይ አስከሬኑ በህይወት ዘመኑ ከኖበት ቤት አይወጣም። ይህ ከሆነ አንድም የሟች ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን አያሳይም ሁለትም "የሟች መንሰፍ በቤት ውስጥ በመቅረት ቤተሰቦቹን ይረብሻል"። በመሆኑም በህመመ መዕናት እንደማይድን የታመነበት ሲሆን አዲስ ቤት እንዲሰራ ተደርጎ እዛ እንዲገባ ይደረጋል። ሲሞት አስፈላጊው የጭፈራና የዘፈን ዝግጅትና ድግስ ከተካሄደ በኋላ አስከሬኑ በአዲስ በር ነው የሚወጣው። ይህ ደግሞ ሟች ወደ አዲስ አለም እየሄደ ነው የሚለውን የማህበረሰቡን አመለካከት የሚያሳይ ነው። በእድሜ ትንሽ ለሆኑ ሟቾችም ይኸው ትርጉም ተመሳሳይ ነው።

ሌላው የብሔረሰቡን እምነት የሚያሳየን ሥርዓት የግንዘት ሥርዓቱ ነው። በዚህ ወቅት በተለይም ሟች ወንድ ከሆነ እና በእድሜም ትልቅ ከሆነ ብልቱ "ኮርባ" በተሰኘ ማሰሪያ ይታሰራል። ይህ የሚደረገው በማህበረሰቡ እምነት የሟች የዘርፍሬ ከፊሰሰ ዘመዶቹ ሁሉ ይሞታሉ የሚል እምነት በመኖሩ ነው። ስለዚህ ይህ አደጋ እንዳይከሰት ማህበረሰቡ በወል በግንዘት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰውን ሥርዓት ይፈፅማል።

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት አከዋወን ላይ የሚታዩ የተለያዩ ሥርዓቶች ከሥርዓትነታቸው በስተጀርባ የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት የሚያሳዩና የሚገልፁ ናቸው።

4.4 ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓቱን ለትውልድ ለማስተላለፍ ያስቻሉ መንገዶችና የማህበረሰቡ ትጋት

ባህል የተለያዩ መተላለፊያ መንገዶች አሉት። ከነዚህ ውስጥ ድርጊት ወይም ክዋኔ አንዱ ባህል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ነው። በዚህም የማህበረሰቡ እውቀትንና ልምዶችን ሲከወኑ የተቀሩት ትምህርት ይወስዳሉ። እነሱም ያዩትን እና የሰሙትን በጨዋታና በቀልድ መልክ በማዳበር እውነተኛ ቦታው ላይ የመከወን እድሉን ያገኛሉ። በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓትን ለትውልድ እንዲተላለፍ ከሚያስችሉ መንገዶች ውስጥ ተሳታፊዎች ላይ (በእድሜ፣ በፆታን በመሰል ማህበራዊ ደረጃዎች) የሚጣል ገደብ አለመኖሩ አንዱና ዋነኛው ነው።

ማንኛውም የመኢኒት ብሔረሰብ አባል የሆነ እና በሥርዓቱ ላይ መሳተፍ የፈለገ ሁሉ ክልከላና ገደብ አይደረግበትም። ይህ ደግሞ እንደ ወ/ሮ ጀጋች ቻልኩ አገላለፅ

> *በእኛ ባህል ህፃናት በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ እንዳይሳተፉ አንከለክልም። ማንኛውም የፈለገ ሰው መሳተፍ ይችላል። እነሱን መከልከል ደግሞ ባህላችንን ሜዳ ላይ ዝም ብሎ እንዲወድቅ ማድረግ ነው። አንጀት ሲነበብ ብዙ ህፃናትና ወጣቶች አንጀት አንባቢውን ይመለከቱታል። ይህ እኮ እንዴት እንደሚያነበውና እንዴት እንደሚተነብየው ለመማር ነው። በሌላ በኩልም አንዲሁ ነው። ቀብር ጉድጓድ ከቻሉ ይቆፍራሉ። የቀብር ድንጋይ ያመጣሉ። አዲስ ቤት ሲሰራም በጉልበት እየረዱ ይማራሉ። (13/08/2003 ቢያዜሊች ቀበሌ)*

ህፃናቱ በክዋኔው ላይ ከመሳተፍ አልፈው ምን ለምን አላማ እንደሚደረግ የመማር እድል እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ከላይ የተጠቀሱት መረጃ አቀባይ እንደገለፁት የብሔረሰቡን ባህል

በቀጣይነት ለትውልድ ለማሸጋገር ህፃናትንና ወጣቶችን በክዋኔው እንዳይሳተፍ ክልከላ አለማድረግ አንዱና ዋነኛው ነጥብ መሆኑን ገለጸዎል ::የመኢኒት ብሔረሰብ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔውን አምኖበት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። ሥርዓቱን ባህሉ በሚፈቅደው የማይተገብር ወይም ለተግባራዊነቱ የማይተጋ ቢሆን ባህሉን በመናቁ ይገለላል። በዚህ ተግባሩ ከተለያዩ ማህበረባህላዊ ተሳትፎዎች እንዲታገድ ይደረጋል። በመሆኑም የብሔረሰቡ አባል ከሥርዓተ ማህበሩ ህግና ደንብ ባለማፈንገጥ ለሥርዓቱ ቀጣይነት ያራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል። በዚህ ሀሳብ ላይ አቶ ሲምንቶ ሸማቻ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል፡-

> *እንዴት ክባህሉ ሊወጣ ይችላል። እኛ ከአባትና ከአያቶቻችን ተቀብለን የያዝነውን ባህል መናቅና ማጣጣል አይችልም። ይህን ካደረገ ክባህሉ በማፈንገጡ እንደሰው አይታይም። ክብርም አንሰጠውም። ባህላችንን ያበላሸ ስለሚባል ከተለያዩ ማህበራዊ ስራዎች እገዳ ስለምናደርግበት አያፈነግጥም። (14/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)*

አያይዘውም በተለያዩ ምክንያቶች በማህበረሰቡ ስምምነት ቱባው ባህል ሊሻሻል የሚችልበትን አጋጣሚም እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> *አሁን ድሮ ድሮ የአገናነዝ ሥርዓታችን ሰውየውን ቁጢጥ አድርገን አስቀምጠን እጅና እግሩን በገመድ በጣም ጥብቅ አድርገን እናስራን። ክዚያ በትክስ የክብት ቆዳ ጠቅልለን እንገንዝና እንደመቀጫ አይነት ጉድጓድ ቆፍረን ነበር የምንቀብረው። አሁን ግን በተለይ በኢህዴግ መንግስት ይህ ሥርዓት እንዲያው በጣም አሰቃቂ መሆኑን በመስማማታችን ትተነዋል። ክዛ ይልቅ ቀጥ አድርገን አስተኝተን በልብስና በቆዳ እንገንዘዋለን። ሌላው በስምምነት እያስቀረነው የመጣነው ነገር አለ። ይህ አንድ ትልቅ ሰው ሲሞት ድሮ እህልና ክብት በብዛት እስኪገኝ ድረስ እስክ ሦስት አመት ሳንቀብር እናቆይለን። አሁን ግን አስክሬኑን እንቀብርና አስፈላጊው እህልና የክብት ሲገኝ ዘመድ ሁሉ ተሰብስቦ ጭረፋው እንዲቀጥል ይደረጋል። (ገዢ ክማሁ)*

ማህበረሰቡ ተስማምቶ ላፀደቀው ህግና ደንብ ተሰማምቶ መገዛት አለበት። ነገር ግን ይህን ህጉንና ደንቡን በመሠረተ ሀሳቡ ተስማምቶ ሊሻሻልበት የሚችልበት አጋጣሚም አለ። ይህ እርምጃ መውሰድ ባህሉን ሙሉ ለሙሉ ተቃውሞ እንዳይገጥመው ከሚረዱ መንገዶች መካከል አንዱ ነው።

በመኢኒት ባህል አንድ ህፃን ተወልዶ እራሱን እስኪችል (ትዳር እስኪይዝ) ከቤተሰቡ ጋር አብሮ ይኖራል። በዚህ ወቅት እናት አባቱ በየጊዜውና በየአጋጣሚው ሁሉ እኔን የምትቀብሩኝ በሬ ቀጥቅጠህ፣ አዲስ ቤት ሰርተህ፣በደንብ ደግሰህና አስጨፍረህ ነው። በማለት ትምህርት እና ምክር ይሰጡታል። ልጁም በለቅሶ ቤት እየሄደ የሚያየውን ሥርዓት እናትና አባቱ ከሚነግሩት ጋር እያስማማና እያጣጣመ እውቀቱን ያዳብራል። በመጨረሻም

ከማህበረሰቡ ባገኘው ባህላዊ እውቀት የእናት የአባቱን የለቅሶ ሥርዓት ይፈፅማል። እሱም ለሚወልዳቸው ልጆች ይህንኑ ባህላዊ እውቀት ያስጨብጣቸዋል።

ወ/ሮ አረጋሽ ቦኤች

> *በእኛ ባህል ልጆቻችንን እንዲህ አድርጋችሁ ቅበሩን እያልን እናስተምራለን። እኛም ከናትና ከአባታችን ያገኘነው በዚህ መልክ ስለሆነ እነሱም ይህንን ባህል እንዲጠብቁ እናስተምራለን። ለምንድን ነው ብለው ቢጠይቁንም እኛ የወለድን ስለሆነ አማች ያየን ስለሆነ እንዲህ እንቀበራለን። ልጆች ሲሞቱ ደግሞ እያለቀስን እንቀብራለን በማለት የሁሉንም አይነት ሥርዓት እናስተምራቸዋለን። (14/08/2003 ዓ.ም ጎማ ቀበሌ)*

በማለት እንደገለፁት ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት አፈፃፀም ለተከታይ ትውልድ በመንገር ብሎም ባህሉን እንዲጠብቁት በማስቻል በኩል የማህበረሰቡ ጥረት ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።

5. ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች

5.1 ማጠቃለያ

የመኢኒት ብሄረሰብ በቤንች፣በጉራፈረዳና በሌሎች የቤንች ማጂ ዞን አካባቢዎች የሚገኝ ቢሆንም ለጥናቱ የተመረጠት ቦታዎች በሄረሰቡ በስፋት የሰፈረባቸው ሁለት ወረደዎች ናቸው። ጥናቱ የለቅሶ ስርዓቱ እነዴት እንደሚከወን ማሳየተ ላይ ትኩረት ተደርጎ በክዎኔው ላይ ወሳኝ የሆኑ የብሄረሰቡ የልቅሶ ስርአት መለያዎች የሆኑትን የመከወኛ ቁሶች ፣መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን ክንውኖች ከተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች አንጻር በመግለጽና በመተንተን የቀረበበት ነው።

የስርዓቱን ክዋኔ ለማሳየት ሂደቱ ቅድመሞት ፣ጊዜ ሞትና ድህረ ቀብር በሚል ቀርቧል። ቅድመ ሞት ተብሎ የተገለጸው ሂደት አንድ ሰው በጠና ታሞ እንደማይድን ከተገመተበት ጊዜ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ የሚደረጉ ክንውኖችን የሚመለከት ነው። ጊዜ ሞት ተብሎ የተገለጸው ሂደት ደግሞ የግለሰቡ ነፍስ ከስጋው ከተለየችበት ጊዜ ግበአተ መሬቱ እስኪፈጸም ድረስ የሚደረጉ ክንውኖችን የሚመለከት ነው።ድህረ ቀብር ክንውኖች ደግሞ ከቀብር በሁዋላ የሚከወኑ ስረአቶችን የሚገለጽ ነው።በነዚህ ሂደቶች በጥቅሉ በብሄረሰቡ አንድ ሰው ሲሞት የልቅሶ ስረአት ክዎኔው በሞተው ሰው እድሜና ባህላዊ ስልጣን እንዲሁም በሞተበት ምክንያት የሚወሰን መሆኑ በጥናቱ ታውቋል።

ጥናቱ በመስክ በተገኙ መረጃዎች ተመስረቶ የለቅሶ ስራአቱን መተንተን ላይ የተካሄደ ነው። በተገኙ መረጃዎች መሰረትም በብሄረሰቡ የለቅሶ ስረአት አፈጻጸም ወቅት በተለይ ከአስከሬን ግንዘት፣ ለሚች ከሚደረግ የልቅሶ ወይንም የዘፈን ስረአት ፣ ያስከሬን አቀባበር አቅጣጫ መረጣ ወዘተ. እምነታዊ መሰረት ያላቸው ልማዳዊ ተግባራት መሆናቸው ታውቋል።

የመኢኒት ብሄረሰብ የኦሞን ወንዝ ተሻግሮ አሁን ወደ ሰፈረበት የቤንች ማጂ ዞን ሲመጣ ቀድሞ ነበረው መህበረሰብ አሉታዊ አመለካከት ዛሬ ለሚከውነው የለቅሶ ስረአት መሰረት ሆኖታል።

የብሄረሰቡ የለቅሶ ሥረአት ክዋኔ የተለያዩ መህበራዊ ደረጃዎችን መሰረት አደረጎ ይከወናል።ለዚህም እደሜና ባህላዊ ስለጣን ትልቅ ድርሻ አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ

ሰው የሞተበት ሁኔታም የለቅሶስረአቱን የሚወስን መሆኑ ሌላው በጥናቱ የተገኘ ነጥብ ነው።

ብሄረሰቡ በልቅሶ ሰረአቱ አማካኝነት የተለያዩ ባህላዊና መህበራዊ እሴቶችን በድረጊት ከትውልድ ትውለድ ያስተላልፋል ።በዚህም ታሪኩን እምነቱን እና ስረአቶቹን በመከወን ለትውልድ ያሻግራል ።የቀደመውን ትውለድ አሻራም በዛሬው ትውልድ ህያውነት ያሰርጻል።የማንነቱ መለያ ይሆነው ዘንድ በአውዱ የሚፈቀዱ ተግባራትን ይከውናል።

5.2 ይሁንታ

በዚህ ነኡስ ርእስ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት መረጃ ለመሰብሰብ መስክ በወጣሁበት ጊዜ ጉዳዩ ከሚመለለከታቸው አንዳንድ መስሪያቤቶች ላይ የታዘብኳቸውን ችግሮች ፣መስሪያቤቶቹም ሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ቢያደርጓቸው ይበጃሉ የምላቸው ሀሳቦች ስንዝሪያለሁ።-

1. በዚህ ጥናት መረጃ የመሰብሰብ ተግባር በማከናውነበት ወቅት ስለመኢኒት በሄረሰብ ደራ ለመሰጠት የሚያስችሉ መረጀዎችን ለመግኘት ወደ ወረደዎቹ በህልና ማስታወቂያ ቢሮዎች ሄጀ ነበር። ይሁን እንጂ ከቢሮዎቹ የተገኙ መረጃዎች በጣም ጥቂተና በየወረዳዎቹ የሚገኙ መስሪያቤቶች ያጠናቀሯቸው የስራ ሪፖረቶች ናቸው።እነዚህን ሰራዎች እንደመረጃ ለመጠቀም ያልታተመ ከመሆናቸው በተጨማሪ መቼና የት እንደተሰበሰቡ የሚገልጽ መረጃ ሰላልተቀመጠባቸው አስተማማኝነታቸው ላይ ጥየቄ የሚያስነሱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ አጠቃለይ ስለህዝቡ ብዛትና ስለወረዳዎቹ የቆዳ ስፋት የተገኙ መረጃወች እርስ በእርስ የሚጣረሱ ሆንው ተገኝተዎል። ይህ ደግሞ የመረጃ ክፈተት የሚፈጥር በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ሊያስቡበት ይገባል፣

2. በሁለቱም ወረደዎች የባህልና ማስታወቂያ ቢሮዎች ስራቸው ብሄረሰቡ ያለውን በህላዊ እውቀትና ጥበብ ማስተዋወቅ ነው። ይህንንም ባህል ነክ ጉዳዮችን በመሰብሰብ በማጥናትና በመሰነድ ማሳየት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። ነገር ግን በቢሮቹ ቀሳዊ በህሎች ብቻ (የተሟላ መገለጫ ሳይደረግላቸው) ለእይታ ቀርበው ተመልክቻለሁ። የብሄረሰቡን ባህል ለማስተዎወቅ እነደ ቁሳዊ ባህል ሁሉ

ስነቃሉች፣የተለያዩ ክፖኔችን የሚያሳዩ የምስል መረጀዎች በባለሙያዎች እየተሰበሰቡና እየተጠኑ የሚሰነዱበት ሁኔታ ቢመቻች፣

3. በብሄረሰቡ ስልጣን ባለቤቶችና በእድሜ ባለጸጋዎች የቀብር ስረአት ላይ ከብት የመቀጥቀጥ ስረአት የካሄዳል። የሚቀጠቀጡ ከብቶች ቁጥር የሚወሰነው እንደሟች ዘመድ ብዛት ፣በወንድ ለጆቹ ቁጥርና ሀብት ፣በአማቾች ብዛት ፣እነዲሁም አሳትና የአጎት ልጆች ቁጥር ነው። በዚህ ስረአት በረካታ ቁጥር ያላቸው ከብቶች የሚቀጠቀጡ በመሆናቸው በማህበረሰቡ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና አለው።ለዘህም የሚመለከተው አካል ማህበረሰቡን አወያይቶ የመፍትሄ ርምጃ ቢወስድ፣

4. አንድ የብሄረሰቡ አባል የሆነና ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ሲሞት አለም አይቶ ነውና የሞተው አይለቀስም ይጨፈራል። በዚህ ጊዜ ቡራለዳይ እየተባለ ብዙ ጥይት የተኮሳል ። በዚህ ጊዜ ወኔ የሚቀሰቅሱ ዘፈኖች ይከወናሉ ።በዚህ ስሜት ውስጥ ጥይቱ አደጋ ሊያደረስ የሚችልበትን አጋጣሚና በኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ጫና በማስተማር ለውጥ እነዲመጣ ቢደረግ ።

ዋቢዎች

ሐረገወይን ድፋባቸው:: "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ 1974 ዓ.ም::

ሞገስ ሚካኤል:: "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርዓት፣ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ሩክራና ክዋኄው":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2002 ዓ.ም::

ባልከው ቸርነት:: "የመንዝ ለቅሶ ግጥሞች ጥናት":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1974 ዓ.ም::

በርሃኑ መኮንን:: "የአማርኛ የሙሾ ግጥሞች":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1973 ዓ.ም::

ተሾመ ሙሉጌታ:: "በቤንሻንጉል ጉምዝ በደባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነስርዓት":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1998 ዓ.ም::

ታደሰ መንግስቱ:: "የጎጃም ለቅሶ ግጥሞች":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህረት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1963 ዓ.ም::

ነጉሴ አክሊሉ:: "ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞች (ምንጃርና ሸንኮራ) አካባቢ":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1974 ዓ.ም

አስመላሽ ወልደማርያምና ጽጌረዳ ትክሌ። "በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልዕክቶች"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም አመታዊ ሴሚና የቀረበ፣ 1980 ዓ.ም።

አስቴር አንጀሎ። "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1997 ዓ.ም።

አየለ መሎሬ። "የሀድያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1986 ዓ.ም።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም።

ካሳው ደሳለው። "የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1997 ዓ.ም።

ወርቁ ማንደፍሮ። "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነስርዓትና የሙሾ ግጥሞች"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1987 ዓ.ም።

ወርቃየሁ አረጋ። "የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት) እና የአወኒ ዚንዚምኒ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1995 ዓ.ም።

ወርቅነሽ ደምለው። "ጅግና ወንዶችና ሴቶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች (በአቸፈር ወረዳ ዙሪያ)"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1992 ዓ.ም።

ዘላለም ኢዮብ። "በጎፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዮሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነግጥማዊ ገፅታ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ምትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1995 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው። <u>የስነፅሁፍ መሰረታውያን</u>። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም።

የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት። "የክልሉ ዋንኛ እምቅ ሀብቶች እና የልማት ማነቆዎች"። ክፍል አንድ የመጀመሪያ ረቂቅ፣ ሀዋሳ፣ 1999 ዓ.ም። (ያልታተመ)

የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋና ታሪክ ቅርስ ጥናት ተቋም። <u>የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል</u>። ሀዋሳ፣ ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

ደስታ ተክለወልድ። <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት</u>። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም።

ዳንኤል አለባቸው። "የጋብቻ ትውፊት በመኢኒት ብሔረሰብ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትርና ስነጥበብ ትምህርት ክፍል፣ በአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ድጋፌ ፈይሳ። "የሲዳማ ብሔረሰብ የለቅሶ ስነስርዓት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1986 ዓ.ም።

ጌጡ ታደሰ። "ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ስርዓት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት፣ ለአርትፈቃደስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1986 ዓ.ም።

ጥላሁን ኢቢዶ። "የጌዲኦ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1982 ዓ.ም።

ፍቃደ አዘዘ። <u>የስነቃል መምሪያ</u>። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም።

_____:: "የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አፋዊ ኪነተቃል ጥናት":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሴሚና የቀረበ፣ 1970 ዓ.ም (ያልታተመ)::

_____:: የመስክ ስራ ስነቃል አሰባሰብ፣ አከለሳሰፍ፣ አተናተንና አሰናነድ፣ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴ፣ ለ"ባህልና የባህል አመራር ለልማት፣ ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ":: የቀረበ ፅሑፍ ሚያዝያ 3-5፣ 1999 ዓ.ም (ያልታተመ)::

Awoke amzaye. Mosaic Cultures and Peoples of South Nations Nationalities and Peoples, Reginal State. Awassa: African printing PLC, 2007.

Bauman, Richard. Verbal Art as Performance. Woveland: Woveland University Press, 1977.

Ben-Amos, Dan. Folkore in Context: Essays. Newdelihi: South Asian Publishers Pvt. Ltd, 1982.

Fassika Bellete. "The Death Customs Among the Ameharas of Śäwa". Ethnological Society Bulletin. Vol. I, No. ii. Ed. Alula Pankhurst, 1953.

Finngan, Ruth. Oral Poetry: It's Nautre, Significance and Social Context. Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

_____. Oral Literature in Africa. Oxford; Clarndon Press 1970.

Glassie, Henry. Material Culture. Chicago and London: the University of Chicago Press, 1999.

Goldstein, Kenneth. Aguide for field workers in folklore. Pennsylvania: Gola Reserech Companey, 1974.

Hoebel, Adamson E. Anthropology the Study of Man. University of Minnesota: mcaraw-Hill Book company, 1966.

CoRinne, Brown. Understanding other Cultures. United States of America: Library of Congress press, 1963.

Jon, Abbink. Artifacts as "Dali art" in Mne'en culture, In Ethiopia: Traditions of creativity. edited by Raymond A, Silver man. Seattle: university of Washington, 1999.

_____. "The deconstruction of 'tribe' ethnicity and politics in south western Ethiopia". Journal of Ethiopian studies. vol. 3, Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 1991, 4-11.

_____. "The Final Rite: Burial Among the Mean of South West Ethiopia". Proceedings of the first national conference of Ethiopian Studies. Addis Ababa University: Institute of Ethiopian Studies., 1990.

_____. "The me'en as Historical Transformation of the Surma". Preliminary not on society and culture African studies. vol. 3, 1988, 7-21.

_____. "Tribal formation on the Ethiopian fringe: toward a history of the Tishana: North east". African studies. Vol. 3, 1989, 120-138.

Kottack, Phillip. Anthropology The Explanation and Human Diversity. McGraw-Hill: Companies Inc, 2002.

Mac, Donald A. Filed work; Collecting Oral Literature. In Richard Dorson (Ed.) London: The University of Chicago Press, 1972.

Martha, C. Sims and Stephens Martine. Living folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Ohio: Ohio State University Press, 2005.

Miklown, Jones. Folkloristic: An Introduction. Bloomington and Indian Polis: Indianan University Press, 1995.

Nega Tessema. "The Death Customs in the Province of Tigre". Ethnological Society Bulletin. Vol. i, No. 2. Ed. Alula Pankhurst. Addis Ababa University, 1953.

Ralph, Linton. The Study of Man an Introduction. The United States of America: Division of Meredith Publishing Company, 1964

Richard M., Dorson. Ed. Folklore, and Folk life Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Vansina, Jan. Oral Tradition As History. USA: The University of Wisconsin Press, 1985.

Wiessnor, Polly and Wulf, Schiefeohovel. Food and the Status an Interdisciplinary Perspective. USA: Library of Congress Press, 1966.


Will, Hans-Georg. "Sketch of Me'en-Grammar". In M. Bender (Ed.). African studies. Analysis and Documentation Vol. 3, 1999, 129-150.

አባሪዎች

አባሪዎች

አባሪ 1

ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ካርታዊ መግለጫ



ጥናቱ የተካሄደባቸው ወረዳዎች

አባሪ 2፡ የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል						
ተ.ቁ	የአቀባይ ሥም	እድሜ	ፆታ	ሙያ	መረጃ የተሰጠበት መቼት	ቀበሌ
1	ሴላ ባላካሮ	60	ወ	ያገር ሽማግሌ	13/08/2003 ዓ.ም ለቅሶ ላይ	ቢያጌሊች
2	ኤርሚያስ አኛኝ	34	ወ	አርሶ አደር	13/08/2003 ዓ.ም በሚች አባታቸው ቀብር ላይ	ቢያጌሊች
3	ሞይና አኛኝ	35	ሴ	የቤት እመቤት	13/08/2003 ዓ.ም በሚች አባታቸውቀብር ላይ	ቢያጌሊች
4	ኢፋይ ቦሙ	43	ወ	አርሶ አደር	13/08/2003 ዓ.ም በአጎቱ ቀብር ላይ	ቢያጌሊች
5	አረጋሽ ቦኤች	40	ሴ	የቀበሌ ም/አስተዳደር	14/08/2003 ዓ.ም በቡና ስርዓት ላይ	ጎማ
6	ዋየች ጀሻ	67	ወ	ኮሙሩት	14/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ	ዱማ
7	ጋቸሁ ሞላባ	40	ሴ	የቤት እመቤት	14/08/2003 ዓ.ም መንገድ ላይ	ጎማ
8	ብርሃኑ ወርቁ	58	ወ	የወረዳ ጤና ጥበቃ ኃላፊ	17/08/2003 ዓ.ም በቹማ ከተማ	ዱማዳሽ
9	ወልደየስ ዶሌ	60	ወ	የወረዳ ም/አስተዳደር	18/08/2003 ዓ.ም በቹማ አስተዳደር ፅ/ቤት	ሽርሽር
10	ሲሚንቶ ሽማቻ	70	ወ	ያገር ሽማግሌ	14/08/2003 ዓ.ም በቡና ስርዓት ላይ	ጎማ
11	ጥላሁን አጅሩ	37	ወ	አርሶ አደር	13/08/2003 ዓ.ም በአጎቱ ለቅሶ	ዱማዳሽ
12	ለግሊ ቶግሊ	48	ሴ	የቤት እመቤት	13/08/2003 ዓ.ም በሚች አቶ አኛኝ ክሪንታው ቀብር ላይ ዘፈን ቢያቀርቡ	ቢያጌሊች
13	ታቶ ማርደሮ	78	ወ	ያገር ሽማግሌ	13/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ቀበሌ	ጎማ
14	ጳውሎስ ክፍሌ	49	ወ	የጎልደያ ወ/አስተዳደር	17/08/2003 ዓ.ም ባቹማ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ	አደይ አበባ
15	በድሉ ካሳ	40	ወ	የጎልደያ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ	17/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት	ባቹማ
16	ተፈራ ኮርዲ	35	ወ	ሚሊሻ	17/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ አስተዳደር	ሻርያ
17	መልኬ ኬላጊ	34	ወ	የጎልደያ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ም/ኃላፊ	ሸሻ አስተዳደር ፅ/ቤት ቅጥር ግቢ 20/08/2003ዓ.ም መኢኒት	ጎማ
18	ሞላጊ ማናቻ	68	ወ	ያገር ሽማግሌ	ሻሻ አስተዳደር ፅ/ቤት ቅጥር ግቢ 20/08/2003ዓ.ም መኢኒት	ሽርሽር
19	ካሳ ከበደ	59	ወ	ያገር ሽማግሌ	ሻሻ አስተዳደር ፅ/ቤት ቅጥር ግቢ 20/08/2003ዓ.ም መኢኒት	ጀሞ
20	ደምሴ ዘውዴ	80	ወ	አርሶ አደር	19/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ	ጎማ
21	እጅጉ ጥላሁን	56	ወ	ነጋደ	19/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ በንግድ ስራ ላይ እያሉ	ጎማ
22	ወይዳይ ጆጋች	60	ወ	ያገር ሽማግሌ	18/08/2003 ዓ.ም ሻሻ ወረዳ አስተዳደር	ኩዱም
23	ጆሮ ዘሪሁን	70	ወ	ኮሙሩት	13/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ	ጨበራ
24	መሪጊት ታምራት	67	ወ	ኮሙሩት	21/08/2003 ዓ.ም ገበያ ሰፈራ	ችሩ አሩት
25	ጓንጓ ቢደንጓ	68	ወ	ያገር ሽማግሌ	21/08/2003 ዓ.ም ገበያ ሰፈራ	ሻሻ
26	አወቀ ፎርሸዋ	60	ወ	ኤሬይ	19/08/2003 ዓ.ም ጨበራ ከተማ	ዱማ
27	አበበ ለገሰ	40	ወ	የብሔረሰቡ ኪነት ቡድን ኃላፊ	20/08/2003 ዓ.ም ጀሞ ከተማ	ሽርሽር

አባሪ 3፡ በክዋኔው ላይ የሚታዩ ግጥሞች

ወንዶች ለእድሜ ባለፀጋዎች የሚያቀርቡት ሙገሳ "ካክሰዳይ"

መኢኒትኛ	አማርኛ
ባርቱ ከረን ከዳሚ	አባቱ አፈር ይቅለልህ
ባድያኛ ዘልፊይ ከበድ	እኔ አለሁ ልጅህ
ባድያኛ ጠረበጅ ቱማ	በጠጠርማው በሬ ቀብርህ
ከእኻየኝ ስጠራጌ	ይኸው ፈጽሜዋለሁ
ባድያንኛ ከነጀርጌ	ሚች የኔ አባት ገዳይ ነው
ባዲያንቼ ችምወርኬ	አርሶ አደር ገበሬ ነበር
ቀበል	ረሃብ የማያስደርስ

በወንዶችም በሴቶችም ለአዛውንቶች የሚቀርብ ሙገሳ "ኮክሰዳይ"

መኢኒትኛ	አማርኛ
በይዴ ከርግ ጠይድያቼ	እናታችን አፈር ይቅለልሽ
ጠያ ፈሌና ቾም ኬትዬኛ	በግራና በቀኝ አንቺን የሚያሞግሱ
አክሞኝኝ ከዬ ዴድያኛ	ሰዎች መጥተዋል ከበራፍሽ

ሴቶች ለሴት ሚቾች የሚያቀርቡት የመገስ እና የሀዘን ዘርን ግጥም "ኮክሰዳይ"

መኢኒትኛ	አማርኛ
ሸማይ ዴ ጋይ	እናቱ ያለኝን አሚጥጩ
ክቼማጌኝ ሴኛ ስዩ	ለቀብርሽ አውየዋለሁኝና
ኦ ከጋጅ ክቾማጌኛ	ከዚህ በኋላ ሰርቼ እንድኖር
ግላሎች ናይ ሃይድያቼ	እድሉን ስጪኝ

ወንዶች ለእድሜ ባለፀጋዎች የሚያቀርቡት ፉከራ “ሞራሊዳይ”

አኛዳለከ በግቼ ኒሮ	እኔ ገዳይ ፒሮ ከሌመ
ብሉሚ ኮኖመንዳ	ተራራ ላይ ወጥቼ
ማጭ ኩቱነ ተሪዮ	ጎሽን ወግቶ
ካንጋዳ	ገዳይ
በርቴ ትሪጁ ባሲዴ	የአባቴ ጦር ቀደም ሲል
ወዴ ከአይ ሻንተናበይ	የወረስኩት በጀግንነት
አዋን አጉት ኮንባሼ	አንበሳና ነብር
ማጌ በረት ካሳ ኔን	የገደልኩበት ይታወቅልኝ

አባሪ 4፡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. አካባቢያዊና ባህላዊ መረጃን ለማግኘት የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. መኢኒት ማለት ምንድን ነው? አካባቢውስ ለምን በዚህ ሊጠራ ቻለ?
1. የመኢኒት ብሔረሰብ ስለአመጣጡ ምን ምን ታሪኮች አሉት?
2. በብሔረሰቡ ትልቅ ቦታና ሽፋን የሚሰጣቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?
3. በለቅሶ ስርዓት አከዋወን ላይ ምን ምን ትዕይንቶች ይቀርባሉ? ተምሳሌትነታቸውስ ምንድን ነው?
4. በብሔረሰቡ ስንት ጎዳዎች አሉ በጎሳዎች መካከልስ መበላለጥ አለ?
5. የብሔረሰቡ እምነት ምንድን ነው?
6. የብሔረሰቡ በዋናነት የገቢ ምንጭ ምንድን ነው?
7. የመኢኔት ህዝብን ልዩ የሚያደርጉት የታሪክና የባህል ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?
8. ሞት ለመኢኒቶች ምንድን ነው?
9. የመኢኒት ብሔረሰብ አንድ የብሔረሰቡ አባል በሞት ሲለይ ምን ምን ድርጊቶች ያከናውናል?
10. የለቅሶ ስርዓቱ የት እና በምን ሁኔታ ይካሄዳል?
11. ይህ ማህበራዊ አጋጣሚ በህዝቡ ዘንድ የሚሰጠው ቦታ ምን ይመስላል?
12. ሰው ሲሞት የሚከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶች ይኖራሉ?
13. በብሔረሰቡ ሴት ወንድ እንዲሁም ህፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን ሲሞቱ የሚካሄዱ ድርጊቶች ምን ምን ናቸው?
14. ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር የተለያየ የለቅሶ ክዋኔ የሚደረግበት ሁኔታስ አለ? መነሻቸው እንዲሁም በብሔረሰቡ የሚሰጠው ትርጓሜ ምንድን ነው?
15. በብሔረሰቡ ከሚገኙ ጎሳዎች መካከል ሰው ቢሞት ሁሉም በእኩል ደረጃ ለቅሶ ይደረግላቸዋል?
16. የለቅሶ ስርዓቱን ለማካሄድ የሚመረጥ ቦታ እና ሰዓት አለን?

17. አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ሞትን ለመግለፅ /ለቅሶውን ይፋ ለማውጣት/ የሚቻለው እንዴት ነው?

18. በለቅሶው ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎች ምን ይዘው ይመጣሉ?

19. ለቅሶው በማን እና እንዴት ይጀመራል?

20. ሟች ባለስልጣን /የጎሳ መሪ፣ ባለቃልቻ ወዘተ.) ቢሆን ነፍሱ ከስጋው ከተለየችበት ሰዓት እስከ ቀብሩ ብሎም ከቀብር በኋላ ምን ምን ድርጊቶች ይከናወናሉ? ትርጉማቸውስ ምንድን ነው?

21. በብሔረሰቡ የአንድ ሰው ቀብር የሚወሰነው በማን ነው?

22. ሟች ሀብት ንብረት እንዲሁም ስልጣን ቢኖረው ለሌላው የሚያስተላልፈው በምን ሁኔታ ነው?

23. ለለቅሶ ስርዓቱ መከወኛ የሚያገለግሉ ቁሶች ምን ምን ናቸው?

24. በብሔረሰቡ ሟች ከቀብር በኋላ ምን ይሆናል ተብሎ ይታመናል?

25. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች በእድሜና በፆታ እንዴት ይገልፃሉ?

26. በብሔረሰቡ ሰው ሞቶ ከመቀበሩ በፊት ለሟች የሚደረጉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

27. የግንባት ስርዓት አፈፃፀም እንዴት ነው? ሥርዓቱን የሚፈፅሙ ሰዎች በምን ይመረጣሉ

28. አንድ ሰው ሞቶ እስከ ስንት ጊዜ ድረስ ሳይቀበር ሊቆይ ይችላል? በምክንያትነት የሚወሰዱትስ ምን ምን ናቸው?

29. የለቅሶ ስርዓቱን ማን ሊያስጀምር ይችላል?

30. የሀዘን ዘፈኑ ከመጀመሩ በፊት ምን ምን ድርጊቶች ይከናወናሉ? ለምን ይከናወናሉ? ትርጓሜያቸውስ ምንድን ነው?

31. ከቀብር በፊት የሚካሄዱ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች አሉን?

32. ከዚህ ስርዓት ብሔረሰቡ በምን መልኩ ሊጠቀም ይችላል?

33. የመኢኒት ብሔረሰብ ተወላጅ ሆኖ ይህን የለቅሶ ስርዓት የሚያክብር አለ? የሚያክብሩት እንዴት ይታያሉ?

34. ይህን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ለማስጠበቅና ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ የብሔረ
አባላት ትጋት ምን ይመስላል?

35. ሚችን የገደለው በሽታ በለቅሶ ስርዓት አፈፃፀሙ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ይኖራል?

2. ለቤት እመቤቶች የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ሲሞት እቤት ውስጥ ምን ምን ክንውኖች ይካሄዳሉ?
2. ለቅሶ ከመጀመሩ በፊት የሚዘጋጁ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. ከቀብር በኋላ በቤት ውስጥ ምን ም ድርጊቶች ይከናወናሉ?
4. ሴቶች በለቅሶ ስርዓቱ ምን ሚና አላቸው?
5. አባወራ አልያም እማወራ በሞት ቢለዩ ለሟች ቤተሰቦች የሚደረግ እርዳታ አለ? እንደ
ይገለፃል?
6. የሟች ቤተሰቦች በለቅሶ ዕለት የሚደረግላቸው የተለየ እንክብካቤ አለ?
7. ከቀብር በኋላ በሟች መኖሪያ ቤት የሚደረጉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

3. ግላዊ መረጃን ለማግኘት የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስምዎትን ይንገሩኝ
2. የትውልድ ዘመን እና ቦታ የት ነው?
3. የሚከተሉት ሀይማኖት ምንድን ነው?
4. ስለቤተሰብ ሁኔዎ ቢነግሩኝ?
5. የገቢ ምንጭዎ ምንድን ነው (በምን ይተዳደራሉ)?
6. የመኖሪያ አካባቢዎ ምን በመባል ይጠራል?
7. በማህበረሰቡ ውስጥ ያለዎት ቦታ /ድርሻ/ ምንድን ነው?

4. ለተተኳሪ ቡድን ውይይት የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. መኢነት ማለት ምን ማለት ነው ለአካባቢውስ መጠሪያ እንዴት ሊሆን ቻለ?
2. መኢነትን ማን መሰረታት ወይም እንዴት ልትቀረቀር ቻለች?

3. በአሁኑ ወቅት የመኢኒት ህዝቦች የት የት ይገኛሉ?
4. በብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ምን ይመስላል? አከዋወኑ ከተለያዩ ማህበራ
ደረጃዎች አንፃር እንዴት ነው?
5. የለቅሶ ስርዓቱ ምን በመባል ይጠራል?
6. የለቅሶ ስርዓቱ በማህበረሰቡ የሚሰጠውን ቦታ እንዴት ይገልፁታል?
7. የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ሂደቱ በጊዜ ሂደት የመለወጥ አዝማሚያ ይታይበታል
እንዳይለወጥ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት? የማህበረሰቡ ትጋትስ ምን ይመስላል?
8. በለቅሶው ላይ የሚባሉ ግጥሞች፣ የሚነገሩ ተረኮች ወዘተ ካለ ቢነግሩኝ?
9. በማህበረሰቡ በለቅሶ ስርዓት የሚሳተፍ ሰው ዕድሜ ክስንት ይጀምራል?
10. የብሔረሰቡ ተወላጅ ሆኖ ለስርዓቱ የማይገዛ ቢኖር ምን ይደረጋል?

ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የኔ ወጥ ስራ (Original work) መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም ህሊወት አስካ

ፊርማ

ማስረከቢያ ቀን በ9/11/12003/ዓ.ም